አገዛዝና ዓለም-አቀፍ ፖለቲካ የሶርያ ምሳሌ



ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም

በአረብ አገሮች የተካሄደውና በመካሄድ ላይ ያለው ሕዝባዊ አብዮት ማስተዋልና መማር ለሚችሉ ሁሉ ጠቃሚ ትምህርት እያሳየ ነው። መጀመሪያ በአገዛዝና በሕዝብ መሀከል ያለውን ገደል ገልጦ ያሳያል። ከሕዝብ ቁጥር ጋር ሲነጻጸር በጣም ጥቂት በሆኑ የተቀለቡ የሰላማዊና መለዮ-ለባሽ ሎሌዎች በቃሬዛ ታዝሎ ልዩ ዓለም ውስጥ የሚኖር መሆኑ በቱኒዚያም፣ በሊብያም፣ በግብጽም፣ በየመንም ታየ። ገና አልለየም እንጂ በሶርያም እየታየ ነው። በተጠቀሱት የአረብ አገሮች ሁሉ የይስሙላ ምርጫ ሲደረግ ኖሮአል። ሕዝቦቹም የዓርባ ቀን ዕድላችን ብለው ወደእግዚአብሔር ሲያመለክቱ ቆይተዋል። እግዚአብሔር ልቦናቸውን አሳያቸውና የጋረዳቸውን ጥቁር መጋረጃ ቀድደው ጸሐይ ሲወጣ አዩ። የአእምሮአቸው ዓይን ተከፈተ። ብርሃንን ያየ ወደጨለማ መመለስ አይችልም።

በሕዝቦቹ በኩል አስደናቂው ነገር በመሸጦነት ከተያዙት በቀር ወንድ፣ ሴት፣ አሮጊት፣ ሽማግሌ ሕፃናት ሳይቀሩ አገዛዙን ለመጣል በቆራጥነትና በአንድነት ተነስተው ለብዙ ወራት ለአገዛዙና ለሎሌዎቹ ፋታ ሳይሰጡ ትግላቸውን ለድል ማብቃታቸው ነው። የሴቶቹ ተሳትፎ የሚያስደንቅ ነበር። ከአገዛዙ ሎሌዎችም ቢሆን ከህዝብ ጋር ቅራኔ ውስጥ ላለመግባት የፈለጉ ብዙዎች ሎሌነት በቃን እያሉ ከህዝባዊው ትግል ጋር ተቀላቅለዋል።

የአምባ-ገነኖቹ መልስም በጣም የተለያየ ነበረ። የቱኒዚያው አምባ-ገነን ገና በመጀመሪያው ላይ ሳይባባስ ሚስቱን ይዞ ሹልክ አለና ሳኡዲ ገብቶ የሙጢኝ አለ። የግብፁ ደግሞ ትንሽ ከተግደረደረ በኋላ ሥልጣኑን ለምክትሉ አስረክቦ ወጣና በሕዝባዊው ኃይል ቁጥጥር ስር ገባ። ታምሜአለሁ ቢልም በቃሬዛ እየተያዘ ፍርድ ቤት እየቀረበ ነው። የሊቢያው ጋዳፊ ከነልጆቹ ፎከረ፣ ሸለለና በመጨረሻ ስንት ሺህ ሰዎች አጫርሶ የጎርፍ መውረጃ ቦይ ውስጥ ተወሽቆ ተያዘና ጭካኔ ባስተማራቸው ሰዎች አጉል አሟሟት ሞተ። የሱ ቢጤው የየመኑ አምባ-ገነን ከወንበሩ ጋር ተጣብቆ እምቢኝ ብሎ በተጣለበት ቦምብ ቆስሎ ለህክምና ሳኡዲ ሄዶ ቆየ። ተሽሎት ከተመለሰም በኋላ ሥልጣን አልለቅም በማለት ቀጥሎ ብዙ ሰዎችን ከአስጨረሰ በኋላ በድርድር ለቀቀ። ለህክምና ብሎ ወደአሜሪካ ሄደ። ምናልባት እዚያ ለመኖር የማይፈቀድለት በመሆኑ በኢትዮጵያ በኩል ወደአገሩ ገባ። በኢትዮጵያ በጥገኝነት ለመኖር እየተዘጋጀ ነው ይባላል። እጅ እየነሡ ቹክ ሲቀበሉ የነበሩት ሁሉ ለጋዳፊ ለቅሶ አልተቀመጡም። ፈረንሳይ ለቱኒዚያኑ ቤን አሊ ለቅሶ አልተቀመጠም። አሜሪካ መባረክን በርታ አላለም።

እነዚህ አምባ-ገነኖች በሥልጣን ላይ የቆዩባቸው ዓመታት ብዙ ናቸው። ጋዳፊ ዓርባ ሦስት ዓመት፣ መባረክ ሠላሳ፣ ቤን አሊ ሃያ ሦስት፣ ሳላህ ሃያ ሁለት፣ ገና በትግል ላይ ያለው ሀኪሙ አምባ-ገነን ዶር. አሳድ አሥራ ሁለት ዓመታት ገዝተዋል። አእምሮአቸው በትዕቢት ባይደፈን ለትምህርትና ለንስሐ በቂ ጊዜ ነበራቸው። መማርና ንስሐ መግባት ተስኖአቸው ራሳቸውንም አገሮቻቸውንም አጠፉ። በአንጻሩ ሥልጣን አልጠግብ ብሎ ሕገ መንግሥቱን በመጣስ ለሦስተኛ ጊዜ ለምርጫ የገባው የሴኔጋሉ የሰማንያ አምስት ዓመት ሽማግሌ መሸነፉን ሲረዳ ለአሸናፊው ስልክ ደውሎ ‹‹እንኳን ቀናህ!›› ብሎ ሥልጣኑን ለማስረከብ ቆርጦአል። የአፍሪካ መሪዎች ሰማንያ እስኪሞላቸው አይበስሉም እንዳይባል የዚንባብዌው ሙጋቤ አሉ።

ዛሬ የዓለምን ሁሉ ትኩረት የሳበው የአረብ አምባ-ገነን የሶርያው አሳድ ነው። የግብጹና የየመኑ አምባ-ገነኖች በአሜሪካ ስር የነበሩትን ያህል የሶርያው በሩስያ ስር ነው። ከዚያም በላይ ለእስራኤል፣ ለቱርክና ለኢራቅ ጎረቤት ነው። የሶርያ ደቡባዊ ጎረቤት ዮርዳኖስ ነው። ዮርዳኖስ የዙፋን አገዛዝ ሆኖ የምዕራባውያን ምሽግ ነው። ለሶርያ ፋርስም ሩቅ አይደለም። የሶሪያ ጦስ ጦሰኛውን አካባቢ ይበልጥ እንዳይመርዘው ሁሉም ይፈራል። የሶርያው አምባ-ገነን ይህንን እንደጥንካሬ ቆጥሮታል። ስለዚህም የሚቀጣጠለውን እሳት ፈርተው አይነኩኝም በማለት ከሕዝቡ ጋር ሙሉ ጦርነት እያካሄደ ነው። በመድፍና በታንክ ሳይቀር ሕዝቡን እየደበደበ ነው። እስካሁን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ አሥራ ሁለት ሺህ የሚጠጉ ሰዎች ሞተዋል። ቆም ብለን ራሳችንን አንድ ጥያቄ ጠይቀን ከየራሳችን ጋር እንነጋገር። የሶርያው አምባ-ገነን ከሕዝቡ ሲገነጠልና በሕዝቡ ላይ ሲነሣ በርከት ያሉ የጦር ኃይሉ አባላት ከሕዝቡ ጋር ተሰለፉ። ብዙዎች ግን ሎሌነት በልጦባቸው ሕዝቡን እየጨፈጨፉት ነው። አገርንና ሕዝብን አጥፍቶ የሚገኘው ጥቅም ምንድን ነው?

በሶርያ ጉዳይ ለተባበሩት መንግሥታት በምዕራባውያን ኃይሎችም በአረቦች ማኅበርም የቀረቡትን የውሳኔ ረቂቆች ሩስያና ቻይና እየተቃወሙ ለሶርያ ህዝብ ማንም ሳይደርስለት አሳድ በሩን ጥርቅም አድርጎ ዘግቶ ሕዝቡን በጭካኔ እየደበደበ ነው። ሩስያና ቻይና ከዓለም መንግሥታት ተገንጥለው አሳድን የሚደግፉበት ምክንያት ምንድን ነው? ጥቅም ነው። አሳድ የጦር መሣሪያውን የሚገዛው ከነዚህ አገሮች ነው። ከገንዘብ ጥቅምም ሌላ የሶሪያ አቀማመጥ ለሩስያ ወታደራዊ ፋይዳ አለው። ለዚህ ነው አሜሪካ የሶርያን መዳከም የሚፈልገውን ያህል ሩስያ የሶርያን ጥንካሬ የሚሻው። የምዕራባውያንን በጥቅም ላይ የተመሠረተ አመራር አሜሪካ አሁን ለማለ ወታደሮች በሰጠው የእርዳታ መንፈግ ማስጠንቀቂያም ይረጋገጣል።

በሦስተኛው ዓለም የሚገኙ ደሀ ሕዝቦች ቢጨራረሱ ምዕራባውያንም ሆኑ ሩስያና ቻይና ከይስሙላ በላይ ግድ የላቸውም። ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም እንደሚባለው ነው። የሦስተኛው ዓለም አገዛዞች የሕዝቦቻቸውን ሕይወት እንዲጨነቁላቸው መመኘት ከንቱ ነው። አንድ ጊዜ ተማሪዎች ለሰላማዊ ሰልፍ ሲወጡ ተገድለው ስለሞቱት ሳዝን አንድ ጎረምሳ ዲፕሎማት (አገሩን መጥቀሱ አስፈላጊ አይመስለኝም) ‹‹እዚህ አገር ሰዎች በችጋር ያልቁ የለም እንዴ እነዚህ ተማሪዎች በጥይት መሞታቸው ምን ያስደንቃል!›› አለኝ። ሁኔታን መካድ አልቻልኩም። በወገን ጥይት መሞትና በችጋር መሞት ውጤቱ አንድ ነው። ግን ሁለቱንም አሚሚቶች ማኅበረሰባዊ ኃላፊነት የሚመለከታቸው ቢሆንም መንፈሳዊ ቁም-ነገር የጨበጠ ሰው በችጋር የሚሞተውን በጥይት ከሚገደለው ጋር አያመሳስለውም። ለጎረምሳው ዲፕሎማት የሰጠሁትም መልስ ይኸው ነበር።

የሦስተኛው ዓለም አገዛዝና የምዕራባውያን ዓለም-አቀፋዊ ፖለቲካ በጥብቅ የተቆራኘ ነው። አሁን ግን ለምዕራባውያን ኃይሎች የአምባ-ገነኖች ጠቀሜታና አገልግሎት በጥያቄ ውስጥ ገብቶአል። ከአሁን በኋላ ሕዝብን ችላ ብለው በአምባ-ገነኖች ላይ መተማመኑ የማያዋልቅ ለመሆኑ የአረብ አገሮች አብዮት ትምህርት እየሰጣቸው ነው። አምባ-ገነኖች ግን በዚያው ልክ ለመማር ይችላሉ ለማለት የሚቻል አይመስለኝም።

የሁለት ሥልጡን-ህዝቦች ወግ

ዓለማየሁ ገላጋይ

ኢትዮጵያና ጃፓን ከአንድ የጊዜ ማህፀን የተወለደ መንትያ ታሪክ አላቸው። ያቺ የመንታ ታሪኮች እናት የሆነችው ዘመን 1860 ዓ.ም ናት። ኢትዮጵያ በአፄ ቴዎድሮስ፣ ጃፓን በአፄ ሙትሱሒቶ (Mutsuhito) ከመሣፍንት አገዛዝ ነፃ ወጡ። ሁለቱም ወጣት ንጉሠ-ነገሥቶች ‹‹ሥልጣኔን›› በተመሳሳይ ሥሜት የሚመኙ ሆኑ። አፄ ቴዎድሮስ እና አፄ ሙትሱሒቶ የአውሮፓውያን ስልጣኔ ወደ አገራቸው የሚገባበትን መንገድ እኩል አዉጠነጠኑ። ሁለቱም አፄዎች ስለስልጣኔ ህልማቸው የአገር ውስጥ ተቃውሞ ገጠማቸው። አፄ ቴዎድሮስ ከቤተክህነት ነባር ስርዓትና ወግ ጋር ፊት-ለፊት ተላተሙ። አፄ ሙትሱሒቶም ‹‹ቡሺዶ›› (Bushido) እየተባለ ከሚጠራው ከኮንፊሺየስ መንፈሳዊ ነባር ሥርዓትና ወግ ጋር ግጭት ውስጥ ገቡ። አፄ ቴዎድሮስ ተጠለፉ፣ አፄ ሙትሱሒቶ አለፉ...

...ኢትዮጵያና ጃፓን ከአንድ የጊዜ ማህፀን የተወለደ ተመሳስሏቸው ይሄ ብቻ አይደለም። ሁለቱም አገሮች ተዘግተውና ተቆልፈው ከውጭው ዓለም ጋር የተረሳሱበትን ረጅም ዘመን አሳልፈዋል። ጃፓን ከ1630 እስከ 1850 ዓ.ም. ድረስ ከሁሉም የአለም አገራት ጋር የተቆራረጠች ሆና ነበር። JAMES CLAVELL በጃፓን ታሪክ ላይ ተመስርቶ በተፃፈው “SHOGUN” በተባለ መጽሐፉ መሳፍንቶቹ (Shogunate) የተሳሳቱበትን ውሳኔ ለማስረዳት ይጥራል። የፖርቹጋሎችን በሃይማኖት ስም የመንሰራፋትና አገር የመቀማት ዘዴ በመፍራት ሁሉንም ባዕዳን አስወጥተው በራቸውን የጠረቀመ አዋጅ አወጡ። የዜጐች መውጣት፣ የባዕዳን መግባት በሞት እንዲያስቀጣ ተደነገገ። እስከ ሁለት መቶ ሃያ አመት ድረስ ጃፓን ፀጥ ም፣ ፍቅሯም፣ ንግዷም... እርስ በእርስ ተወሰነ። በወግና በስርዓት ተቀበተተች። ጥቂትም ከፖላንዶች ጋር (እጅግ የሩቅ የሚባል) የንግድ ልውውጥ ከማካሄድ ውጭ ጃፓን ለተቀረው አለም የተጠረቀመች በር ሆና ቆየች።

በ1853 ዓ.ም ነበር። አሜሪካ የጃፓን በር በተለይ ለንግድ መክርቸሙ እየከነከናት ሄደ። በመሆኑም አንድ የባህር ኃይል ቡድኗ የጃፓንን ወደብ ለንግድ ክፍት እንዲያደርግ ግዳጅ ሰጥታ ላከች። ግዳጁን የተቀበለው መኮንን Matthew C. Perry ይሰኛል። በመንፈሳዊና በአስተዳደራዊ የገዛ ጉዳይዋ ብቻ ተጠምዳ የኖረችው ጃፓን በአሜሪካ ባህር-ኃይል ጥቃት ተደናገጠች። መሳፍንቶቹ ገዢዎች ከአቅማቸው በላይ ስለሆነ ሺሞዳ እና ሐኮዳቴ ወደቦች ለአሜሪካ ንግድ ክፍት እንዲሆኑ የግዳቸውን ተስማሙ። ጃፓኖች ለራሳቸው ያላቸው ክብር ጥያቄ ውስጥ ገባ። የማንነት ቀውስ አንገበገባቸው። መንፈሳዊ ስልጣኔያቸው ከቁሳዊ ስልጣኔ ሥር እንዲወድቁ እንዳስገደዳቸው ተረዱ-ቁጭት። አፄ ሙትሱሒቶ የዚህ ቁጭት ውጤት ነው። የተውሸለሸሉትን መሳፍንት ገዢዎች ሁሉ ድል አድርጐ የጃፓንን አንድነት እውን አደረገ።

ኢትዮጵያም ተመሳሳይ ዕጣ-ገጥሟታል፡ በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከመካከለኛው ምስራቅ የተነሳው የእስልምና እንቅስቃሴ የኢትዮጵያን የባህር በር ዘግቶ ነበር። ኢትዮጵያ ከዚያ በፊት የነበራት ዓለማቀፍ የዲፕሎማሲ ግንኙነትና የንግድ ልውውጥ ሙሉ በሙሉ ተቋረጠ። ኤድዋርድ ጊበን “History of the Decline and foll of the Roman Empire” የተሰኘ መጽሐፉ ላይ እንዳለው ሆነ ‹‹ኢትዮጵያና የቀረው ዓለም ተረሳሱ›› እንደ ጃፓን ሁሉ ኢትዮጵያም ፀጪ፣ ፍቅሯ፣ ንግዷ... እርስ በእርስ ተወሰነ። በወግና በሥርዓት ተቀበተተች። አንድ ያደረጋት አፄ ቴዎድሮስ እስኪመጣ በዘመነ መሳፍንት ኃይሏ ተባጣጥሶ እና ተዳክማ ቆየች፡ አውሮፓዊ ሥልጣኔን ለመጀመሪያ ጊዜ በአፄ ቴዎድሮስ ብትማትርም የከሸፈ መማተር ሆነባት።

ጃፓን ግን ሥልጣኔ መማተሯ ስላላት-እንዴት?

አፄ ሙትሱሒቶ የጃፓንን መሳፍንታዊ አገዛዝ (Shogunate) አስወግደው ሙሉ ስልጣን እጃቸው እንዳስገቡ አዲሱን ስርዓትና እራሳቸውን ‹‹ሚጂ›› (Meiji) ሲሉ ሰየሙ። ቀጥታም ወደ ባህል አብዮት አመሩ። የጃፓንን ልምድ በዘመናዊው አውሮፓዊ አስተሳሰብ ለመተካት ኃይል ተጠቀሙ። ከአውሮፓ ባስመጧቸው ከባባድ ጦር መሣሪያዎች በጉራዴና በቀስት የተደገፈውን ባህላዊ ሰራዊት (Samurai) ገጥመው ድል መቱት። ይሁንና የባህላዊው ጦር አስተሳሰብ ከጃፓናዊው ልብ ውስጥ እንዳልተነቀለና እንዳልተመታ ተረዱ፡ ስለዚህ ለማስወገድ ከመሞከር ይልቅ የጃፓንን መንፈስ ከአውሮፓዊ መንፈስ ጋር የማዋሃድ ሥራ ሰሩ። ጥንታዊው የጃፓን ትውፊታዊ መሠረት ላይ አዲሱን ሠራዊትና ኢንዱስትሪያዊ ፍላጐት ተከሉ። “The cultural Library” የተሰኘው መጽሐፍ በ10ኛ ቅፁ ገፅ 373 ላይ “There forces combined to create in Japan an irresistible drive toward imperialism the conquest of foreign lands and peoples.” ይላል። (ጃፓን ወደ ኢምፔሪያሊዝም የምታደርገውን ጉዞ የማይገታ ለማድረግና የአካባቢውን አገሮች እንዲሁም ህዝቦች ድል ለመምታት እነዚህ ኃይሎች ህብረት ፈጠሩ) እናም በአርባ አመታት እድሜ ውስጥ ጃፓን ኃያል ከተሰኙት የአለም አገራት አንዷ ሆነች።

የአፄ ቴዎድሮስ የለውጥ ፍላጐት ብቻ ሳይሆን አተገባበራቸውም ጭምር የአፄ ሙትሲሒቶን መንገድ የተከተለ ነበር። ዓፄ ትእዛዘቸው አለቃ ዘነብ አፄው ዘመናዊ ሰራዊት እንዲደራጅ ጥረት አድርገው እንደነበር ይናገራል፡ የባህበሬው ቤት እየተሰራ በመዝረፍ የሚኖረውን ባህላዊ ወታደር ወደዘመናዊ ሰራዊትነት ለማሸጋገር በቅድሚያ የወሰዱት እርምጃ የጉልበት ሥርዓትን በማጥፋት የመንግስት ግምጃ ቤትን ማዳበር ነበር፡ ከዚያ ለሰራዊቱ ቀለቡን ከመንግስት እየሰፈሩ ደሃውን ከማስቃየት እንዲተቃብ ማድረግ። ለዚህም በ1856 ዓ.ም አቡኑና ዋና-ዋና የቤተክህነት ሰዎች በተገኙበት አንድ ጉባኤ አካሄዱ። ጉባኤው የግብር አሰባሰብን የተመለከተ ነበር። አልተሳካም እንጂ።

ስለዚህ ያልተሳካ የአፄው ትልም የእንግሊዙ ቆንስል ፕላውደን በቁጭት ይናገራል። የቴዎድሮስ መሪነት ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን እድገት የሚጠቅም መሆኑን በመረዳቱም ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ለማቀራረብ ተዘጋጅቶ ነበር። ምን ይሆናል፤ ፕላውደን እቅዱን ሳይተገብር በጋረድ ተገደለ።

አፄ ቴዎድሮስ ጉልትን አስቀርተው ግብር በቀጥታ መንግሥት እንዲሰበሰብ የማድረግ እቅዳቸው ተሳክቶ ቢሆን ኖሮ ጃፓን ወደ ኢምፔሪያሊዝም ያደረገችው ጉዞ በኢትዮጵያም በተደገመ ነበር። ይህን የምንለው የአፄው የስልጣኔ ፍላጐት በአውሮፓውያን መንፈስ ስር ብቻ የወደቀ እንዳልነበር በመገንዘብ ነው። የአፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያዊ መንፈስ ከፍተኛ እንደነበር የምናውቀው ነው። እንደ አፄ ሙትሲሒቶ ሁሉ ‹‹ኢትዮጵያዊውን ሥልጣኔ›› ከአውሮፓዊ ሥልጣኔ ጋር አዋህደው አንድ የማይገታ ጉዞ መፍጠራቸው አይቀርም ነበር፡ ለመሆኑ በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ‹‹ኢትዮጵያዊ ሥልጣኔ›› የሚባል ነገር ነበር? ኢትዮጵያዊውስ ሥልጡን ህዝብ ሊባል ይችል ነበር?

ኢትዮጵያ እና ጃፓን በሥልጣኔ ረገድም መንትዮች ነበሩ ማለት ይቻላል። የሁለቱም ነባር ስልጣኔ ከአውሮፓው ስልጣኔ የተለየና መንፈሳዊነት ላይ የተመሰረተ ነው። “Theocentric” ይሉታል። እንደአውሮፓውያኑ ስልጣኔ በቁስ ላይ የተመሰረተና የሰውን ልጅ ማዕከል ያደረገ “Anthropocentric” አይደለም። ኢትዮጵያዊው ሥልጣኔ እንደ አውሮፓዊው ሥልጣኔ የሰው ሕሊና በገዛ ሕግጋቱ እየተመራ በመጣር ያገኘው እንዳልሆነ ዶ/ር እንለ ገብረዮሐንስ ‹‹የክፍተኛ ትምህርት ዘይቤ›› የተሰኘ መፅሐፋቸው ላይ ይገልፃሉ። ኢትዮጵያዊው ሥልጣኔ ‹‹በራዕይ፣ በሕልም፣ በአቡቀለምሲስ... ከአምላክ ወይም ከመላዕክት የተገለፀ የህይወትና የአለም ዘይቤ ወይም ትርጓሜ›› ነው ይሉታል።

ጥንታዊዎቹ ኢትዮጵያውያን ‹‹የነገሮችን ሁሉ ባህርይ ማያ፣ መመልከቻ መነፅሩን እግዚአብሔርን በማድረግ ብዙ እውቀቶች ስለአለምና ስለህይወት›› አግኝተዋል። በእነዚህ እውቀቶች ፋናነት የታሪክ ጉዳናቸውን ቀደው ተጉዘዋል የሚሉት ዶ/ር እንለ ከመቅድማዊ ሁኔታ ከአረማዊነት ወደ ከፍተኛ የሥልጣኔ ደረጃ መድረሳቸውን፣ እውነትን፣ ትክክለኛነትን፣ ፍርድን በመትከል የአናብስት መፈንጫ ምድረበዳ የነበረውን ቤተመቅደስ፣ ቤተ መንግስት፣ ሐውልት፣ እልፍኝ ከአዳራሽ እየሰሩ ከትመዋል። በዙሪያቸው የነበረውን እንደ እሳት ያለውን የሥነ ፍጥረት ተቃራኒነት አስገዝበው ለፈቃዳቸው አስገብረውታል። የኢትዮጵያና የጃፓን ነባር ስልጣኔ ይሄ ነው።

አፄ ቴዎድሮስ አውሮፓዊ ስልጣኔ እንዲገባ ከመፈለጋቸው ጋር ጐን ለጐን ነባሩ ስልጣኔያቸን እንዳይጠፋ ይጣጣሩ ነበር። እውነት፣ ትክክለኛነት ፍርድ የነባሩ ሥልጣኔ አውዶች እንደሆኑ ተገንዝበው በአርአያነት ያከናወኗቸው ነበር። እውነትን የሚያጠፉ፣ ትክክለኛነትን የሚበርዙና ፍርድን የሚያዛቡ ካጋጠማቸው መቀጣጫ ከማድረግ ወደኋላ አይሉም ነበር።

በአፄ ቴዎድሮስ ተጀምሮ የነበረው በነባር ሥልጣኔ ላይ አዲሱን ሥልጣኔ የመገንባት ፍላጐት ከአንድ ተኩል ክፍለ ዘመን በኋላም አልተሳካም። ዶ/ር እንለ ይሄን ተመልክተው እንዲህ ብለው ነበር ‹‹ሁለቱን ስልጣኔዎች የኢትዮጵያንና የአውሮፓን በገዛ መንፈሳችን ድልድይነት ማገናኘት በጥረታችን ግለትና ሙቀት እንዲዋሐዱ ለፍሬም እንዲበቁ ማድረግ። ዋናው ሥራ ይህ ነው። መጀመሪያ የገዛ ራሳችንን ደህና አድርገን ማላመጥ መዋጥ፣ ቀጥሎም ከውጭ የመጣውን በዚሁ መንገድ አግልፎ መደባለቅ ማዋሐድ። ያን ጊዜ ከሁለቱ የሰረፀ በገዛ ወዛችን የተጥለቀለቀ አዲስ የመንፈስ ህይወት ይታያል። በሁለቱ ስልጣኔዎች መዋሃድ መንፈስ ከፍራሉማነቱ፣ ከወላድነቱ እንደገና ይመለሳል።››

በአዲሱ ዘመን... በአዲሱ ትውልድ... በአዲሱ መንግስት ይሄ አልሆነም። ‹‹ነባሩን ኢትዮጵያዊ ስልጣኔ ጥሎ፣ ቻይናዊ እድገትን አንጠልጥሎ›› ሆነናል። እውነት፣ ትክክለኛነትና ፍርድ ሆን ተብሎ ተገስሰዋል። ‹‹እስካልተያዙ ድረስ ሌብነትም ሥራ ነው›› ተብሎ በመሪዎች ተለፍፏል። የልማት እሳቤ ከሰው አልፎ ከመሬት ላይ እንዲውል ተደርጓል። ኢትዮጵያዊ ኩራት፣ በኢትዮጵያዊ ኃፍረት፣ ኢትዮጵያዊ ጀግንነት በኢትዮጵያዊ ፍርሃት፣ ኢትዮጵያዊ እምነት በኢትዮጵያ ሥጋት... ተተክተዋል። ጃፓን ስፈጣን እድገቷ መሰረት ያደረገችውን ነባር ስልጣኔ እኛ ፈነቃቅለን ጨርሰናል። የማንነት ምድረ-በዳ ላይ ቆመናል። ከዚያስ??

ሰውዬውን ከሀሳቡና ከአስተሳሰቡ እንለየው



ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም

አቶ ስብሐት ስለ ውይይትና ስለክርክር ጠቃሚነት ደጋግሞ ይጽፋል፤ በሰንደቅ ጋዜጣም በጻፈው ውስጥ (መጋቢት 12/2004) ‹‹ውይይት እየተደረገበት፣ ሕዝብ እየተሳተፈበት፣ ሓቁ እየተነጠረ፣ እውቀት እየተመረተ፣ ሕዝባዊ ጉልበት እየተጠናከረ እንዲሄድ የሚያደርግ ዓይነተኛ የዴሞክራሲ ሂደት ይመስለኛል፤ ሂደቱ መበረታታት አለበት።›› ይላል፤ በመሠረቱ ይህ ግሩም ሀሳብ ነው፣ ግን ማንም የማይደግፈው የለም ለማለት አይቻልም፤ ይህንን ሀሳብ የማይደግፉት ለስብሐት ቅርብ ናቸው፤ መልእክቱ እንደሚደርሳቸው ተስፋ አለኝ፤ አፈና በኢትዮጵያ ታሪክ በተከታታይና በተለያዩ አገዛዞች የኢትዮጵያን ሕዝብ ጸጥ-ለጥ አድርጎ ለመግዛት መሣሪያ ሆኖ እስከዛሬ ቆይቶአል፤ ከላይም ሆነ ከታች፣ በግልም ሆነ በአደባባይ ይህንን ኋላ-አስቀሪ ባህል ብናጠፋው ትልቅ የአስተሳሰብ እመርታ ይሆን ነበር፤ አስተሳሰብ ሲቃና ብዙ ነገሮች ይቃናሉ፤ እኔ ስጽፍ ዓላማዬ የተዛባ አስተሳሰብ የመሰለኝን ለመጠቆም ነው፤ አስተሳሰባችን ትክክል ካልሆነ ተነጋግረን ለመግባባት አንችልም፤ ከአቶ ስብሐት ነጋ ጋርም ያለኝ ችግር ይኸው ነው።

በተግባር ሲታይ አቶ ስብሐት የሚሰብከውን አያምንበትም፤ አንድ ጊዜ ተመስገን ለጻፈው ሲመልስ፣ በቅርቡ ደግሞ አቶ አስገደ ለጻፈው ሲመልስ የሦስተኛ ክፍል አስተማሪ ጠባይ አሳይቷል፤ በአገራችን በመሠረቱ ሥልጣኑ ጎልቶ ለሚሰማው ሰው በእኩልነት ከተራ ሰው ጋር ያለቅሬታ ለመነጋገር በጣም ያስቸግረዋል፤ የተለመደው ለተራው ሰው ትእዛዝ መስጠት ነው፤ የተለመደው ተራው ሰው ባለሥልጣኑ ሲናገር ከሰማ በኋላ እጅ ነሥቶ መቀበል ነው፤ የደኅዝማቾቹ ሥርዓት እንዲህ ነበር፤ በተግባር እንደደኅዝማች በቃል እንደምሁር ለመሆን መሞከሩ እምብዛም አያራምድም፤ በሕዝብና በአገር ጉዳይ በአደባባይ ክርክር ለመግጠም የፈለገ ሰው ነፃነትና እኩልነት የተከራካሪዎቹ ሁሉ መብቶች መሆናቸውን አስቀድሞ ማወቅ ብቻ ሳይሆን በሙሉ ልብ መቀበልም አለበት፤ አለዚያ ይወርዳል፤ ሀሳብን በሀሳብ መመለስ ሲያቅት እንደስብሐት ወደሰውዬው ዞሮ እሱን ለማብጠልጠል መሞከር ማንንም አይጠቅምም፤ እንዲያውም ወደሌላ ስሕተት ያስገባል።

ክርክሩ አቶ ስብሐት ስለ አክሱምና ስለ ከተማ መንግሥት በተናገረው ላይ እኔ የሰጠሁት አስተያየት ነው፤ ለእኔ አስተያየት ስብሐት የሰጠው መልስ ስለመስፍን ወልደማርያም ምንነት ነው፤ እኔ ስለእኔ ለሚጻፉ አሉባልታዎች መልስ መስጠት አልለመድሁም፤ ጠቃሚም አይደለም፤ ስለቁምነገር መነጋገሩን ትተን ስለግለሰብ ያውም ስለተራ ግለሰብ መነጋገሩ ፋይዳ የለውም፤ የዛሬው የመጀመሪያዬና የመጨረሻዬም ይሆናል፤ በአጭሩ የሚከተሉትን አራት ነጥቦች ላንሣ፤

1. ‹‹ክትልልቅ ሰዎች መገናኘትና ‹‹ማማከር›› እንደታላቅነትና ዝና (Glorification by Association) ስለምታየው ይመስለኛል እንጂ...›› ይለኛል፤ (ለእኔ በቀጥታ ነው የሚናገረው፤ የአጻጻፍ ስርዓት አለማወቅ ሆኖ ነው እንጂ ለእኔ በቀጥታ መናገር አልነበረበትም፤) የእንግሊዝኛውን ሐረግ ከየት አምጥቶ እንደሻጠውና ከዝና ጋር እንዳያያዘው ቢጠየቅ መልሱ መስሎኝ ነበር ሳይሆን አይቀርም፤ አንድ ሰው በትክክል የማያውቀውንና ያልተገነዘበውን ሀሳብ ከግራም ከቀኝም እየነጠቀ ከወረወረ በኋላ ‹‹መስሎኝ ነው›› ቢል ምን ግምት ይሰጠዋል? በተለይ ደግሞ ልማድ ሲሆን ከሳይንሳዊ ጥርጣሬ ይወጣና ሌላ ነገር ይሆናል፤ በአጠቃላይ ግን ከመምሰል ለመሻገር አለመሞከር የአእምሮ ስንፍናን እንጂ አዋቂነትን አያመሳክትም፤ በአለፈው ጽሑፌ ለወዳጄ ለአቶ ስብሐት ለማመልከት ከፈለግኋቸው ነጥቦች አንዱ አደባባይ ከመውጣቱ በፊት ሀሳቡን እንዲያጣራ የሚል ነበር፤ በአለፈው ንግግሩ ላይ ስለአክሱም፣ ስለተምቤንና ስለአጋሜ ያነሳውን የተዛባ ነጥብ በአጋጣሚ ‹‹አንድ የኦሮሞ ልጅ ፕሮፌሰር›› እንዳስለወጠው ነገረን፤ በጡንቻ እርግጠኝነት የተናገረውን በአንድ ‹‹ልጅ›› አስረጂነት መለወጡ የሚያስመሰግነው ነው።

2. ‹‹ጃንሆይና ሥርዓታቸው ሲፈረድበት አንተ መርማሪ ነበርክ።›› እግዚአብሔር ያሳያችሁ! አሁን ይህንን ከአክሱም ጋር ምን አገናኘው? የማያውቀው ነገር ውስጥ እየዘለለ የሚገባው ለምንድን ነው? አዋጁን ቢያነብበውና በጊዜው የነበረውን ሁኔታ ቢያውቅ ጃንሆይ ዘንድ ቀርበን መሐላ እንደፈጸምን ይረዳ ነበር፤ ከዚህም አለማወቅ ለመውጣት አንድ ሌላ ‹‹ልጅ›› ፕሮፌሰር በአጋጣሚ እስቲያገኝ መጠበቅ የለበትም፤ ሰነዶቹ ሁሉ በእጁ እንዳሉ የሚቆጠሩ ናቸው፤ እነዚህን ሰነዶች አይቶ ቢናገር አሉባልታ ውስጥ አይወድቅም ነበር።

3. ‹‹ጠመንጃ በእጃችሁ እያለ የምን ምርመራ መጠበቅ ነው›› ብሎናል ነው የሚለው መንግሥቱ።›› ስብሐት ነጋ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ለምስክርነት ጠራ፤ ምስክርነቱንም ተቀበለ፤ መንግሥቱ ስለስብሐት የሚለውን እንድነግረው ፈልጎ ከሆነ እኔ መንግሥቱን ለምስክርነት አልጠራም።

4. ‹‹የብስጭትና የጥላቻ ፖለቲካ ግን ያደባድባል። ከውጭ ጠላት ጋርም ስለሚያሰልፍ ምናልባት በየጊዜው ይቀያየር ይሆናል።›› አንደኛ አያደባድብም፤ ቢበዛ ያጨቃጭቃል ወደዱላ አያመራም፤ ወደዱላ ካመራ ፖለቲካ መሆኑ ቀርቷል፤ ሁለተኛ በእነዚህ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ስለተነገሩት ስሜቶችና ዝንባሌዎች ሁሉ ከውጭ ጠላት ጋር ስለመሰለፍም ጨምሮ አቶ ስብሐት ከእኔ ይበልጥ በጣም ያውቃል፤ በእኔ በኩል አገርን ለሆድ ወይም ለሥልጣን የለወጠ ዘመድም የለኝ፤ ታላቅ ወንድሜ (ነፍሱን ይማረውና) ባንዳ ሆነና እናቴ ‹‹ማንን ልትገል ነው የጣልያን ወታደር የሆንከው!›› ብለው ቤት አላስገባም አሉትና ወጣ፤ አባቴም ማይጨው ዘምተው የቆሰሉ ናቸው፤ አንድ ወንድሜም በማይጨው ሞቶአል፤ በአባቴም ሆነ በእናቴ በኩል ከጠላት ጋር የተሰለፈ የለም፤ ስብሐት የሚያውቀው ከአለ ይህ የአገር ጉዳይ ነውና በይፋ ሊያወጣው ይገባል።

አቶ ስብሐት ስለሀሳቤ ወይም አስተሳሰቤ ሳይሆን ስለኔ የተናገረውን እዚህ ላይ እስክዘላለሙ እገታና ወደ አቶ ስብሐት አስተሳሰብ እገባለሁ፤ በየካቲት 014 ሰንደቅ ጋዜጣ በተናገረው ላይ ‹‹ታሪክ የፖለቲካ አቋም ስላልሆነ ተነቦ ሊስተካከል ይችላል፤›› በማለቱ የሀሳብና የአስተሳሰብ ግድፈት አድርጌ ያነሣሁት ነጥብ ነበር፤ ታሪክ ተማሪው፤ ታሪክ ተመራማሪው ይለወጣል እንጂ ታሪክ አይለወጥም፤ በአጭሩ እኔ ያልሁት ታሪክ የሆነ፣ የተደረገ፣ ያለፈ ነገር ስለሆነ አይለወጥም የፖለቲካ አቋም ግን እንደጊዜው ሁኔታ ሊለዋወጥ ይችላል፤ ስለዚህ ትክክለኛ አስተሳሰብ የሚሆነው ስብሐት ከተናገረው ተቃራኒው ነው፤ ነበር ያልሁት።

አሁን ደግሞ በወሩ ስብሐት ‹‹ፖሊቲካዊ አቋም የተነሣበት ሁኔታ እስኪቀየር ድረስ አይለወጥም››!!! ይለናል፤ የቃላት ችግር ነው? ወይስ የአስተሳሰብ? እንደሚመስለኝ የፖለቲካው አቋም ግቡን እስቲመታ ድረስ የፖለቲካው አቋም አይለወጥም ማለቱ ነው፤ ይሄ ሃይማኖት ነው ፖለቲካ? በብሪታንያ የሠራተኞችም ሆነ የወግ አጥባቂዎቹ ቡድኖች በኛ እድሜ በጣም ተለዋውጠዋል፤ በሶቭየት ኅብረትማ ትልቅ ለውጥ አይተናል፤ በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካ ውስጥ ሁለቱም የፖለቲካ ቡድኖች በጣም እየተለወጡ ናቸው፤ ከዱሮው ይበልጥ እየተራራቁ የሚሄዱ ይመስላሉ።

ፖለቲካ ማለት ጥቂቶች ሰዎች ተመራርጠው ሥልጣን ላይ ለመውጣት የሚዘረጉት መሰላል ከሆነ የእነዚያ ሰዎችና የሎሌዎቻቸው እድሜ ልክ መስሎ ሊታይ ይችላል፤ ግን ከአለፈው ዓመት ጀምሮ በአካባቢያችን እንደምናየው የገዢዎቹ የፖለቲካ ዓላማና የሕዝቡ የፖለቲካ ዓላማ የተራራቀ በመሆኑ ፖለቲካው እየተለወጠ መሆኑን ነው፤ ታሪክ ግን አይቀየርም።

‹‹የኢትዮጵያ ግዛቶችን ሳንገደድ በውዴታ ለምን አላልፈን እየሰጠን ቆየን?... በምን ምክንያት ነው ነጋ ጠባ ለውጭ ወራሪ ተጋልጠን ተወራሪዎችና ተደብዳቢዎች›› የሆንነው? ጥሩ ጥያቄ ነው፤ ግን ጥያቄው በተለይ ከእንደአቶ ስብሐት ካለ ሰው ለእንደኔ ያለው መቅረቡ ያስደንቃል፤ የቱን ታሪክ ለማስታወስ ነው የተፈለገው፤ የቀድሞው ታሪክ ብዙ ተጽፎበታል፤ በአለፉት ሃያ ዓመታት ስለተቆራረሰው የኢትዮጵያ አካል የሕወሓት (ወያኔ) መሪ የነበረ ሰው ማንን ይጠይቃል? ከአረቦች እርዳታ ሲቀበል የነበረው ማን ነው? የሻቢያ ጥገኛና ረዳት ሆኖ ያደገ ማን ነው? ስለአክሱም ታሪክ ስንነጋገር ስለትናንትናው ልንካካድ አንችልም።

አፄ ቴዎድሮሳዊ ሥልጣኔና አለቃ ዘነብ ኢትዮጵያዊ

ዓለማየሁ ገላጋይ

ያለፉት ሁለት ሳምንታት አክርሞታችን ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያዊነት ጋር እንደነበር አንዘነጋውም። በተለይ ባለፈው ሳምንት ከኢትዮጵያ አፄ ቴዎድሮስን፣ ከጃፓን አፄ ሙትስሒቶን አንስተን ሁለቱን አገሮችና ህዝቦች በንፅፅር አይተናል። ዛሬ ደግሞ በአፄ ቴዎድሮስ ዙሪያ ከነበሩ አሽከሮቻቸው፣ በተለይም ከአለቃ ዘነብ አንፃር የያኔዋን ኢትዮጵያና የስልጣኔ ጅማሬዋን እንቃኛለን።

እዚያው 1960 ዓ.ም....

...ኢትዮጵያም እንደ ጃፓን ሁሉ ከረጅም እንቅልፍ ድንገት የባነነችበት ዘመን ነበር። ጃፓን ቀስቃሿን አፄ ሙትስሒቶን መሪ አድርጋ መንገድ ስትገባ ኢትዮጵያ ግን ከእንቅልፍ ያናጠባትን አፄ ቴዎድሮስን አቅል ነስታ ተደላድላ ተኛች፡ ፡ ሁለቱ ወጣት ነገስታት መጨረሻቸው እንጂ አጀማመራቸውስ ተመሳሳይ ነበር። በሁለቱም ህዝቦች ዘንድ እንደዋነኛ እሴት የሚቆጠረው ወግ፣ ቅኔና ሃይማታዊ ሥርዓት ብቻ የትም እንደማያደርስ በመሪዎቹ ታመነ። የአውሮፓውያኑ ሌላው ሥልጣኔ በነባሩ መንፈሳዊ ልቀት ላይ እንዲመሰረት ጥረት ተደረገ።

ጃፓን ያኔ እንደነቃች እንዲሁ አለች

ኢትዮጵያ ያኔ መልሳ እንደተኛች እንዲሁ አለች።

አፄ ቴዎድሮስ የስልጣኔ አባትነታቸውን ለመዘከር ብዙ ተብሏል በታሪክ መፃህፍት፣ በልቦለድ፣ በቴአትር፣ በግጥም እንደየፀሐፊዎቹና ደራሲዎች ፍላጐት የተለያየ አምሳለ-ገፅታ እየተሰጣቸው ቀርበዋል። ነገር ግን የአፄ ቴውድሮስ እምነት ሆነ ምኞት ከራሳቸው አልፎ ሌሎች ላይ ሲጋባና ሲተላለፍ ለማሳየት የሞከረ ፀሐፊ አልገጠመኝም። የያኔዋ ኢትዮጵያ አውሮፓዊ ሥልጣኔ መሻቷ የአንድ ሰው፣ ግለሰባዊ ህማም እስኪመስል ድረስ በአፄ ቴዎድሮስ ተቀንብቦ ብቻ እንዲቀርብ ተደርጓል።

የጃፓኑ አፄ ሙትስሒቶ የፀነሱትን ሥልጣኔ ተንከባክበው በማዋለድ የተረከቧቸው ሦስት ሰዎች ነበሩዋቸው። እነሱም ካትሱ የተባለ ተመራማሪ፣ ፉኩዛ የተባለ የስልጣኔ አቀንቃኝና አድሜራል ቶጐ የተባለ የጦር ሰው ናቸው። በተመሳሳይም የአፄ ቴዎድሮስ የስልጣኔ ፍላጐት እውን እንዲሆን የለፉ ሶስት ሰዎች ነበሩ። አለቃ ዘነብ የተባሉ ተመራማሪ፣ አለቃ አካለወልድ የተባሉ የስልጣኔ አቀንቃኝና ገብርዬ የተባለ የጦር ሰው፡ ፡ አፄ ሙትስሒቶ የታሪክ አውድ ሆነው ሲቀርቡ ሶስቱ ሰዎቻቸው መቀሰቻ ተደርገው ይቀርባሉ፡ ፡ አፄ ቴዎድሮስ ግን ከእነዚህ መቀሰቻዎቻቸው አንፃር አልተዳሰሱም።

አለቃ ዘነብ፣ አለቃ አካለወልድ እና ገብርዬ የአፄ ቴዎድሮስ መስሎ አዳሪዎች ነበሩ፡ ፡ ጌታውን ለማወቅ መስሎ አዳሪውን አሸክር መመርመር ብልህነት ነው። አለቃ ዘነብ የአፄ ቴዎድሮስ የቴክኖሎጂ ጥማት ምልክት ነው። አለቃ አካለወልድ ደግሞ አፄው በአስተዳደር በኩል የነበራቸውን የማዘመንና ፍትህና ርትዕን የማስፈን ፍላጐት የሚተረጉሙ ምሁር ነበሩ። ገብርዬ ደግሞ የግዛት አንድነትን ለማጥበቅ አፄ ቴዎድሮስ ብቻ የሚያውቁት የውል ቋጠሮ ነው። በዛሬው ዕሁፍ አፄ ቴዎድሮስንና የያኔዋን ኢትዮጵያ የምንመለከተው ከአለቃ ዘነብ አንፃር ብቻ ይሆናል። አፄ ቴዎድሮስ እራሳቸው ‹‹ይማሯል እንደ አካልዬ፣ ይዋጓል እንደ ገብርዬ›› ያሉላቸው ሁለት ሰዎች ባልተቀጠበ ሌላ ቀን ይዳሰሳሉ።

አለቃ ዘነብእንኳን ታሪኩ ስሙም ተሟልቶ ያልተገኘ የአፄ ቴዎድሮስ የአንድ ወገን ጥላ ነበር። አለቃ ዘነብ የአፄ ቴዎድሮስ ‹‹መስሎ አዳሪ›› ነበርና የአፄው የአንድነት ህልም አባቱ አድርገው ይጠራበት ነበር። ማለቱ ‹‹ከዘነብ ኢትዮጵያዊ›› እያለ ነበር የሚፅፈው። እንደነ አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ዘብሔረ ዘጌ ቢል አፄ ቴዎድሮስ ስለማይቀበሉት ነበር ‹‹ዘነብ ኢትዮጵያዊ›› የሚለው። (የዚህ ዘመን ለውጥ ‹‹በዘመቻ ቴዎድሮስ›› ድል ቢቀናጠጥም በዐረ-ቴዎድሮስ ፖሊሲ ከስማቸው ኋላ ‹‹ኢትዮጵያዊ›› የሚሉ በጠላትነት ተፈርጀዋል)

አለቃ ዘነብ ታሪክ የዘነጋው ታሪክ ፀሐፊ ነው። የአፄ ቴዎድሮስን ታሪክ ሲፅፍ እራሱ ታሪክ እየሰራ እንደሆነ ዘንግቶታል። በመሆኑም የአባቱ ስም ማነው? ከሚለው ጀምሮ የት ተወለደ? መቼ ተወለደ? ምን አይነት ሰው ነበር? አስተዳደጉ? ትምህርቱ?... ለሚለው እንኳ ታሪክ አይኑንም ጆሮውንም ነፍጐታል። ስለአለቃ ዘነብ መጥቀስ ግድ የሆነባቸው አንዳንድ ፀሐፊዎች የሰሚ-ሰሚያቸውን ባልተረጋገጠ አካኋን ጣል አድርገው ያልፋሉ። ለምሳሌ ፕ/ር ታምራት አማኑኤል በ1936 ዓ.ም. በዓፋት ‹‹ስለኢትዮጵያ ደራሲያን›› የተባለ ጥናት ላይ እንዲህ ይላሉ፡-

‹‹....ፊተኛ ሁኖ ንፁህ በሆነ አማርኛ የተፃፈው መጽሐፍ የአፄ ቴዎድሮስ (1947-1860) ታሪክ ነው። ደራሲው የአፄ ቴዎድሮስ ፀሐፊ ትእዛዝ አለቃ ዘነብ የተባለው የሸዋ ሰው ነው። የሞተበትን ዘመን ለማወቅ አልተቻለም። ነገር ግን በ1880 ዓ.ም. ግድም ትግሬ ሁኖ ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ሲፃፃፍ እንደነበር እርግጥ ነው።››

ፕ/ር ታምራት አማኑኤል አለቃ ዘነብ በ1880 ዓ.ም. ትግሬ ሁኖ ከአፄ ምኒልክ ጋር ይፃፃፍ ነበር ይበሉ እንጂ አለቃ አፅሜ (አፅመጊዮርጊስ) በአንድያ መጽሐፋቸው ላይ የአለቃ ዘነብን የመሞቻ ዘመን ወደ 1869 ዓ.ም. ያወርዱታል። እንዲህ በማለት፡-

‹‹አፄ ምኒልክ ከወሎ ወደ ሸዋ መጡ፤ ልቼ ገቡ፣ ወዲያው በጥቅምት (1869) ብዙ ጦር አስከትተው ብዙ ፋኖ አስከትለው ወደ ጉራጌ ዘመቱ፡ ፡ በጥቅምት 21 ቀን የንጉስ ሰራዊት አለቀ። አለቃ ዘነብ የሚባል አዋቂ መጽሐፊ ጨዋታ ብሎ የደረሰ፣ የዚያኑ ዕለት ሞተ። ብዙ መካንንት ሞቱ...››

ለአለቃ ዘነብ ብቸኛ የመኖሩ ማረጋገጫ ታሪኩ ሳይሆን እንደዱካ ታትመው የቀሩ ሁለት መፃህፍቱ ናቸው። በአፄ ቴዎድሮስ ህይወት ላይ የሚያተኩረው የታሪክ መጽሐፍ እና ‹‹መጽሐፈ ጨዋታ ሥጋዊ ወመንፈሳዊ›› የተሰኘ ድርሰቱ አለቃ ዘነብ እንዴት ያለ የዕውቀት ሰው እንደነበር ይመሰክራሉ። በተለይ ‹‹መጽሐፈ ጨዋታ›› አለቃ ዘነብ ለአፄ ቴዎድሮስ ባለሟልነት ያበቃው ዕውቀቱና ሳይንሳዊ ምርምሩ እንደነበር ምስክር ነው። አለቃ ዘነብ በዘመኑ አሰላላይ (“Thinker”) ነበር ቢባል አይበዛበትም። ህዝቡ ስንፍናን እንዲጠላ ሳይንስን እንዲቀበልና ነገሮችን እንዲመረምር አጥብቆ ይወተውታል። አንዳንዴም ያውጠነጠነውንና የመረመረውን እንደፍንጭ ጣል ያደርጋል። አለቃ ዘነብ በአርግጥም አሰላላይና ተመራማሪ ነበር፡ ፡ እንደውም በአፄ ቴዎድሮስ ዘብጥያ ከወረዱት ፈረንጆች ውስጥ ዶክተር ሔነሪ ብላንክ ስለአለቃ ዘነብ እንዲህ በማለት በመጽሐፋቸው ምስክርነት ይሰጣሉ።

‹‹ከሚገ-ባችን ሹማምንት መካከል ደብተራ ዘነብ የንጉሰ ነገስቱ ፀሐፊ አሁን የዓለማየሁ (የአፄ ቴዎድሮስ ልጅ) አስተማሪ በጣም ብስልና ታማኝ የሆነ ሰው አዘውትሮ ይጠይቀን ነበር። ይህ ሰው ስለክዋክብት የማወቅ ፍላጐቱ እጅግ ብርቱ ስለሆነ በመጣ ቁጥር እየተደጋገመ የክዋክብት ታሪክ እንዲነገረው ስለሚሰለቸን እንደ እብድ እንቆጥረው ነበር።››

ዶክተር ሔነሪ ብላንክ ጥቁምታ እንደሰጡን አለቃ ዘነብ የማይታክት እውቀት አሸጋጋሪ ነበር ማለት ነው። ‹‹መጽሐፈ ጨዋታ›› ላይ እንደምንረዳው ስለክዋክብት ብቻ ሳይሆን ስለኃይል ማመንጫ ቴክኖሎጂዎችና ስለሳይንሳዊ ጉዳዮች ጠያቂ፣ ተርጓሚና ወገኖቹን ለተሳታፊነት የሚጐተጉት መምህርም ጭምር ነበር። በጌታው በአፄ ቴዎድሮስ የሚደገፍ ተግባር በመሆኑም አለቃ ዘነብ እውቀት ለመቅሰም የባዕዶች ጉያ አይጠፉም ነበር። ለነገሩ አፄ ቴዎድሮስም እንዲሁ እንደነበሩ ይነገራል። ፈረንጆች ዘንድ ያለው እውቀት አገር ውስጥ እንዲቀር አንዳንድ እርምጃዎችንም ያዘወትሩ ነበር። ለምሳ አፄው ቤተመንግስታቸው ውስጥ ለቅርብ አገልጋይነት አዘውትረው የሚቀጥሩት ከአውሮፓውያን ጋር የሰሩትን ሰዎች እንደነበር ሔነሪ ብላንክ ይገልፃል። በመጨረሻው ጊዜ ካጠገባቸው ያልተለየው የቤት አሸክር ምዕዋ ምክትል ቆንስል የነበረው የባሮኒ አሸክር ነበር። አንድ ፓል የተባለ ወጣት አሸክራቸውም በተመሳሳይ የሚስተር ወክር አሸክር ነበር። ሌሎቹም አሸክሮቻቸው የፐላውድን የቤልና የካሜሮን አሸክሮች ነበሩ። በዚህ እውቀት መሸጋገሪያ ዘዴ ተጠቅመው ሳይሆን ይቀራል አፄ ቴዎድሮስ አንድ የሞተር መርከብ የሰሩት? ለዚህ ዶ/ር ብላንክ ምስክርነቱን ሰጥቷል።

አለቃ ዘነብም የጌታው ጥላ ነው። አፄ ቴዎድሮስ ክብራቸው የማይፈቅድበት ቦታ እየተገኘ፣ የአፄው ክብር የማይፈቅድበት ቦታ እና ክብራቸው የማይፈቅደው ባህሪ ውስጥ እየተሰለቸም ቢሆን በእውቀት ቃርሚያ ላይ ተሰማርቶ ወገኖቹን ሳይንስ ለመቀሰብ ያደገደገ ታታሪ። ‹‹መጽሐፈ-ጨዋታ ስጋዊ ወመንፈሳዊ›› የተባለ ድርሰቱ ለእነዚህ እውቀት እንቢ-ባይ ወገኖች የቀረበ ማዕድ ነው። ደጋግሞ እንዲህ በማለት ይመክራል። ‹‹ድንጋይና ጭቃ ቢቀጣጠሉ ታላቅ ቤት ረጅም ቅጥር-ይሆናሉ፤ እናንተም መሬታውያን ሰዎች እንዲህ ብትረዳዱ ጥበባችሁና ኃይላችሁ ከሰማይ በደረሰ።››

የዚች የአለቃ ዘነብ ንግግር ውስጥ ታላቁ የዚያ ዘመን የስልጣኔ መንፈስ እንደ ዘንዶ ተጠቅልሎ እናገኘዋለን። ‹‹ታላቅ ቤት››፣ ‹‹እረጅም ቅጥር››፣ ‹‹መሬታውያን››፣ ‹‹ጥበባችሁ››፣ ‹‹ኃይላችሁ››፣ ‹‹ከሰማይ››... የሚሉት ቃላት የሚወክሉት ምንድነው? ግልፅ ነው! ባለፈው ሳምንት ያየናቸው የሰውን ልጅ ማዕከል ያደረገው አውሮፓዊው ስልጣኔ (Anthropocentric) እና እግዚአብሔርን ምርኩዝ ያደረገው ኢትዮጵያዊ ስልጣኔ (Theo centric) አደባልቆ የማስኬድ ፍላጐት ነው፡ ፡ ከመንፈሳዊ ንፅህና ባሻገር ምድራዊ ትጋትና ትብብር እንደ ሰማይ (ጽድቅ) ከሚቆጠር ስኬት ላይ እንደሚያደርስ የሚጠቁም ነው። መንፈሳዊ ትጋትን አያናንቅም፣ ስጋዊ ትጋትንም አያጣጥልም። ከአፄ

ወደ ገፅ 14 ዞሯል

ሙንጣዝ-ቡልቅበሽ ገድሏል እያስመሰከረ፤ አንበሳው ታከለ ራሱን ሲገድል ማነው የነበረ?



ከታዴዎስ ታንቱ

ተኩስ ተከፍቷል! የመትረየስ ድምፅ ተሰምቷል። የአርበኛው ጊዜአዊ ማረፊያ ተከብቧል፡ ፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ልዩ ኮማንዶ ተጠናክሮ መጥቷል። ውድቅት ሌሊት መሆኑን አንጣ! ከመትረየስ ተኩስ በመለጠቅ ቦምብ ተወርውሯል! ልዩ ኮማንዶ ሁለት ሐሳብ ታጥቋል! አርበኛው በሩን ከፍቶ ከወጣ ወዲያው በጥይት ለማንሳት ቋምጧል። አሊያም ከኬቱ በእሳት ለማውደም ተስፋ ሰንቀዋል። ግን ሁለቱም ምኞት ሆኖ ይቀራል። ታሪክ የምሥክርነት ቃሉን በቃሉ አስቀምጧል። ምኞት የፋሽስት ወራሪ የተስፋ ፈረስ ሆኗል! አንበሳው አርበኛ በሕይወት ቆይቶ በቀኑ አልፏል።

ምድሪቱን ዕልመት ውጥዋታል። የጨለማ ቡልኮ በኛኖ ስፋት አርፎባታል! አርበኛው በተኩሱ ፈዕሞ አልተደናገጠም። ከብርሃን በፊጠነ ቅፅበት መትረየሱን ጨብጦታል። በአንድ እጁ ደግሞ ዝናሩን አንሥቶታል። መትረየሱን ከእግሩ ሥር አስጠግቶታል፡ ፡ የሚባክን ጊዜ አልነበረውም። የአንበሳ ልጅ አንበሳ ነው። ወዲያው ዝናሩን ከወገቡ ጋር አዋሐደው። የፋሽስት ኢጣሊያ ልዩ ኮማንዶ ተኩሱን አፋፍሞታል፡ ፡ አርበኛው በሩን በቀስታ ከፈተው። በራሱ ድምፅ ላይ ብቻ ሳይሆን መዝጊያውም ኳኳታ እንዳያሰማ ማዕቀብ ጥሎበታል። ፀጥ ብሎ አድፍጧል። የልዩ ኮማንዶ ተኩስ እንደ ዶፍ ይወርዳል። ጥይት የተረፈው ፋሽስት ያርከፈክፋል። አርበኛው በመዝጊያው ሥር መትረየሱን አስተካክሎ ያዳምጣል! ተኩሱን ሰምተው በአቅራቢያው በዕረፍት ላይ የነበሩ አርበኞች ተንቀሳቅሰዋል፡ ፡ አፀፋ ባለመሰማቱ የፋሽስት ኮማንዶ ተኩሱን አቋርጧል። ጥርጣሬ ውስጥ ገብቷል። በዚያች ጎጆ ውስጥ አርበኛው መኖሩን ላለማመን አምኗል። ግን አርበኛው በእርግጠኝነት ነበረ። ብዙም አልቆየም፡ ፡ መኖሩን ለማሳወቅ መዝጊያውን አስደግፎ አንድ ጊዜ መትረየሱን አናገረው። አልደገመውም! ፀጥታ! የመቃብር ፀጥታ! ወዲያው ልዩ ኮማንዶ ተኩሱ ወደ ተሰማበት አቅጣጫ ተማተለተለ። አርበኛው ያመለጠ መስሎታል። አጅሬ ግን ዘይዷል። የውሸት የተኩስ ሽፋን ሰጥቷል። እሱ ግን በሌላ በር ወጥቶ በተገን ጥግ ይዟል። ተዘጋጅቷል! ጊዜ አላባክነም! ሁለት ጊዜ መትረየስ አሰማ። መብረቅ በጨለማ ውስጥ ታየ፡ ፡ ልዩ ኮማንዶ የአፀፋ ተኩስ አላሰማም። ይልቁንም እየተሸሎከሎኩ ማምለጫ ይፈልግ ገባ። የወገን ኃይል ጎለበተ! አርበኞች የበላይነትን ጨበጡ! በ1930 ዓ.ም. ይህ ሆነ! ታከለ ወልደ ሐዋርያት በቡሬ!

ጀግናው ታከለ ለእናት ሀገራችን ለኢትዮጵያ ለአርበኝነት ታበቦ የተሰራ ይመስላል። ቆራጡ ታከለ በ1928 ዓ.ም. የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አዲስ አበባ ሲገባ በከተማው ውስጥ ከታዩት ሁለት ባለስልጣናት አንዱ እንደ ነበር ታሪክ እማኝነቱን ይሰጣል። ሁለተኛው ደግሞ አበበ አረጋይ ነበር። ታከለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድንገት በባቡር ተሳፍረው ወደ ስደት ማቅናታቸውን ሰምቶ በድንጋጤ ወደቀ! ሆኖም ራሱን አረጋግቶ ለአርበኝነት ተጋድሎ በፍጥነት ከውሳኔ ላይ ሊደርስ ችሏል።

የሀገር መመኪያ የሆነው ታከለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከተሰደዱ በኋላ ሕዝቡን ስብሰባ ጠርቶ አወያይቷል። በዚህ ሒደት ከሕዝቡ ጋር በበለጠ ተቀራርቧል። መረጃ ሰጥቷል። ሐሳብ ተመግቧል፡ ፡ የወደፊት የትግል አቅጣጫን ጠቁሟል። ማለፊያ የውይይት ሁኔት ታይቷል። ጎበዛዝት በቁጠኝነት የአርበኝነት አቋም ወስደዋል። ለሀገራቸውና ለሐይማኖታቸው ለመሰዋት ቃል ገብተዋል። ጊዜው በፊቀደው ቋንቋ በጊዜው አቅራርተዋል። በእናት ሀገርና በሚስት የለም ዋዛ!! የለም! የለም! የለም!

በጎበዛዝት ጎራ የጀግንነት አቋም ተመዝግቧል። በተቃራኒ የተቃርኖ ሐሳብ በስብሰባው መካከል መፍለቁ ግን አልቀረም። ፊሪ የእናቱ ልጅ አይደል? ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከተሰደዱ በኋላ መፈራገጥ የዕልቂት ደወል መሆኑን በአዕንኦት የተናገሩ ተስተውለዋል። በምክንያቱ ምክንያት በስብሰባው ላይ አንድ ዓይነት አቋም አልተወሰደም። ውይይቱ ግን ቀጥሏል! በድንኳን ውስጥ ይካሔዳል! ሆኖም በጥባጭ እያለ ማን ጥሩ ውሃ ይጠጣል? በስብሰባው ሂደት የፋሽስት ኢጣሊያ አየር ኃይል ከሰማይ ወረቀት ያዘንብ ገባ። ሕዝቡ የታከለን ሐሳብ እንዳያስተናግድ የሚያሰስቡ ወረቀቶች ወደ ምድር ወረዱ። እንዲያውም ታከለና ተፈሪ አንድ መሆናቸው ተጠቅሷል። በግልፅ ቋንቋ ተቀርያ በጠራራ ፀሐይ ዘንባል። ወራሪው ኃይል ታከለን ከሕዝቡ ለመነጠል አቅዷል። ግን በከንቱ ደክሟል! ጀግና በወሬ አይፈታም! ፊሪ በሸካም አይነሳም! ጎበዛዝት ወስነዋል! ታከለ ቆርጧል!

ምን አለ ታከለ?

ምን አለ?

ሀገሬን ለሰው!

ሀገሬን ለሰው!

አልሰጥም አለ!

ያም ሆነ ይህ ታከለ አሁንም በዋና ከተማችን ውስጥ ይገኛል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ግን ዘልቆ ገብቷል። በአንዳንድ ቦታዎች በአሰራር ጉዞ ይስተዋላል። ታከለ ደግሞ ያለ ምክንያት አልዘገየም። ልብ ያሰበውን ወደ ተግባር ያመጣዋል። ሰዓቱ ደርሷል፡ ፡ ፊረሱን አስጭኖ ተነስቷል። ዳንገላሳ አያጫውትም! ሶምሶማም አይመታም! ሽምጥ ይጋልባል! ውብ የሳር ቤቶችን በእሳት ይለኩሳል! ለኩሷል! ለኩሷል! ጊዜ ወርቅ ነው! ታከለ በጣም ፈጥኗል! ለኩሷል! ለኩሷል! ለኩሷል! የሰዶምና ገሞራ እሳት ወርዷል! ዋና ከተማችን ነድዷል! ዘረፋው ጦፏል! ተኩስ ይሰማል! ታከለ ግዳጁን ፈፅሟል! ለዋናው ግዳጅ ደግሞ ተነስቷል! የአርበኝነት ጉዞ ሰዓት ደወል ያሰማል! ዛሬ ነው! አሁን ነው!

ታከለ መትረየሱን፤ ቦምቦችንና ሽጉጦችን ታጥቆ ተንቀሳቅሷል። ጭብጦ፤ ባሶ፤ ባቄላና አተር በአህዮች ጀርባ ተቀርቅበዋል። የማብሰያ ዕቃዎችም አልተዘነጉም። ከተከታዮቹ መካከል የጦር መሳሪያ ያልያዙ ብዙ እንደነበሩ ታውቋል።

ጀግናው ታከለ ለአርበኝነት የደቡብ ኢትዮጵያን መሬት ወድዷል። ምክንያቱም ደቡብ ኢትዮጵያን አሳምሮ ያውቃልና ነው። እንዴት ሊያውቅ ቻለ? በንግስተ ንግስታት ዘውዲቱ ዘመነ መንግስት በራስ ተፈሪ ትዕዛዝ በደቡብ ኢትዮጵያ ፀረ-ባርያ ንግድ ዲረክተር ሆኖ ተዘዋውሯል። ታከለ ተራማጅ አስተሳሰብ ሰንቋል። ባርያ እንዳይሸጥ አግዷል። ተወዳጅነትን ገብይቷል። ለብዙ ዓመታት የባሪያ ፈንጋይ የነበረ አላሆ ሎሣ የተባለ ግለሰብ ቦዲቲ ተብሎ በሚታወቅ ገበያ ውስጥ በፍርድ ተሰቅሏል። ይህ ውጤት በታከለ ጥረት ተመዝግቧል። አንዳንድ ፈንጋዮች ደግሞ በመኖሪያ ቤታቸው ደጃፍ ተንጠልጥለዋል። የተቀሩት ተረሽነዋል። የባሪያ ንግድ በአዋጅ ቀርቷል። በዚህ ሒደት የታከለ አስተዋዕኦ ትልቅ ስፍራ ይሏል፡ ፡ ጀግናው ታከለ በዚህም ጀግና ሆኗል። በተራማጅ አመለካከቱ በዘመኑ ጎልቶ ወጥቷል።

አርበኛው ታከለ አሁን በጅማና በሊሙ መካከል መሸጓል። ሞት አይፈራም። ድንጋይ ተንተርሷል። አሸዋ ለብሷል። የቁርጥ ቀን ልጆች ከጎኑ ቆመዋል። ማን ይፈራል ሞት? ስማይና ምድር ለምን አይገለባበጡም? ከጀግና ጋር ለመሞት የቆረጡ መጥተው ተቀላቅለዋል። ተጨማሪ የሰው ኃይል ለወገን ተገኝቷል። ታከለ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሷል፡ ፡ እልህ ንጦታል። ወኔ ገፍትሮታል። የፋሽስት ወራሪ ኃይል የጀኔራል ሚሊዮቲን ትእዛዝ ይጠባበቃል፡ ፡ ሦስት ክፍለ ጦር በተጠንቀቅ ቆሟል። ጀኔራል ሚሊዮቲ ትዕዛዝ አላወረደም። የአርበኞች መሳሪያ ኋላ ቀር መሆኑን ፋሽስት አውቆታል። አሁን የፋሽስት ወራሪ ኃይል ተንቀሳቅሷል። የአርበኞች መረጃ ይህን አመልክቷል። በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ተኩስ ይደመጣል። ትእዛዝ ለክፍለ ጦሮች ወርዷል። አንድ! አንድ! አንድ! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በነፍስ ወከፍ መሳሪያ ተኩስ ከፍቷል። የአርበኞች አፀፋም ቅፅበታዊ ሆኗል። ጦርነቱ ቀጥሏል። ቀናት አልፈዋል፡ ፡ ብዙ አርበኞች ተሰውተዋል። ፋሽስቶች ደግሞ የውሻ ሞት ተስተናግደዋል። ሳምንታት አልፈዋል። አርበኞች በቁርጠኝነት ቀጥለዋል። አንድ ወር ሙሉ የተፋፋመ ጦርነት ተካሂዷል። ጀግናው ታከለ 130 ሰው ብቻ ቀርቶታል። ዕብሪት ፍፃሜው ውድቀት መሆኑ ታውቋል። ጀኔራል ሚሊዮቲ አንገቱን ተቀልቶ ወድቋል። የኢትዮጵያ ልጅ እንዲህ ይሰራል። አርበኞች የበላይነትን ይዘዋል። የፋሽት ወራሪ ኃይል ፈርጥጧል፡ ፡ 1929 ዓ.ም.

ለነፃነታችንና ለአንድነታችን ቆርጦ የተነሳው ጀግናው ታከለ ከውጊያ በተጓዳኝ የአርበኞችን አንድነት ለመፍጠር ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል። በዚህም መሰረት የሸዋን፤ የወሰጋን፤ የኢሊባቦርንና የከፋን አርበኞች በደብዳቤ አገናኝቷቸዋል። ታከለ ሐሳቡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልን በማባረር የሪፐብሊክ መንግስት ለመመስረት እንደነበር ታውቋል። ታከለ የማስተባበር ችሎታው ይደነቃል። በጎጃም ውስጥ በመለስተኛ ልዩነት የተራራቁ አርበኞችንም በማቀራረብ ለአንድ ዓላማ በቁርጠኝነት እንዲቆሙ አድርጓል። እንዲሁም ወደ ሱዳን ተሻግሮ ስደተኞችን አነቃቅቷል። ወደ ጎንደር አምርቶ ደግሞ ከአርበኞች ጋር በስፋትና በጥልቀት ተወያይቷል። በዚህ ሒደት ጊዜያዊ መንግስት ለማቋቋም ከስምምነት ላይ ተደርሷል።

ይህ ጥረት ቀጥሎ ሳለ ጀኔራል ቤሊና በተባለ የፋሽስት ወራሪ አዛዥ የተመራ ተዋጊ ጀግናውን ታከለን ጦርነት ሊገጥመው መጣ። ባንዳው ራስ ኃይሉ ተክለ ሐይማኖት ከጀኔራሉ ጋር ነበረ፡ ፡ ጦርነት ተከፈተ። አርበኞች የበላይነትን ተጎናፀፉ። ጀኔራል ቤሊና ፈረጠጠ። ራስ ኃይሉም ሸሽቶ በፈረስ አምቦ ገባ። እነታከለ የጀኔራል ቤሊናን ወራሪ ኃይል ከደመሰሱ በኋላ በቀጥታ ወዴሣ ወደተባለ ቦታ አመሩ፡ ፡ ለዕረፍት ያልተፈጠረው ታከለ እዚያም ከፋሽስት ጋር ጦርነት አካሄደ። አሁንም ታከለ ድል ነሥቷል። ይዋጋል! ድል ይነግል! ይዋጋል! ድል ይቀዳጃል!!

ትግሎች ተካሄደዋል። ድሎች ተመዝግበዋል፡ ፡ ጦርነቱ ግን ማለቂያ አልነበረውም። መስከረም ወር 1930 ዓ.ም ነው። ታከለ በሁለት ጀኔራሎች የተመራ ወራሪ ኃይል መጣበት። አይሮፕላኖችም ቦምብ አዘነቡ፡ ፡ ምድር ቀውጢ ሆነች። አንደኛው ጀኔራል በአርበኞች እጅ ተገደለ። እንዲሁም ከቦምብ ጣይ አይሮፕላኖች አንዱ ተመትቶ ወደቀ። ድል የአርበኞች ሆነ።

በቆራጡ አርበኛ በታከለ የተመራው ተዋጊ በመቀጠል ወደ ሆሮ ጉድሩ አመራ። አሁንም ጦርነት ተካሔደ። አርበኞች አጠቁ። ይህ ከሆነ በኋላ ደግሞ

ለታከለ ከተገጠመው የተመዘዘ

ከሸዋ ጋሌንኒ የተባለ ጀኔራል እንዲሁም ከጎንደር አንድ ጀኔራል ተጨምሮ ባዳንግላ በኩል ታከለን ሊወጉ መጡ። በአርበኞች መረጃ እውነትነቱ ተረጋግጧል፡ ፡ በፍጥነት ዝግጅት ተደረገ። ታከለ አርበኞችን ይዞ ተራራ ላይ ወጣ። ሃያ መትረየሶች ወራሪውን ኃይል ይቆላሉ። በተራራው ላይ ዙሪያውን ተጠምደዋል። ልብ ያለው እስቲ ወደ ላይ ይውጣ! አርበኞች ቁልቁል አርከፈክፉ። ጀሌ ደግሞ በናዳ አጠቃቸው። ፋሽስቶች እንደ ቅጠል ረገፉ። አርበኞች ድል አደረጉ። ጀኔራል ጋሌንኒ ተጠናክሮ ቡሬን ለመያዝ እንደ ገና መጣ። ብዙ ሰው አለቀበት። ፈረጠጠ።

ጀግናው የጦር አርበኛ ታከለ ስደተኞችን ለማስተባበር እንደ ገና ወደ ሱዳን አመራ። ከእንግሊዞችም ጋር ተገናኝቶ ስለአርበኝነት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተወያይቷል። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግን ይህን ግንኙነቱን አልወደዱለትም። ሆኖም ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ታከለ ከእንግሊዞች ጋር ሞያሌ ውስጥ ተገኘ። እነታከለ ባንዳ እያስከዱና አርበኛ እያበረታቱ ወደ መኻል ሲዳሞ ገቡ። በዚህን ጊዜ በሦስት ጀኔራሎች የሚመራ የፋሽስት ወራሪ ኃይል መጣባቸው። ጦርነት ተከፈተ። ድብልቅልቁ ወጣ። ብዙ አርበኞች ተሰዉ። የፋሽስቶችም ሬሣ ተከመረ። ደም እንደጅረት ወረደ። ያልታሰበ ነገር ደግሞ ሆነ። ጀግናው ታከለ ተማረከ፡ ፡ በጣም አሳዛኝ ሁኔታ ተፈጠረ። እንዴት ታከለን የሚያህል ጀግና ይማረክል? በፍፁም አይታመንም! ግን ተማርኳል! እየተነዳ ሶስቱ ጀኔራሎች ከተቀመጡበት ክፍል ገባ። ጥያቄ ይጠየቃል። ስንሰለት በእጁ ይገባል! ከፋሽስቶች ምን ይጠበቃል? ግልፅ ነው! ይረሽናል ወይም ይሰቀላል!

ቆራጡ አርበኛ ታከለ ምርኮኝነትን በፀጋ ተቀብሎ የሚቀመጥ እንዳልሆነ የማያውቅ ግን አለ እንዴ? በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ታአምር ይሰራል፡ ፡ ከጀኔራሎቹ ፊት ቆሟል! ወደ ቀኝ ተመለከተ፡ ፡ አሁን ደግሞ ወደ ግራ አየት አደረገ። በመቀጠል ወደ ውጭ ተመለከተ! አንድ ነገር አስቧል! በልቡ ተንኮል አርግሟል። ቡም! ቡም! ቡም! ሶስት ቦምቦችን አከታትሎ ለቀቀባቸው። አንዱ ጀኔራል ወዲያው ሞተ! ሁለቱ ቆሰሉ! ታከለ ሲያመልጥ በጀርባው ላይ በጥይት ተመታ! ሆኖም ማምለጡ አልቀረም። ከአርበኞች ጋር ተቀላቀለ። ዕውነት ላይመስል ይችላል። ግን እውነት ነው! ታከለ ተአምር ሰርቷል። አምልጧል።

ቆፍጣናው ጀግና ታከለ ከድል በኋላ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቤትና መሬት ቢሰጡት ለመቀበል ፍቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን በጣም ይንቃቸው ነበርና። እንደ አፄ ቴዎድሮስ ለምን ሽጉጡን አልጠጣም? ወይም ተዋግቶ ለምን ማይጨው ላይ አልተሰዋም? ከማለት አንዱም ተቆጥቦ አያውቅም፡ ፡ የዘውድ ስርዓት አገዛዝ እንዲወገድ ብዙ ታግሏል። ታከለ 19 ጊዜ ታስሯል። ተግሏል። ተፈትቶ ሹመት ተሰጥቶታል። ፀረ-ዘውድ አቋሙን ግን አልለወጠም። ሪፐብሊክ ኢትዮጵያን እንደ ተመኘ ኖረ። ታማኝ አጋር ግን አላገኘም። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ለመግደል ቆረጠ። በሰበታ መንገድ ፈንጂ ቀበረ። ማፈንጃውን ደግሞ ከመኖሪያ ቤቱ ጋር አያይዞታል። ነገር ግን ጠቋሚዎች ለቤተ መንግስት መረጃ ሰጡ። ዓላማው ከሸፈ። ሕዳር 7 ቀን 1961 ዓ.ም ታከለ ህይወቱን በገዛ እጁ አጠፋ! ጀግናው ጀግና እንደሆነ ዘለቀ። የአንበሳ ልጅ ውሻ ሳይሆን አለፈ።

ጀኔራልም ገድሏል፤
ኮሎኔልም ገድሏል፤
ቲንትንም ገድሏል እያስመሰከረ፤
ሬሣ እንደ መንጋ ሔደ እያስቆረጠ፤
ሙንጣዝ-ቡልቅባሽ ገድሏ እያስመሰከረ፤
አንበሳው ታከለ ራሱን ሲገድል ማነው የነበረ?

አፄ ቴዎድሮሳዊ ሥልጣኔና ... ከገፅ 3 የዞረ

ቴዎድሮስ መከራ ቀረብን የምንለውም ይኸው አዲሱን በነባሩ ስልጣኔ ላይ የመገንባት ፍላጐት ነው።

የአለቃ ዘነብ መጽሐፍ ከርእሱ ጀምሮ ሁለቱን ስልጣኔ አቻችሎ የማስኬድ ዋነኛ መንፈስ የሚወክል ነው። ‹‹መጽሐፈ ጨዋታ ስጋዊ ወመንፈሳዊ›› በማለት በዘመኑ እጅግ ይንኳሰስ የነበረውን ምድራዊ ጉዳይ ከሰማያዊው ሕይወት ጋር በእኩያነት አቅርበዋል። የአለቃ ዘነብ ሥጋዊ-ጨዋታ በአራት ንዑስ ክፍሎች ቀርቧል። ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሳይንሳዊ ጉዳዮችን በጭብጥነት ያስተናግዳል። በግልፅ እንደሚታየው የጽሑፉ አላማ የአፄ ቴዎድሮስ አላማ ነው። የግዛት አንድነት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የመልካም አስተዳደር ግብ። አፄው ባዕዳዊ ዕውቀቶችን አንዕሮ አንጥረው በሚመልሱና በማይዘልቃቸው ካህናት ላይ ያላቸውን ቁጣ እና ተግሳፅ አለቃ ዘነብ አለገዙ በመጽሐፉ ውስጥ አካትቶታል።

‹‹ጣዝማ እጅግ ብልህ ናት። መሬት ቀድዳ ገብታ እንደዚያ ያለ መድኃኒት የሚሆን ማር ትሰራለች፡ ፡ ምነው እናንተ ሰዎች ሆይ ከፈጣሪ ወይም ከሰው ብልሃትን አትፈልጉምን››

‹‹እናንተ ሰነፎች ድንቁርናን ከማይመለስበት ሽጡት፤ የሰነበተ እንደሆን ይገድላችኋልና››

‹‹መጋዝ ቢከረክር ምሣር ይፈልጣል። ምነው እናንተ ሰዎች እንዳቅም እንዳቅማችሁ ብልሃት አትፈልጉምን።››

አለቃ ዘነብ ለምርምር በሚቀሰቅስ ደወል ወካይ ተግሳፅ ብቻ አልተቆጠበም። ለምርምር የሚያነሳሱ ጥቁምታዎችን አለዝቦ ያቀርባል።

‹‹ሴትን ወንድ አንድ ጊዜ ይደርስባታል፤ መንታ ትወልዳለች፤ እህልም አንዴት ፍሬ ተዘርታ ብዙ ታፈራለች፤ ይህ ሁሉ ከቶ እንዴት ነው።››

‹‹እንስሶች ሁሉ የሚበሉት አንድ ሣር ነው፤ ምነው ፋንድያቸው ተለወጠ››

‹‹ከዋክብትስ መሞቅ የለ ሁልጊዜ መቀዝቀዝ ምንድነው። ስማይ የለም ይሆን ተሰብስበው ፀሐይን የማይዘርፉት።››

በግልፅ እንደምንመለከተው የአለቃ ዘነብ ግብ የአገር ውስጥ ሳይንሳዊ እሳቤዎችን በአገር ልጅ ውጥንጥኖሽ ማጉልበት ነው። ይህም ብቻ ሳይሆን ከአገር ውጭ እየተከናወኑ ያሉትን የቴክኖሎጂ ውጤቶች በድፍኑ ለአገር ውስጥ ምርምር ማነቃቂያ ማድረግም ነው። ለምሳሌ ‹‹በቀስታና በገዘግታ የተበጀ መዘውር ኋላ ጉልበት ይሆናል›› ይለናል። ሌሎችም አሉት።

‹‹ብልሃተኞች ሰዎች እሳትንና ነፍስን ውሃንም በመዘወር ይዘው ሲያስሯቸው ይኖራሉ፤ ደምወዛቸውን እንኳ አይሰጧቸውም፤ አይኩነኑ ይሆን››

‹‹ነፍስስ እኛን ለመግደል ነው የታዘዘ። አሁን ግንብ ሰርተን መውጫ መተንፈሻ ባሳጣነው›› (የነፋስ ቴክኖሎጂ Windmills)

‹‹(እሳት) ውሃማ ባይኖርበት ይቻላልን። እርሱን እንኳ መክራ እየሰጠ ሲያነደው፤ ሲያነፍረው፤ ሲያጨሰው፤ መርከብና ሰረገላ ሲያስጐትተው፤ ባቡር ሲያስነዳው፤ ሲያስወቅጠው፤ ሲያስፈጨው ይኖራል›› (የእንፋሎት ሞተር-Steam engine)

አለቃ ዘነብን ያበጀው የአጼ ቴዎድሮስ ምኞት ነው። ምኞታቸው የቆሰቆሰው፤ ቆስቁሶ ያነደደው የእውቀት ፋና ነው። ግቡ ሳይቀር የአፄው ግብ ነው፡ ፡ ቁጭቱም የአፄው ነው። አለቃ ዘነብ መጪውን ጊዜና የወገኖቹን ዕጣ የሚመለከተው በነባሩ ስልጣኔ ድልድል ላይ ሆኖ ነው። ታላቅነት ሳይኮነ፤ ኩራት ሳይፈራርስ፤ ታሪክ ሳይደመሰስ፤ ማንነት ሳይጣስ... ስልጣኔን መሻት ከሁሉም በላይ ‹‹ኢትዮጵያዊ››ነትን በአባቱ ተክቶ እስካሁን ይጠራበታል አለቃ ዘነብ ኢትዮጵያዊ። ይሄ እንኳን ምን ያስተምረናል? ከየትኛው ስህተት ይመልሰናል? እንዴት ያለውን ሐፍረት ይገላልጥብናል?...



ዳግማዊት ጃፓን፣ ዳግማዊ ቴዎድሮስ



ደራሲና ገጣሚ በእውቀቱ ስዩም

አለማየሁ ገላጋይ ‹‹የሁለት ስልጡን ህዝቦች ወግ›› የተባለች ኩርማን መጣጥፍ ባለፈው ሳምንት ፍትህ ላይ አውጥቶ አነበብሁ፡ ፡ በመጣጥፏ ውስጥ ኢትዮጵያንና ጃፓንን ባንድ የዘመን ምዕራፍ ላይ ያወዳድራል፡፡ ዳግማዊ ቴዎድሮስን ሙትሱሂቶ ከተባለው የጃፓን መሪ ጋር ያነፃፅራል፡፡ በመጨረሻ በጃፓን አምሳል ሳንሰለጥን መቅረታችን አስቆጭቶት ሁኔታችን ‹‹..ነባሩን ኢትዮጵያዊ ስልጣን ጥሎ ቻይናዊ እድገትን አንጠልጥሎ ሆኗል›› በማለት ወጉን ይዘጋል፡፡

የኔ ፅሁፍ አላማ የዓለማየሁን ሐተታ መጠራጠር ነው፡፡ ብዙዎቻችን እንደሰማነው ፈር ቀዳጅ ሊቃውንት ተብለው የሚታወቁት እነ ገብረ ህይወት ባይከዳኝ፣ ገብረ እግዚአብሔር ኪሳማርያም፣ ተክለ ሐዋርያት ተክለማርያም፣ በኋላም ከበደ ሚካኤል ኢትዮጵያን በጃፓን መንገድ ለመግፋት ሞክረው ነበር፡፡ የዛሬ ልጅ መጠየቅ ያለበት ጥያቄ ‹‹ሙከራቸው ለምን አልተሳካም?›› የሚል መሆን አለበት፡፡ ምናልባት ጃፓንን እንደ አርአያ (ሞዴል) ማጨት በራሱ ስሕተት ሳይሆን ይቀራል?

በቀደምቶቻችን መፍረድ አይቻልም፡፡ ጃፓን ከትቢያ ተነስታ ያስመዘገበችው እመርታ በጣም አስደናቂ በመሆኑ ሊቃውንቶቻችንን ቢያማልል አይገርምም፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ላለ-ከመንገድ ላይ ምኝታ አርፍዶ የተነሣ አገር ስልጣኔን ሀ ብሎ ከመጀመር ይልቅ ተጠናቆ የተገኘውን መኮረጅ አዋጭ ነበር፡፡

ኢትዮጵያን በጃፓን አምሳል ለማሰልጠን ያለሙ ሊቃውንት ሁለቱ አገሮች ተመሳሳይ ጠባይ አላቸው ብለው የሚያምኑ ነበሩ፡፡ ይህንን እምነት አለማየሁ ይጋራዋል፡፡ የዛሬ ሳምንት ከባፈው፣ ልጥቀስ፡፡

> *‹‹ኢትዮጵያና ጃፓን በስልጣኔ ረገድም መንትያ ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡ የሁለቱም ነባር ስልጣኔ ካውሮፓ ስልጣኔ የተለየና መንፈሳዊነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ Theocentric ይሉታል፡ ፡ እንደ አውሮፓ ስልጣኔ በቁስ ላይ የተመሰረተ የሰውን ልጅ ማዕከል ያደገረ Anthrocentric አይደለም››*

በበኩሌ ከዚህ ሐተታ ጋር መስማማት ያስቸግረኛል፡፡ የጃፓኖች ገናና ሐሳቦች ቡዲዝምና ኮንፊሽየሳዊነት መንፈሳዊነት ባያጡም እግዚአብሔርን ማዕከል ያደረገ Theocentric በሚለው ድንኳን ውስጥ አይቀመጡም፡፡ ጃፓኖች ብዙ እሴቶችን ከኮንፊሽየስ ስለወሰዱ ኮንፊሺየሳዊነትም በምድራዊነት ላይ አጥብቆ ስለሚያተኩር ስልጣኔያቸው በቁስ ላይ አልተመሰረተም የሚለው አያሳምንም፡፡

አለማየሁ ያውሮፓ ስልጣኔን ከኢትዮጵያ ስልጣኔ ጋር የሰሜንና የደቡብ ያክል የሚያቃርነው ዕንል ገብረዮሐንስ ያቀረቡትን ሐሳብ ያለ ሂስ ስልተቀበለው ነው፡፡ እንደኔ እንደኔ የኢትዮጵያ ነባር ባህል ስለተፈጥሮ ባጠቃላይ ስለሰው ልጅ በነጠላ ባለው አሉታዊ አስተያየት እንዲሁም ለግለሰባዊነት በሚሰጠው የተጋነነ ቦታ ከሩቅ ምስራቅ ይልቅ ወደ አውሮፓ ጠጋ ይላል፡፡ የሚለየን ነገር ቢኖር አብረን ሄደን ሄደን፣ ብርሃነ ሕሊና (ኢንላይትመንት) የተባለው ያመለካከት ፈርማታ ላይ ሳንደርስ መውረዳችን ይመስለኛል፡፡

በጥንታዊት ኢትዮጵያና በጥንታዊት ጃፓን መካከል ከነበሩት ልዩነቶች አንዱ ስለለውጥ የነበራቸው አስተያየት ነው፡፡ ቀዳሚውን ማክበር አዲሱን መጠራጠር የኢትዮጵያውያን ጠባይ ነበር፡፡ ካዲሱ ብልሃት አሮጌውን ግራ መጋባት መምረጥ፣ ከማያውቁት መልአክ፣ የሚያውቁትን ሰይጣን የሙጥኝ ማለት ብሒራዊ መለዮ ነበር፡ ፡ የዚህ ምክንያት ግልፅ ነው፡፡ በአገራችን ታሪክ በሰላምና በሲሳይ የተደመደመ ለውጥ ብዙ አልተመዘገበም፡፡ እንግዳ ሆኖ ገብቶ ባላንጣ ሆኖ የማያድር ባእድ ብዙ አልታየም፡፡ ስለዚህ ቀስ በቀስ ለውጥን ከጥፋት እንግዳን ከጠላት ጋር የሚያቆራኝ ብሄራዊ አእምሮ ሳይፈጠር አልቀረም፡፡

ባገራችን የመኪና ወፍጮ ሲገባ እናቶቻችን ጋኔን ይፈጭበታል በማለት በድንጋይ ወፍጮአቸው ላይ ረጉ፡፡ ይህንን የተመለከቱ ተራማጅ ነን ባዮች በእናቶቻችን ‹‹አላዋቂነት›› ሲሳለቁ ተመስጌን ገብሬ የተባለ ፀሐፊ ስላቁን ከንቱ ለማድረግ ተነሳ፡፡ እንደ ተመስጌን እይታ ከሆነ፣ በጊዜው የመኪና ወፍጮ ባለቤት የሆኑት ፈረንጆች የባላገሮችን ዱቄት ከቋት ላይ ይሰርቁ ነበር፡፡ ባላገሮች ይህንን ቢያውቁም ፈረንጆችን ሌባ ብሎ ከማሳቀቅ በጋኔን ላይ ማሳበብ ጥሩ የማህበራዊ ዘዴ ሆኖ አገኙት፡፡ ስለዚህ እናቶቻችንን በማህበራዊ ህይወት ፈሊጣቸው ልናደንቃቸው እንጂ ባልገባን ነገር ልንሳለቅባቸው አይገባም ባይ ነው፡፡ ተመስጌንን ቃል በቃል አልጠቀስኩትም፡፡ ግን ሐሳቡ ከዚህ እንደማይወጣ ርግጠኛ ነኝ፡፡

እንግዲህ አስቡት፡፡ የመኪና ወፍጮ ድካምን ከማቃለል ይልቅ የዱቄትን መጠን በማቅለል ተዋውቋል ማለት ነው፡፡ የለውጥ መሳሪያ ከጉድለት ጋር ሲገጣጠም ሰዎች ለውጥን በበጎ ሊያዩት እንዴት ይችላሉ?

ጥንታዊ ጃፓን ግን ለውጥን የሚያስጠላ ክፉ እድል የገጠማት አይመስልም፡ ፡ ባርትራንድ ረስል የተባለ ፈላስፋ እንደጠቀሰው ጃፓኖች ቡዲዝምን ከጉረቤት አገር ተውሰው በብሔራዊ ህይማኖት ከማድረጋቸው በፊት በጥቂት መሳፍንት ላይ ሞከሩት፡፡

አዳዲሶቹ የቡዲስት ተከታዮች የባላገሮች እምነት ከሆነው ሺንቶይዝም ተከታዮች በብልጥግና ከበለጡ ቡዲዝምን እናስገባዋለን ነበር እቅዳቸው፡፡ የቤተ መከራው ውጤት እንደሚያሳየው በተውሶ የመጣው እምነት ካገር ቤቱ እምነት የተሻለ ብልጥግና አፈራ፡፡ ስለዚህ ቡዲዝም፣ ቤት ለእንግዳ ተባለ፡፡ ሼንቶይዝምም በእንግዳው መምጣት ሳይገፋ ቀጠለ፡፡ እንግዲህ ለጃፓኖች

1. አንድ ያስተሳሰብ መስመር የሚለካው በጠቃሚነቱ እንጂ በአገር በቀልነቱ ወይም በማይረጋገጥ እውነቱ አይደለም፡፡
2. አዲሱ የነባሩ ጠላት አይደለም፡ ፡ ‹‹የጉመን ምንችት ውጣ የገንፎ ምንችት ግባ›› የሚል የለውጥ መዝሙር አይሰራም፡፡

ይህን ይህን ስናይ ኢትዮጵያውያን እና ጃፓናውያን ‹‹መንትያ›› የሚያሰኝ ያመለካከት መስመር ወይም የስነ ልቦና ዘይቤ እንዳልነበራቸው እንረዳለን፡፡ የጃፓን ባህላዊ አመለካከቶቻቸው ወደ ምዕራባውያን ስልጣኔ በፍጥነት የሚያደርሱ መንኮራኩሮች ነበሩ፡፡ ስለኢትዮጵያ ተመሳሳይ አስተያየት መስጠት አይቻልም፡፡

ፋናወጊዎቻችን ኢትዮጵያን ዳግማዊት ጃፓን ለማድረግ ያደረጉት ያልተሳካ ጥረት የተደመደመው የጃፓንን ኋላቀር ሕገ-መንግስት በመገልበጥ ነው፡፡ ጃፓኖች የቁሳዊ እድገታቸውን የሚመጣጠን ያስተዳደር ስርዓት አልነበራቸውም፡ ፡ በሌሎች አገሮች ዴሞክራሲ በሰፈነበት ወቅት ኢትዮጵያ ታሣቹናትን የሚያጋንነውን ጥንታዊ የጃፓን ህገ መንግስት መገልበጧ ነባትን አስከፍሏታል፡፡

ስለዳግማዊ ቴዎድሮስ

> *‹‹አፄ ቴዎድሮስ›› ይላል ዓለማየሁ ‹‹አፄ ቴዎድሮስ አውሮፓዊ ስልጣኔ እንዲገባ ከመፈለጋቸው ጐን ለጐን ነባሩ ስልጣኔያቸን እንዳይጠፋ ይጣጣሩ ነበር፡፡ እውነት ትክክለኛነት ፍርድ የነባሩ ስልጣኔ አውዶች እንደሆኑ ተገንዝበው በአርአያነት ያከናውኗቸው ነበር፡፡ እውነትን የሚያጠፋ ትክክለኛነት የሚበርዙና ፍርድን የሚያዛቡ ካጋጠማቸው መቀጣጫ ለማድረግ ወደ ኋላ አይሉም ነበር››*

በኔ አስተያየት፣ በዘመነ መሳፍንት የነበሩ አብዛኛዎቹ ገገርዎች ያውሮፓ ስልጣኔን ማስግባት ይፈልጉ ስለነበር ዳግማዊ ቴዎድሮስ በዚህ በኩል ልዩ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ አለማየሁ አብዝቶ የተሳሳተ የመሰለኝ ግን ቴዎድሮስን የሞራል ስልጣኔ ምሳሌ ሊያደርጋቸው ሲሞክር ነው፡፡ የዳግማዊ ቴዎድሮስ ወኔያምነት አልበገር ባይነት አንድ ነገር ነው፡፡ ስነምግባራቸው ደሞ ሌላ ነገር ነው፡፡

ይልቁንም ‹‹ነባር ስልጣኔያችን እንዳይጠፋ ይጣሩ ነበር›› የተባለው በማስረጃ እስካልተደገፈ ድረስ አያሳምንም፡፡ ለኔ ተቃራኒው የበለጠ እውነት ነው፡፡ ለምሳሌ ውስንም ቢሆን ሀሳብን የመግለፅ ስልጡን ባህል ካጤ ቴዎድሮስ በፊት ነበር፡፡ በቅኔ ቤት አሠረ ንጉስ የሚል መጠሪያ ነበረው፡፡ በዚህ የቅኔ መንገድ ነገስታቱን መውቀስ የእርምት ሐሳብ መጠቆም የተፈቀደ ነበር፡፡ ለምሳሌ በአድያም ሠገድ ኢያሱ ዙፋን ፊት የቀረበ ቅኔ እንዲህ ይላል፡፡

ድምፀ ቃለ ሐሜት ተሰምዓ ኢያሱ በዘመንከ ሠናይ
ከመ ሰማዕነ ባሕቱ እንዘ ይብለከ ነዳይ
ፍትሕከ ይብራህ ከመ ፀሐይ
ሚመት ኩሉ ዘታሕተ ሰማይ
እስመ ኮነ ለዘቦ ንዋይ
ኢያሱ በመልካም ዘመንህ የሐሜት ቃል ተሰማ
ድሃ እንዲህ ሲልህ ሰማን
ፍርድህ እንደ ፀሐይ ይብራልን
ከፀሐይ በታች ያለው ሹመት ሁሉ ገንዘብ
ላለው ብቻ ሆኗልና፡፡

ባለቅኔው የንጉሡ አድልኦ በመዘርዘር ወቀሳውን አቅርቧል፡፡ ወቀሣውን ካቀረበ በኋላ ወህኒ አልወረደም

ከባለቅኔዎች ያልተናነሰ የነባ አመለካከት ፋና ወጊዎች አዝማሪዎች ነበሩ፡ ፡ ዳግማዊ ቴዎድሮስ ግን አዝማሪ ቀጥቅጠው በመግደል የሚካኤል ስዑልን ፊለግ ተከትለው የነባ ሐሳብን ባሕል ባጭር አስቀሩት፡፡ በጊዜው አዝማሪ መግደል በዛሬ ዘበን የተቃዋሚ ጋዜጠኛ ከመግደል ጋር መሣ ነው፡፡ ከዳግማዊ ቴዎድሮስ ፊት ቅሬታ መግለፅ ምን አይነት ቅጣት እንደሚያስከትል ለማስረዳት የሚከተለውን ገጠመኝ ካለቃ ዘነብ እጠቅሳለሁ፡፡

> *‹‹..አግታ በደረሱ ጊዜ አንድ ሴት ከሸፍቶች ምሽት ተያዘች፡፡ ንጉሥ ቴዎድሮስም ግፈኛት ባሉ ጊዜ ደንግጣ ደም ፈሠሣት፡፡ ንጉሱም አልብሳት አሉ፡ ፡ ሴቲቱም እንዲህ አለች፡፡ የሞትሁኝ ቀድሞ ባለብስ ምን እዳም ባለቺ ጊዜ ንጉሱም በነፍጥ በላት አሉ፡፡ በተመታችም ጊዜ ሞተች፡፡ የባሩድ እሣት በነካት ጊዜ ሁለት ቀን እንደ ሟኝ ነደደች››*

ያጤ ቴዎድሮስን ግፍ በሰፊው በመዘንብ የአርብ አንባቢን ድብርት በድብርት የማድረግ አላማ የለኝም፡፡ አለማየሁ ንጉሱን የሞራል ስልጣኔ አርአያ ሊያደርግልን የሞከረውን ለማስተባበያ የጠቀስኩት ይበቃል፡፡ እውነት ለመናገር አጤ ቴዎድሮስ በዘመናቸው ከነበሩ ወደረኞቻቸው ጋር ሲመዛዘኑ በሞራል እጅግ ኋላ ቀር ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ስሙ ያልታወቀ ያጤ ቴዎድሮስ የዜና መዋዕል ፀሐፊ አገው ንጉሤ ስለተባለው የንጉሱ ተቃዋሚ የፃፈውን እንመልከት፡፡

> *‹‹...(አገው ንጉሤ) ጭራሽ ሩሀሩህ ናቸው ይላሉ፡፡ ይቆረጥ በቃ የተፈረደበት እንደሆነ አያ እግርና እጅ በውሃ አይበቅልም ገርፈህ ስደደው ይሉ ነበር ይላሉ፡፡ ይሙት በቃ ቢፈረድበትም ገንዘብ ይከፍሉ ነበር ይላሉ፡፡››*

በዚህ ብርቅ አንቀጽ ውስጥ መስፍኑ፣ የሞት ፍርድን በደም ካሣ ለመተካት እጅና እግርን ለመቁረጥ የሚፈፀምን ቅጣት ደግሞ ጨርሶ ለማስቀረት መጣሩን እመለከታለን፡ ፡ እጅና እግርን መቁረጥ ዳግማዊ ቴዎድሮስ እንደ ሽመና የሚራቀቁበት ቅጣት ነበር፡፡ ለነገሩ ይህ አይነቱ ጭካኔ የፍትሐ ነገሥት ድጋፍም አያጣም፡፡ በኔ ግምት ያገው ንጉሤ ትልቅነት ገናናውን ልማድና ፍትሃነገስቱን ቸል ብሎ የገባ ልቦናውን ለማድመጥ መድፈሩ ነው፡፡ ልቦናው ‹‹...እግርና እጅ በውሃ አይበቅልም›› የምትል፣ ብትቀጥንም ጠጅ የሆነች፣ እንደ ምሥጢረ ሥጋዌ ያልተወሳሰበች ለባላገሩ በቀላሉ የምትገባ የሞራል ፍልስፍና አቀብሎታል፡፡ ይህ እንግዲህ የብርሃነ ሕሊና ውጤት ነው፡፡ ብርሐነ ሕሊና ማለት ያለ ደጋፊ ራስን ችሎ ማወቅ ማለት ነው ብሏል አማኑኤል ካንት፡፡

ያገው ንጉሤ የሞራል ሐሳብ ከዳግማዊ ቴዎድሮስ ዘመን ኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን፣ ከዛሬይቱ ኢራንና ሳኡዲ አረቢያ ጋር ሲነፃፀር እጅግ የቀደመ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ፅሁፌን በዚህ ሰውዬ ብሩሕ ሐሳብ በመደምደሜ ራሴን እንደ እድለኛ ቆጠርሁት፡፡

ስብሐት ገ/እግዚአብሔር ሕይወትና ክህሎት


መጽሐፍ ድጋሚ ታትሞ ገበያ ላይ ዋለ!

‹‹ይህ የዓለማየሁ ገላጋይ መጽሐፍ... የስብሐትን ማንነት (በሰብዓዊነቱ፣ በተፈጥሮው፣ በአመለካከቱ፣ በአስተሳሰቡ) በመውደድና በማክበር ረገድ ጥሩ ትሕትና የተላበሰ መጽሐፍ ነው፡፡ አውነት ለመናገር አንደ ቀድሞ ሥነ-ጽሑፍ መምህርነቱ በአፈ ሙሉ ላድንቅ ብል ዓለማየሁ ገላጋይን ጥሩ አማርኛ አዋቂና ከቃላት አመራረጡ ጀምሮ እስከ ንድፈ ሀሳብ አደራደሩ... የመሰጠኝ መሆኑን መግለፅ እፈልጋለሁ፡፡ . .በምርመራውና አዲስ የአመለካከት ፈር በመቅደዱ ዓለማየሁን አሁንም የደራሲነት ጥረትና ቋንቋውን አደንቅለታለሁ፡፡››

መስፍን ኃ/ማርያም

‹‹ድንቅ ስራ ነው፡፡ ይህ የዓለማየሁ ገላጋይ መጽሐፍ የሥነ-ጽሑፍና ሃያሲያንን ትኩረት እንደሚስብ አያጠራጥርም፡፡ ጋዜጠኛ ዓለማየሁ ለብዙ መሰረታዊ ሂደቶች የሚሆን ጥናት አቅርቧል ማለት እችላለሁ፡፡››

አዮብ ካሣ



‹‹በዚህ በዓለማየሁ ገላጋይ መጽሐፍ ላይ....መጠነ ሰፊ ውይይትና ክርክር የተደረገበት አጋጣሚ ተከስቷል፡፡ ዓለማየሁ ገላጋይ በዚህ መጽሐፍ... ያልተደፈሩ ርዕሶችን በማንሳት ችሎታው ያለውን የተለየ ነገር ከመግለፁም በላይ... ስለስብሐት ህይወትም ሆነ ስለሥራዎቹ በርካታ አዳዲስ ነገሮች ነግሮናል፡፡ በሚያምር የቋንቋ አገላለፅ ስለስብሐት የተለየ ህይወትና ክህሎት ከማናውቀው አቅጣጫ ተነስቶ በተጋፋጭነት አቋም ይተርካል፡፡ ተወደደም ተጠላም ለደረሰባቸው አዳዲስ ድምዳሜዎች ምክንያቱን አቅርቧል፡፡ በዚህ መጽሐፍ የተነሱትን ጉዳዮች ወደ ጉን በመግፋት የምናደንቃቸው ታላላቅ ሰዎች ሲነኩ ብቻ ‹‹ዘራፍ!›› ማለት ከታሪክ ተጠያቂነት አያስተርፍም፡፡››

ሰለሞን ጉሹ

ይህን በታዋቂ ሰዎች ዘንድ እንዲህ ምስክርነት የተሰጠለት
አነጋጋሪና ድንቅ መጽሐፍ በአነስተኛ ቅጂዎች የታተመ ስለሆነ ሳያመልጥዎ
ዛሬውኑ ፈጥነው የግልዎ ያድርጉት በሁሉም መጽሐፍት መደብሮች ያገኙታል፡፡
ዋና አከፋፋይ አምባሳደር መጽሐፍት መደብር ስ.ቁ. 0911 67 64 57

አለውክልና ግብር የለም



ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም

ስለግብር ስናገር ወደ አርባ ዓመት ሊሆነኝ ነው፤ ዛሬ ሁሉም ስለግብር ይናገራል፤ እንዲያውም ወሬው ሁሉ ስለግብር፤ ስለቫት እየሆነ ነው፤ ዱሮ እኔ የምጮኸው በገበሬው ላይ ስለተጫነው ግብር ነበር፤ የዛሬው ጩኸት በነጋዴው ላይ ስለተጫነው ግብርና ወደበላተኛው ስለሚተላለፈው ግብር ነው።

በፈረንጆች አንድ የታወቀ አባባል አለ፦ አለውክልና ግብር የለም --ተረት ሳይሆን ከፖለቲካ ፈላስፋዎቻቸው የመነጨ ቁም-ነገር ነው፤ ለአንድ አገር መንግሥት ገንዘብ እንደሚያስፈልገው ሳይታለም የተፈታ ነው፤ የአገርን ዳር-ድንበር ለማስከበር ወታደር ያስፈልጋል፤ የሕዝቡን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ የፖሊስ ኃይል ያስፈልጋል፤ የሕግ አስተዳደሩን የሚያካሂዱ ዳኞችና የሕግ ሰዎች ያስፈልጋሉ፤ አስተዳደሩን በየደረጃው የሚያስኬዱት ብዙ ሰዎች ያስፈልጋሉ፤ ለትምህርት ቤቶች መምህራንና መጻሕፍት፣ ሌሎችም ነገሮች ያስፈልጋሉ፤ ለሀኪም ቤቶች ሀኪሞች፣ እቴዋዎች፣ ሌሎችም ባለሙያዎችና መሣሪያዎች ያስፈልጋሉ፤ ከነዚህ ሁሉ ጋር የውሃ፣ የመብራትና የመንገድ ነገሮች ሁሉ ሰዎች ያስፈልጓቸዋል፤ እነዚህ ሁሉ ሰዎች እንደሌላው ሰው ሁሉ መብላትና መጠጣት ብቻ ሳይሆን የተደላደለ ኑሮ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፤ ይህ ሁሉ ‹‹ያስፈልጋል›› ሳይታለም የተፈታ ነው።

አንድ ያስፈልጋል ያላልሁት በጣም የሚያስፈልግ ነገር አለ፤ ግን የአገዛዞች ሹማምንት ሁሉ ከጉዳይ የማይቆጥሩት የመኖሪያ ቤት ጉዳይ ነው፤ የመኖሪያ ቤት ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን ሹማምንቱ ዱሮም አሁንም ለራሳቸው እያንዳንዳቸው ለአምስት ቤተሰብ የሚበቃ ቤት በመስራታቸው ይረጋገጣል፤ ይሁን እንጂ በዝቅተኛ ኑሮ ላይ ለሚገኘው ሕዝብ በአቅሙ መኖሪያ ቤት ለመገንባት የሞከረ አገዛዝ የለም፤ ደርግ መሬቱን ነፃ በማድረግ ትንሽ ተቃርቦ ነበር፤ እንደሚመስለኝ ዋናው ምክንያት ትንንሽ ቤቶችን በመሥራት ብዙ የሚገሸለጥ አለመኖሩ ነው፤ አንድ ምስክርነት ልስጥ፤ በ1967 ግድም ቀበሌዎች እንደተመሰረቱ በየዋህነት ለሕዝቡ ጥቅም የሚያገለግሉ መስሎኝ የልማት ኮሚቴ የሚባለው ውስጥ ገባሁ፤ በባለሥልጣኖች እንደተለመደው ኮሚቴው የቀበሌው ችግሮች የሚላቸውን በመላ-ምት መዘርዘር ሲጀምር፣ ልክ እንዳልሆነ ተገንዝበን በእኛ ስብሰባ የቀበሌውን ሕዝብ ችግር በቅደም-ተከተል ልናውቀው አንችልም፤ ስለዚህ ራሱ ችግሩን ይናገር በማለት ተወሰነ፤ ሕዝቡን አንደኛ ችግር፣ ሁለተኛ ችግር፣... እያለ እስከአምስተኛ ችግር ድረስ እንዲገልጽ መጠይቅ ሠርተን ሰዎች በየቤቱ እየተዘዋወሩ እንዲሞላ ተደረገ፤ ውጤቱ ማንም የጠበቀው አልነበረም፤ አንደኛ ችግር ቤት፣ ሁለተኛ ችግር ሰገራ ቤት!

ከዚህ ተነስተን በጥሩ ሁኔታ በእንጨትና በጭቃ የሚሰሩ ቤቶች እቅድ አወጣን፤ ወጪውን ሁሉ አሰላን፤ ለነጠላ ሰዎች በአምስት ብር፣ ለባልና ሚስት በሃያ አምስት ብር የሚከራይና በአስር ዓመታት ዋጋውን የሚመልስ አድርገን ለቀበሌው ስናቀርበው የቀበሌው ሱቅ ለሚባለው ገንዘቡን ሲሰጡ ለእኛ ከለከሉ፤ ቀረ! እኔም ከቀበሌ ጋር በየዋህነት የጀመርሁትን ግንኙነት አቋረጥሁ፤ ዛሬም ቢሆን ‹‹የመንግሥት ሌቦች›› ከፈቀዱ በገቢቱኛ ኑሮ ላለው ሕዝብ መጠነኛ ቤት በመጠነኛ ኪራይ ለመሥራት ይቻላል፤ ኮንደሚኒየም የሚባለውን አለማንሣቱ ረስቼ እንዳይመስላችሁ!

ጥያቄዎች የሚነሡት ገንዘቡ እንዴት ይሰብሰብ? እንዴት ይደልደል? የት የትና እንዴት ይከፋፈል? በሚሉትና ሌሎችም ጥያቄዎች ላይ ነው፤ የፈረንጆቹ አለውክልና ግብር የለም የሚለው ቁም-ነገር ሥራ ላይ የሚውለው እዚህ ላይ ነው፤ ማህበረሰቡ ወይም ህዝቡ ችግሩን ያውቃል፤ የችግሩን ቅደም-ተከተል ያውቃል፤ ስለዚህም እንኳ ገንዘብና ጉልበቱንም ቢሆን ለመገበር ዝግጁ ነው፤ ማናቸውም የሹማምንት ውሳኔ ላይ የችግሩ ባለቤት የሆነው ሕዝቡ በእውነት ተወክሎአል ወይ? በስራውስ ላይ እውነተኛ ተሳትፎ ነበረው ወይ? የመንግሥት ሌቦች የፈለጉትን፣ በፈለጉበት ጊዜና በፈለጉበት ቦታ እየሠሩ ደሀውን ከደሀነት እናድንሃለን ቢሉ ደሀው ከቁልቁለቱ መንገድ አይወጣም፤ ደሀው ግብሩን ይከፍላል፤ ከግብር በተገኘው ገንዘብ የሚጠቀመው ግን ሌላው ነው።

የተመረጡ ‹‹ደሀዎች›› በቴሌቪዥን ጨዋታ ቢያሳዩም ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው፤ የቴሌቪዥን ጨዋታው ወደአልጀዚራም መተላለፉ አስደናቂ አይደለም፤ ደሀነትን ለማጥፋት ሊወጣ የሚገባው ገንዘብ ለአንድ እበላ-ባይ ጋዜጠኛ ኑሮ ማዳበሪያ መሆኑ ያሳዝናል።

ሕጋዊ ግብር ሲባል የከፋዩ የገቢ መጠንና የኑሮ ሁኔታ መታየት አለበት፤ ለምሳሌ አንድ ሰው በዓመት አራት መቶ ብር ቢያገኝና የቤተሰቡ ቁጥር አምስት ቢሆን ከዚህ ሰው ላይ ምንም ያህል ገንዘብ በግብር ስም መውሰድ ወደወንጀል ይጠጋል፤ ልብስንና ሌላውን እንርሳና ለምግብ ብቻ ብናስብ ቤተሰቡ በሙሉ የሚያገኘው በቀን አንድ ብር ከአስር ሳንቲም ነው፤ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል እኩል ከተካፈለ በቀን የሃያ ሁለት ሣንቲም ምግብ ያገኛል፤ ይህም ቁርስን ትቶ ለምሳ አስር ሣንቲም፣ ለራት አሥር ሣንቲም ይሆናል ማለት ነው፤ ይህንን ቤተሰብ ግብር ማስከፈል ወንጀል አይሆንም?

ደሀውን ገበሬ አስቡት፤ ምናልባት በኩርማን ሄክታር መሬት ላይ ሶስት ኩንታል ጤፍ ያመርት ይሆናል፤ ለምግብ ሳያስቀር ሶስቱንም ኩንታል እያንዳንዱን በስምንት መቶ ብር ሂሳብ ቢሸጠው ለእያንዳንዱ አባል የሚደርሰው አንድ ብር ከሠላሳ ሣንቲም ነው፤ ማሽላና ዘንጋዳ፣ ወይም በቆሎ የዘራው ያንን ያህል አያገኝም፤ ለጅምላ ሞት የሚያበቃ ችጋር አለመከሰቱ እርዳታ እያሉ ጥገኝነትን የሚያስፋፉ አገሮች በሚሰጡት እርዳታ ነው።

በአለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ ትልቅ እርምጃ (ወደፊት ይሁን ወደኋላ ባይታወቅም) የታየው ከህዝብ ገንዘብ የመሰብሰቢያው ዘዴ ነው፤ አልፎ አልፎ ከሚደረግ የደርግ ‹‹የአናት አገር ጥሪ›› በጣም የረቀቀና ፋታ የማይሰጥ ነው፤ ማንም አያመልጥም፤ በረሀብ እየተዝለፈለፉ ተማሪ ቤት የሚሄዱ ተማሪዎችም መዋጮ እንዲከፍሉ ይገደዳሉ፤ ልዩ ልብስ ገዝተው እንዲለብሱ ይገደዳሉ፤ ሕጋዊው ግብር ጭነቱ በዛ ሲባል ከሕግ ውጭ ያለው መገበሪያ እየተስፋፋ ነው።

ችጋር ወደሞት አፋፍ ላይ የሚያደርስ የደሀነት አዘቅት ነው፤ የሞት አፋፍ ላይ የቆመውን ግብር ማስከፈል ወይም መዋጮ መጠየቅ ደሀነትን ያስፋፋል እንጂ አይቀንሰውም፤ አለውክልና ግብር የለም የሚባለውንም ቁም-ነገር ይጥሳል።

ስለአፄ ቴዎድሮስ የሥልጣኔ አባትነት

ዓለማየሁ ገላጋይ

በዕውቀቱ ስዩም ባለፈው ሳምንት በትህትናም በእውቀትም ‹‹ጨዋ›› የሆነ የአቋም ማጣጥፍ አስነበበን። ‹‹ዳግማዊት ጃፓን፣ ዳግማዊ ቴዎድሮስ›› የተሰኘው ይሄ መጣጥፍ በተሸኮርማሚነት አጠራጣሪ ሐተታ በመደርደር የእኔን ሐተታ ለመጠራጠር ሞክሯል። ‹‹የሁለት ሥልጡን ሕዝቦች ወግ›› በተሰኘ የቀድሞ-ማምንት ፅሁፌ ከእኛ አፄ ቴዎድሮስን፣ ከጃፓን አፄ ሙትስሒቶን፣ ከዘመን 1960 ዓ.ም. አነሳስቼ መቋጫዬን የከሸፈ ስልጣኔ የፈጠረውን ቁጭት አድርጌ ነበር። በዕውቀቱ ስዩም ጃፓን ከኢትዮጵያ፣ አፄ ቴዎድሮስ ከአፄ ሙትስሒቶ መነሻዐራቸው የጉሮሮ ቅርቃር ሆኖ እንዳልተዋጠለት በሚጠቁም መልኩ አንዳንድ ሐሳቦችን ጣል አድርጓል። ሐሳቦቹ ሲጠቃለሉ፦

1. በጥንታዊት ጃፓንና በጥንታዊት ኢትዮጵያ መካከል ተመሳስሎ አለመኖሩ እንደውም መቃረኑ

2. ጥንታዊ ኢትዮጵያውያን ለውጥ ጠል መሆናቸው

3. ጥንታዊ ጃፓናውያን ለውጥ የሚያስጠላ ክፉ እድል ያልገጠማቸው መሆኑ

4. ዳግማዊ ቴዎድሮስ እንዳብዛኞቹ ዘመነ መሳፍንት ገገርዎች የአውሮፓን ስልጣኔ ለማስገባት ከመፈለግ ውጭ የስልጣኔ አባት የሚያሰኝ አዲስ ነገር አለማድረጋቸው

5. በተለይ ዳግማዊ ቴዎድሮስን የሞራል ስልጣኔ-ምሳሌ ማድረግ አብዝቶ ስህተት ላይ መውደቅ መሆኑንና ሌሎችንም ነጥቦች አንስቷል።

ዘርፍ ዘርፉንና ነገር ማቀጣጠያ ጭራሮውን አራግፈን ስናየው የበዕውቀቱ አንኳር ሀሳብ ይሄው ነው። እዚህ ላይ በዕውቀቱ እንደመስታወት ሰባሪ አንዴ በመወርወር ያንከሻከሸው ብዙ እውነት አለና ስንጥርጣሪው ሁሉ (ዋጋ ቢኖረውም) እየለቀመ ና-ተከፈል ማለት ለጊዜም፣ ለጉልበትም፣ ለወረቀትም ፀር ነው። በዕውቀቱ ‹‹በጨዋዎች›› ዕውቀት የእልህ ዘገር የነቀነቀበት የጥንታዊት ጃፓንና የጥንታዊት ኢትዮጵያ አለመመሳሰል ማስረጃዎቹ እውነታን የሚያጣርሱና በሙያም የሚያውቃቸውን እንኳን በይሆነኝ የካዱ ናቸው። ለምሳሌ ይሄንን የማህበረሰብ ሥነልቡና (Social psychology) እውነታ እንዴት እንደጣሰ እንመልከት።

‹‹በጥንታዊት ኢትዮጵያና በጥንታዊት ጃፓን መካከል ከነበሩት ልዩነቶች አንዱ ስለለውጥ የነበራቸው አስተያየት ነው። ቀዳሚውን ማክበር አዲሱን መጠራጠር የኢትዮጵያውያን ጠባይ ነበር። ካዲሱ ብልሃት አሮጌውን ግራ መጋባት መምረጥ ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁትን ሰይጣን የሙጥኝ ማለት ብሔራዊ መለየ ነበር።››

ይሄንን ከእውነታ ጋር የተጣረሰ የማህበረሰብ ማንፀሪያ አንድ ለሥነ-ልቡና እውቀት ‹‹ጨዋ›› የሆነ ሰው በተናገረው ይቅርታ ባደረግንለት ነበር። ነገር ግን የሥነ-ልቡና ትምህርት ምሩቁ በዕውቀቱ ሆነ። በሥነ-ልቡና ትምህርት ጅማሬ ላይ ስለማህበረሰብ ደህንነት በሚያትተው ክፍል ውስጥ ማህበረሰብ በሙሉ አንዱ ካንዱ ሳይለይ ለውጥ-ጠልና አሮጌውን ሙጥኝ ባይ መሆኑ ተገልጧል። ኢትዮጵያ፣ ጃፓን፣ አውሮፓ... የሚል ፍረጃ ደንቅሮ በለውጥ ፈላጊና አል-ፈላጊነት የመመደብ የበዕውቀቱ ፍላጐት ከምን እንደመነጨ ግልፅ አይደለም። ይሁንና ‹‹ቀዳሚውን ማክበር አዲሱን መጠራጠር የኢትዮጵያውያን ጠባይ›› ብቻ ሳይሆን የመላው የሰው ልጅ ባህርይ ነው። በዕውቀቱ ‹‹ጥንታዊ ጃፓን ግን ለውጥን የሚያስጠላ ክፉ እድል የገማት አይመስልም›› በሚል የደረሰበት ድምዳሜ በላይንስ ብቻ ሳይሆን በታሪክም ያልተደገፈ ሀሳብ ወለድ ነው። ለምሳሌ፦

በ1614 ዓ.ም. ነጋሪት የተጐሰመበት የፊውዳላዊት ጃፓን አስቸኳይ አዋጅ በግልፅ ከሚያሣዳቸው ነገሮች ውስጥ የክርስትና እምነት ማራመድ ዋነኛው ነበር። ይሄ እጋዳ እስከ 1889 ዓ.ም ድረስ ፀንቶ ቆይቷል። ከወጪ ሰዎች ጋር የንግድም ሆነ የሐሳብ ግንኙነት ማድረግ ሌላኛው በአዋጁ ከታገዱት ውስጥ ይቀሳል። ይሄን-ይሄን ስንመለከት ጃፓን እንደውም ከአለም ህዝቦች ሁሉ በተለየ ለውጥን በአዋጅ ያገደች፣ ድንበሯን የጠረቀመች ብቸኛዋ አገር ነች። በዕውቁ ጥንታዊ ኢትዮጵያንና ጥንታዊ ጃፓንን ነጣጥሎ ለማሰብ ብቻ ይሄንን እውነታ ገድፎ ፅፏል። ከዚህ ግድፈቱ ተነስቶም ባለሁለት ነጥብ አቋም ይሏል። ቃል በቃል ላስቀምጠው።

1. አንድ የአስተሳሰብ መስመር የሚለካው በጠቃሚነቱ እንጂ በአገር በቀልነቱ ወይም በማይረጋገጥ እውነቱ አይደለም።

2. አዲሱ የነባሩ ጠላት አይደለም። ‹‹የኮመን ምንቸት ውጣ የገንፎ ምንቸት ግባ›› የሚል የለውጥ መዝሙር አይሰራም።

እዚህ ላይ የበዕውቀቱ የአቋም መግለጫ ከምን እንደመነጨ ብቻ ሳይሆን ምን ለማለት እንደፈለገም ግልፅ አይደለም። አንድ አዲስ አስተሳሰብ ሲመጣ የአገር በቀል አስተሳሰቡ የሚጠቅመው የሰው ልጅ በተፈጥሮ ለውጥ-ጠል በመሆኑ ሳይቃረነው እንዲላመደውና እንዲያራምደው ማስቻሉ ላይ ነው። ጥንታዊቷን ጃፓንና አፄዋን ሙትስሒቶን አንስተን ያወዳደስነው ምዕራባዊውን ስልጣኔ በጃፓናዊው ነባር ስልጣኔ ቀስተውና አደጋፊው ያለቅራኔ ፈጣን እድገት ማምጣት በመቻላቸው ነው “Japanesque” ይሰኛል። የበዕውቀቱ የአቋም መግለጫ ነጥብ 1 ግን የሶሻሊስቱ የለውጥ ዘመን የታየውን ስህተት ለመድገም ያቆበቆበ ወይም ከስህተቱ ያልተማረ ነው። ሩሲያዊ፣ ቤትናማዊ፣ አፍጋኒስታናዊ ወይም ቻይናዊ ባዕድ አስተሳሰብን በአገር በቀል አስተሳሰብ ፋንታ የመተካት ፅኑ ፍላጐት።

የበዕውቀቱ አቋም መግለጫ ነጥብ 2 ህብርና እውነታ የሌለው ነው። ‹‹አዲሱ የነባሩ ጠላት አይደለም›› ይላል። ካልሆነ ለምን ለውጥ አስፈለገ? ለውጥ (Change) በባህሪው የቅራኔና የጠላትነት ውጤት መሆኑን በዕውቀቱ ዘንግቶታል ወይም ሆን ብሎ ገድፎታል። አለበለዚያም ለውጥ የሚለውን እሳቤ የያዘው ከእግር ኳስ የተጫዋቾች ለውጥ ነው። እዚያም ተሰዋጪ በሰዋጪ አሰልጣኝ ላይ መነጫነጩ ይቀራል ብላችሁ?

በበዕውቀቱ ስዩም ፅሁፍ ውስጥ የእራስን አሳንሶ የመመልከት አባዜ ጉልቶ ይስተዋላል። ለምሳሌ ዶክተር እንሰ ገብረጽሐንስ ያቀረቡት ምርምር ያለ ሂስ መቀበል ጉዳት እንዳለው ጠቅሶ የበርትራንድ ረስልን ዘበታዊ ንግግር አገላብጦ ሳይመረምር ይውጣል። ጃፓናውያንን ለውጥ ተቀባይ አድርጐ ኢትዮጵያውያንን የአርጌ ግራ መጋባት ቁራኛ ያደርጋል...

በእኔ አመለካከት ጥንታዊዎቹ ጃፓኖችና ጥንታዊዎቹ ኢትዮጵያውያኖች የለውጥ ጠል ባህሪያቸውና ለስልጣኔ የተነሱበት አግባብ ተመሳሳይ ብቻ ሳይሆን አንድ ነው። ለምሳሌ ጃፓኖች አንድ የሚታወቁበት ባህርይ አላቸው። ከእምነት አንፃር መጤውን ሃይማኖት ላለመቀበል የቻሉትን ሁሉ ማድረግ። ካልቻሉና ተፅዕኖ ከበዛባቸው እንዳለ ከመቀበል ይልቅ ከአገር በቀሉ ነባር እምነት ጋር አዋህዶ አንድ ላይ ማስኬድ። ለምሳሌ እስካሁን ድረስ ጃፓን ውስጥ አዳጋች የሆነው የሺንቶንና ከቡዲሒዝም እምነቶች መነጣጠል ነው። “History of Religion” የተሰኘ መጽሐፍ ይሄንን ርዕሰ ጉዳይ አንስቶ እንዲህ ይላል። “Buddhist images and other objects were removed from Shinto temples. But it was not possible to complety separate the two religions because they had merged together so thoroughly.” (የቡድሒዝም ምስሎችንና ሌሎች ንዋየ ቅዱሳን ከሺንቶ ቤተመቅደስ የማስወገድ ተግባር ተከናውኗል። ነገር ግን ሁለቱን እምነቶች መነጣጠል ፈፅሞ የማይቻል ሆኗል። ምክንያቱ ደግሞ በጥብቅ የተዋሃዱ በመሆናቸው ነው።)

ወደኛም አገር ስንመጣ ተመሳሳይ የእምነት ባህርይ እናገኛለን። Reidulf Knut Molvaer የተባለ ተመራማሪ “Tradition and change in Ethiopia” በተሰኘ መፅሐፉ ይሄንኑ የነባርና የአዲስ እምነት መዋሃድ አንድ ምዕራፍ ሰጥቶ ተንትኖታል። “Syncretism in Christianity and paganism” በሚል ርዕስ

ይሄ የጃፓንና የኢትዮጵያ ተመሳስሎ በአንድ አይነት የስልጣኔ ብሒል እንዲሄዱ የሚጠቁም ጭምር ነው። ላለመቀበል የቻሉትን ሁሉ ያደርጋሉ ካልተቻለ የቀረው አማራጭ አዋህዶ መቀጠል ነው። የአውሮፓውን ስልጣኔ ለማስገባት ሲሞክር በእምነቱ በኩል የታየው እውነታ በዚህም ረገድ ተፈፃሚ ሊሆን ይገባው ነበር። የዚህ ሁሉ ማጠቃለያ ደግሞ በዚህ ዘመን የሚታየው ማንነትን አፈራርሶ በመቃብሩ ላይ ቻይናዊ ስልጣኔን የመገንባት ፍጭርጭሮሽ መሰረት እንደሌለው ማስገንዘብ ነው።

በዕውቀቱ ስዩም ሳያውቅ በስህተት፣ እያወቀ በድፍረት ከያዛቸው አቋሞች የከፋው ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር ተያይዞ ደረስኩበት ያለው ድምዳሜ ነው። ቃል በቃል እንዲህ ይላል።

‹‹በእኔ አስተያየት፤ በዘመነ መሳፍንት የነበሩ አብዛኞዎቹ ገገርዎች ያውሮፓ ስልጣኔን ማስገባት ይፈልጉ ስለነበር ዳግማዊ ቴዎድሮስ በዚህ በኩል ልዩ ሊሆኑ አይችሉም።››

ታሪክ በመቅመል አፄ ቴዎድሮስን አሳንሶ የማሳየት ፍላጐት የቅጂ መብቱ የልዑል መኮንን እንዳልካቸው እንጂ የበዕውቀቱ ስዩም አይደለም። ልዑሉ ‹‹ጣይቱ ብጡል›› በሚል በ1958 ዓ.ም. በዛፉት ተውኔት ላይ አፄ ቴዎድሮስን ተኮናኝ ነፍስ አድርገው ስለዋቸዋል። ይሄንን የልዑሉን ድፍረት ባዕዱ Molvaer ሳይቀር ታዝቦ መኮንን እንዳልካቸው በፊትም ሆነ በኋላም ያልተሞከረ የማሳነስ ስራ ነው ብሎታል። እንግዲህ ከልዑሉ ወዲህ ደግሞ ብላቴናው በዕውቀቱ ሳምንት በሞላው ፅሁፉ አፄውን የማሳነስ አቋም ያዘ። በመሰረቱ ታሪክ እያጣቀሱ የማተለቅ ፍላጎትን የመወጣት አዝማሚያ እንዳለ ሁሉ የማሳነስ ጥማት ቢከሰት አስደናቂነት የለውም። እንደውም ቢያንስ-ቢያንስ ሀሳብ እርስ-በርሱ ተሟርዶ የሰላ ግንዛቤ እንዲፈጠር ያደርጋልና ጐጂነት የለውም።

በዕውቀቱ የትኛው የዘመነ-መሣፍንት ገገር በአፄ ቴዎድሮስ መጠንና አይነት ስልጣኔን ለማስገባት እንደፈለገ በግልፅ አልጠቆመም። ስልጣኔን የማስገባት ፍላጐት ጠበንጃና መድፍ በማስመጣት ተተርጉሞለት ከሆነ ታላቅ ስህተት ላይ እንደወደቀ ሊረዳው ይገባል። አፄ ቴዎድሮስ የስልጣኔ በር ከፋች ተደርገው እንዲታሰቡ

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

የፍትህ ዓምድ

በዚህ ዓምድ የአገራችንን ህጎች ፣ ዓለም አቀፍ ህግጋት ፣ በሀገራት መካከል የተደረጉ ስምምነቶችን እንዲሁም ለንፅፅር እና ለማገናዘቢያ ይረዳን ዘንድ ሌሎች ሀገሮችን ህጎች መሰረት በማድረግ ከማንኛውም አይነት የፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መልኩ ትንታኔ ይሰጣል፡፡

ፅንስን ማቋረጥ (ውርጃ) ሕጋዊ ወይስ?

ከሚፈጥረው የማህበራዊ ህይወት መስተጋብር ቀውስ፣ በትውልድ ቀጣይነት ላይ ካለው አሉታዊ ተፅዕኖ፣ በጉዳዩ ዙሪያ የሚነሳቸው ግለሰቦች ውስን አለመሆን እንዲሁም ከሚያስከትለው የሞራል ዝቅጠት አንፃር ፅንስን ማስወረድ (ወይም በተለምዶ አጠራር ውርጃ) በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ መንግስታትን፣ የፓርቲ መሪዎችን፣ የሃይማኖት መሪዎችን፣ የጦሳ አለቆችን የሃሳብ ልዩነት እንዲፈጥሩና በቃላት እንዲቆራቆዙ ምክንያት ሆኗል። መንግስታት ፅንስን ማስወገድ በመፍቀድ እና በመከልከል ዙሪያ ከተቀናቃኞቻቸው ከፍተኛ ሙግት ገጥሟቸዋል እየገጠማቸውም ነው። የሃይማኖት መሪዎች የጉዳዩን አሳሳቢነት ለተከታዮቻቸው አሳስበዋል ውርጃን መፈፀም በሃይማኖቶቻቸው አስተምህሮት መሰረት ክልክል እንደሆነ በአደባባይ ተናግረዋል። የጉዳዩ አሳሳቢነት በተለያዩ ተያያዥ ምክንያቶችና የግለሰቦች መብት ከፍተኛ ቦታ እየተሰጠው ሲመጣ አብሮ በመነሳት ለሙግት እና ለውዝግብ እየተመቸ ቢሄድም አለመግባባቱ የጀመረው ከጥቂት ዓመታት በፊት እንዳልሆነ አንዳንድ መረጃዎች ያሳያሉ። እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር እስከ 1960ዎቹ ድረስ በአሜሪካ ፅንስን መስወረድ ህገወጥ የነበረ ሲሆን ክስልሳዎቹ ቡኋላ ግን በተለያዩ ወገኖች አማካኝነት ክርክር ማስነሳት ጀመረ። በ1970ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ የአሜሪካን ጠቅላይ ፍርድ ቤት በውርጃ ህጋዊነት ዙሪያ የሚያሻማ ፍርድ ሰጠ። ፍርድ ቤቱ በ1973 በያዘው Roe Vs wade ጉዳይ በአሜሪካ በየትኛውም ክልል የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ፅንስን ስለማስወረድ ያደረጉትን ክልከላ እንዲያነሱ ድርጊቱም ህገ-መንግስታዊ እንዳልነበረ በመግለፅ ውሳኔ ሰጥቷል። በየትኛውም ዓለም በውርጃ ላይ ያለው ውዝግብ በግለሰቦች መብት እና በመንግስታት ፍላጐት መካከል ያለው አለመግባባት እንደሆነ በዚሁ ዙሪያ ጥናት ያደረጉ ምሁራንን ያሰማማል። በአንድ በኩል የግለሰብ መብት በሌላ በኩል ደግሞ የማህበረሰብ መብት /Collective right/ የውዝግቡ መንስኤ እንደሆኑ ይታሰባል። ፅንስ በራሱ ለተፈጥሮ ሰው የሚሰጠው መብት ያልተሰጠው መሆኑ በሌላ ወገን ግለሰቦች በራሳቸው አካላት ላይ የሚፈፅሙት ማናቸውም ነገር በህግ የተከለከለ አለመሆኑ ፅንስን ማስወረድ መፍቀድ እና መከልከልን አስቸጋሪ አድርጐታል።

በሀገራችን ኢትዮጵያ ፅንስን ማስወረድ በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል እንደመጥፎ ተግባር የሚወስድ እና በሀገሪቷ በሚገኙ ብዙ ተከታይ ያላቸው ሃይማኖቶች እንደ ውግዝ የሚቆጠር ተግባር ነው። ምንም እንኳ በፍትሐብሔር ጉዳይ አንድ ፅንስ እስካልተወለደ ድረስ ይህ ነው የሚባል ለተፈጥሮ ሰው የሚሰጥ ሙሉ መብት ባይኖረውም የሀገራችን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ፅንስን ማስወረድ በሕግ ከተፈቀደላቸው ምክንያቶች በስተቀር ክልክል እንደሆነ እና ከዚህ ውጭ ውርጃም የሚፈፅሙ ግለሰቦች ወንጀለኛ እንደሚሆኑ ደንግጓል። የኢፌድሪ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከአንቀፅ 545 እስከ አንቀፅ 552 ውርጃን በተመለከተ ሊያስቀጡ የሚችሉ ሁኔታዎችን ከነ አጠቃላይ መርሁ ደንግጓል። በመርህ መልክ የተቀመጠው አንቀጽ 545 ንዑስ አንቀፅ 1 እንዲህ ይላል፡- በአንቀጽ 551 ከተገለፀው ውጭ በማናቸውም መልኩ በየትኛውም ደረጃ ላይ ያለን ፅንስ አውቆ ማቋረጥ ከዚህ በሚከተሉት አንቀፆች አማካኝነት ያስቀጣል። በዚህ አንቀጽ መርህ መሰረት ፅንስን አውቆ ማቋረጥ (ምክንያቱም ፅንስ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድም ሊወርድ ስለሚችል ነው) ያስቀጣል። ፅንስ በሰው ሰራሽ መንገድ በባህላዊም ይሁን በዘመናዊ መልኩ ሊቋረጥ ይችላል። ከዚህ ሌላ ሳይታሰብ በስራ መብዛት ወይም ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ሊቀጥል የማይችልበትም ሁኔታ አለ። ይሁን እንጂ በሀገራችን ህግ መሰረት አውቆ ፅንስን እንዳይቀጥል ማድረግ በምንም መልኩ የተደረገ ቢሆንም ያስቀጣል። ከዚህ ሌላ አንቀጽ 545 (1) ውስጥ የተቀመጠው መሰረታዊ ጉዳይ የፅንሱ ደረጃ ነው። በዚህ መርህ መሰረት ፅንሱን ለማውረድ የፅንሱ እድሜ ወይንም የእድገት ደረጃን እንደ ማስረጃ ወስዶ መከራከር አይቻልም። በየትኛውም ደረጃ የሚገኝን ፅንስ በህግ ከተፈቀደው አግባብ ውጭ ማቋረጥ ወንጀል ነው። አንዳንድ ሀገራት ፅንስን በማስወረድ ላይ ያላቸውን አለመግባባት ከሁለቱም ወገን ፅንፍ ይዞ ላለማስቀመጥ ጥቂት ወራት የሆናቸውን ፅንሶች ማስወረድ ህገ ወጥነት እንዳልሆነ በህጐቻቸው አካተዋል። ይሁንና ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አልተካተተም። የፅንሱ የእድገት ደረጃ እንደ መከራከሪያ ሊቀርብ አይችልም።

በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሰረት ፅንስን ማቋረጥ የሚፈቅድባቸው ሁኔታዎች በአንቀጽ 551 የተካተቱት ሲሆኑ የቀሩት ግን ህገ ወጥ ተግባራት እንደሆኑ አንቀጽ 545 ደንግጓል። ለመሆኑ ፅንስን ለማቋረጥ በህግ የተፈቀደላቸው ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው? አንቀጽ 551 ፅንስን ለማቋረጥ በህግ የተፈቀዱ ሁኔታዎች ብሎ ይዘረዝራል። አንቀፅ 551 (1)፡- እውቅና ካለው የህክምና ተቋም ሙያው በሚፈቅደው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚደረግ ፅንስ የማቋረጥ እርግዝናው የመጣው በአስገድዶ መድፈር ወይም ከፍላጐት ውጭ በሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት ከሆነ፣ የእርግዝናው መቀጠል እናትየውን ወይንም ፅንሱን አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ፣ ፅንሱ የማይድን የአካል ጉዳት ያለበት ከሆነ እና እናትየው በአካል እና በአእምሮ ብቃት ችግር ኖሮባት ልጅ መውለድ የማትችል ከሆነ በሀኪሞቹ ትእዛዝ መሰረት ፅንሱን ማስወረድ እንደሚቻል ደንግጓል። ከዚህ በተጨማሪ አንቀፅ 551 (2) አደገኛ የሆነ አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ አንቀጽ 75 በሚፈቅደው መሰረት ፅንስን ማቋረጥ ወንጀል እንዳልሆነ ይገልፃል። አንቀጽ 75 ደግሞ ሁኔታውን ለማስቀረት ሌላ አማራጭ ከሌለ ፅንስን ማቋረጥ ወንጀል ሊሆን እንደማይችል ይገልፃል።

ምንም እንኳን ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ፅንስን ማቋረጥ ወይም ማስወገድ ወንጀል ባይሆንም ህጉ ያስቀመጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸው የግድ ነው። ከእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው አስገዳጅ ሁኔታዎች ቢኖሩ እንኳ ፅንሱን የማቋረጥ ስራው መፈፀም ያለበት እውቅና ባለው የህክምና ተቋም መሆን አለበት። በዚህ ውጭ የሚደረግ የፅንስ ማቋረጥ ተቀባይነት ስለማይኖረው ከወንጀለኛነት አያድንም። በአንቀፅ 551 (1) (ሀ) ውስጥ የተጠቀሰው የመጀመሪያ አስገዳጅ ሁኔታ እርግዝናው የተከሰተው በአስገድዶ መድፈር ወይም ከፍላጐት ውጭ በሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት ከሆነ እውቅና ባለው የህክምና ተቋም የሚደረግ ፅንስ ማቋረጥ ህጋዊ ነው። የዚህ ዓይነቱ ውርጃን የሚፈቅድ ህግ በሌሎች ሀገራትም በስራ ላይ ያለ ሲሆን ዋና ዓላማው አስገድዶ መድፈር የተፈፀመባት ግለሰብ ከደረሰባት አደጋ በተጨማሪ አደጋው ይዞት ከሚመጣው የተፈጥሮ፣ የስነ ልቦና እንዲሁም የኢኮኖሚ ችግር ለመታደግ ታስቦ የተቀመጠ ነው። በአስገድዶ መድፈር ምክንያት ያረገዘችው ግለሰብ ከደፈራት ሰው ፅንሱ ሊወስድ የሚችለው ዘረ መል በውስጡ ተፈጥሮአዊ ችግሮች ካሉት በፅንሱ በወደፊት ህይወት ላይ አደጋ ሊፈጥር ስለሚችል እናትየው ያለፍላጐቷ ባጋጠማት ግንኙነት ምክንያት የዚህ አደጋ ገፈት ቀማሽ እንዳትሆን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን ሌሎች ተፈጥሮአዊ ተያያዥ ችግሮችም በወደፊት የልጇ ህይወትና በእርሷ ላይ ችግር ይፈጥራሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ፅንሱን ካልፈለገችው ብታስወርደው እንደወንጀል አይቆጠርባትም። ሌላው ችግር ግለሰቧ ሊደርስባት ከሚችለው የስነ ልቦና ችግር አንፃር ልጅን የመጥላት እና በደፈራት ግለሰብ አይን የማየት ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል ለሚወለደው ልጅ ደህንነት እንዲሁም ለእናትየው የስነ-ልቦና ጤንነት ሲባል ፅንሱን እውቅና ያለው የጤና ተቋም ሄዳ ብታቋርጠው እንደ ወንጀል አይቆጠርም። አስገድዶ በመደፈር የመጣን ፅንስ ለማቋረጥ ህጋዊ ሽፋን የተሰጠበት ሌላው ምክንያት በሚወለደው ልጅ ምክንያት እናትየው ሊገጥማት የሚችሉትን ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ከወዲሁ ለመታደግ ነው። ምንም እንኳ እናት ለልጅዋ ማድረግ የሚገባት ነገሮችን ህግ ቢያስገድድም እናቶችም ይህን የማድረግ የሞራል ግዴታ ቢኖርባቸውም እንደዚህ ዓይነት የህይወት መስመር ውስጥ ለመግባት የእናትየው ፍላጐት አሁን ያላት የኢኮኖሚ አቅም እና ሌሎች ጉዳዮች ሊወስኑት ይችላሉ። ነገር ግን በዳብዳ የሚፈፀሙ አስገዳጅ ምክንያቶች በእናትየውም ሆነ በሚወለደው ህፃን የወደፊት የኑሮ ሁኔታ ላይ ችግር ሊፈጥሩ ስለሚችሉ እናትየው ፅንሱን ለማስወረድ ከፈለገችና በተገቢው ቦታ ሄዳ ከፈፀመችው ህጉ ሽፋን ይሰጣታል። ይቀጥላል።

ቸር እንሰንብት።

የነፃው ፕሬስ ... ከገፅ 2 የዞረ

ፕሬስ ለማፈን መወሰኑን ያሳያል። ይህን ቅጣት መክፈል ያልቻሉ የፕሬሱ አባላት ቅጣታቸው ወደ እስር ይዛወራል። ዶ/ር ቴሬሴ “A test of democracy: Ethiopia’s mass media and freedom of information proclamation” በሚለው ስራቸው እንደሚያወሱት ይህን መሰል የተጋነነ የገንዘብ ቅጣት የፕሬሱን የገንዘብ ምንጭ በማድረቅ ጋዜጦቹን ወደመዘጋት ያቀርባቸዋል። የፕሬሱ የተለምዶ የገንዘብ ምንጭ ማስታወቂያ እና ሽያጭ ቢሆንም ብዙዎቹ ተቋማት ስርዓቱ በመልካም ዓይን በማያያቸው ፕሬሶች ላይ ማስታወቂያ ማውጣትን ከህልውናቸው ጋር በማያያዛቸው ጋዜጦቹ በአንባብያን ላይ ብቻ እንዲመሰረቱ አድርጓቸዋል። ከብዙ ውስጣዊ እና ውጪያዊ ተግዳሮቶች አንፃር የጋዜጦቹ የሽያጭ ቁጥር እጅግ አነስተኛ መሆኑ በዛው ልክ የጋዜጦቹን ገቢ ዝቅ ያለ አድርጐታል።

ገዢው ፓርቲ እነዚህ ጉዳዮች ላይ ያለው አቋም ግልፅ ይመስላል። ጋዜጦች ላይ ማስታወቂያ እንዲወጣ የሚሹ ድርጅቶችን በተመለከተ ‹‹ማስታወቂያ የሚያስነግሩ ተቋሞች በተለይም የመንግስት ድርጅቶች እና ልማታዊ ባለሀብቶች ማስታወቂያቸውን ለስርዓቱ አደጋ በሚሆኑ ተቋሞች ላይ ማውጣቱን እንዲተውት›› ይመክራል። በመጋቢት ወር 1999 ዓ.ም. ‹‹የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ትግል እና አዮታዊ ዴሞክራሲ›› በሚል ርዕስ ፓርቲው ያሳተመው ድርሳን እንደሚያትተው ፕሬሱ የሚቆምበትን የአንባቢዎች ክፍያ እንዴት እየተቀዛቀዘ ሊሄድ እንደሚችል ሲያብራራ ‹‹ዜጎች በሂደት ስርዓቱን ለአደጋ የሚጥል ሚዲያ መጠቀም በራሳቸው ላይ እባብ መጠምጠም መሆኑን ተገንዝበው›› ጋዜጦቹን ከመግዛት እንደሚቆጠቡ ይጠቅሳል። በሀገሪቱ ውስጥ መኖር ያለበት ‹‹አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ሚዲያ›› ነው የሚለው ይህ ዶክመንት የአነዚህ ሁለት ሁነቶች መፈጠር ፓርቲው የሚፈልጋቸው ጋዜጦችን ብቻ በአደባባዩ ላይ እንዲያስቀር ያስችለዋል።

ዶ/ር ቴሬሴ እንደሚሉት በዚህ አነስተኛ ገቢ ላይ የቆሙ የፕሬሱ አባላት ላይ ተደጋጋሚ የገንዘብ ቅጣት መጣል የጋዜጦቹን ህልውና ያከስማል። ፀሐፊው ‹‹የገቢ አቅምን መጭመቅ›› ሲሉ የጠሩት ይህ የገንዘው ፓርቲ ስልት ፖለቲካዊ መነሾ እንዳለው ማሳያ የሚሆነው የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን አልያም አስገድዶ መድፈርን በተመለከተ የተቀመጡት የገንዘብ ቅጣቶች ፕሬሱ ላይ ከተጣሉት እጅግ ያነሱ መሆናቸው ነው። ትዝታ ከበደ የተባሉ ፀሐፊ “Ethiopia: Independent media professionals deplore press law” በሚለው መጣጥፋቸው እንደሚያነሱት ለአስገድዶ መድፈር ወንጀል የተቀመጠው የገንዘብ ቅጣት ከአንድ ሺህ ብር አለመብለጡ ፕሬሱ ላይ ከተቀመጠው ጋር ሲታይ የፕሬሱን ቅጣት አስከፊነት ያጎላዋል።

ከፕሬስ ህጉ በተጨማሪ ገዢው ፓርቲ ፕሬሱን ለማድቀቅ እየተጠቀመበት ነው ተብሎ በብዙ የጋዜጠኞች ተቆርቋሪ ተቋማት የሚከሰስበት ህግ የፀረ-ሽብርተኝነቱ አዋጅ ነው። ይህን ብዙዎች ‹‹አፋኝ›› ሲሉ የሚተቹትን አዋጅ በተመለከተ የሚሰጡ አስተያየቶች ወደ አንድ ጫፍ ያዘነበሉ ናቸው። ዘካሪያስ ሙሉታ የተባሉ ፀሐፊ በጥልቅ ሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚወነጀለው ስርዓት ይህን ህግ የማውጣቱ መነሻ አምባገነናዊ ጉዞው ላይ የሚቆሙ ዜጐችን ለመጨፍለቅ ነው ሲሉ ይሟገታሉ። ፀሐፊው አዋጁ በሽብር ወንጀል ተጠርጥረዋል የሚባሉ ዜጎችን በተመለከተ ለፖሊስ የሰጠው ገደብ አልባ ስልጣን፣ የመንግስት የደህንነት ተቋማት ስልክ፣ ፋክስ፣ ኢንተርኔትና መሰል ነገሮችን ካለዜጎች ፍቃድ የመጥለፍ መብት ማግኘቱ አልፎም የደህንነት ተቋሙ የሚያገኛቸውን መረጃዎች ምንጭ ለፍርድ ቤት እንዲያስረዳ አለመገደዱን በመጥቀስ አዋጁ የመንግስቱን የስራ አስፈፃሚ ክፍል ጡንቻ ለማጎልበት እንደሚጠቅም “Antidemocratic system of governance in Ethiopia under absolute dictatorship of TPLF regime” በሚለው ፅሁፋቸው ይከራከራሉ።

የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁ የፕሬሱን ህልውና ስለመፈታተኑ ከቀደመው ዓመት ወዲህ የተከሰቱት ሁኔታዎች በቂ ማሳያ ይመስላሉ። በዚህ አዋጅ መነሾ ሁለት ጋዜጦች ሲዘጉ፤ ከስደት የተረፉት ጋዜጠኞች ከባድ እስር ገጥሟቸዋል። ይህ አዋጅ በውጭ የሚገኙ ድረ-ገጾችን እና የቴሌቪዥን ጣቢያንም በ‹‹ሽብርተኝነት›› ለመክሰስ ጠቀሜታ ላይ ውሏል። ለገዢው ፓርቲ እነዚህን የዲያስፖራ ሚዲያዎች በዚህ ክስ መክሰስ ሚዲያዎቹ በሀገር ውስጥ የሚኖራቸውን የመረጃ ምንጭነት ለማድረቅ ህጋዊ ሽፋን ይሰጠዋል። የአዋጁ ተራዛሚ ተፅዕኖ አሁን በሀገር ውስጥ ባሉት ጋዜጦችና ጋዜጠኞች ላይ እያሳደረ ያለው ጫና (Chilling effect) ከበድ ያለ ይመስላል። የጋዜጠኞች መብት ተቆርቋሪ ተቋሙ ሲ.ፒ.ጄ “Attacks on the press” በሚል ርዕስ ባወጣው መድብል ላይ ኢትዮጵያን በተመለከተ አስተያየቱን ያሰፈረው የተቋሙ አማካሪ ቶም ሮድስ ‹‹ግራ-የሚገባ››´ሲል የከሰሰው አዋጅ ወደ ፕሬሱ እጁን መዘርጋቱ ከባድ የፖለቲካ ስህተት እንደሆነ ይናገራል። ‹‹ሽብርን የሚያበረታቱ ፅሁፎችን›› በተመለከተ አዋጁ የዘረዘራቸው ጋዜጠኞችን ለመክሰስ እየዋሉ ያሉ አንቀፆች ለፖለቲካዊ ትርጓሜ በሚጋለጡ ሀሳቦች ስለመሞላታቸው ብዙ ተንታኞች ይስማማሉ። በወሳኝ ሀገራዊ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የሚወጡ ዘገባዎች እና ትንታኔዎች ላይ ጥልቅ ገደብ የሚያደርገው ይህ አዋጅ የመጨረሻ ግቡ ማህበረሰቡን ከአንድ ሚዲያ ብቻ በሚገኝ መረጃ መጠርነፍ ይመስላል።

ስለአፄ ቴዎድሮስ ... ከገፅ 3 የዞረ

ያደርጋቸው የቴክኖሎጂ ሽግግርን ጭምር ተልመው በመንቀሳቀሳቸው ነው። ጋፋት የያኔዋ ‹‹የኢንዱስትሪ ዞን›› እንደነበረች ከብዙ ፀሐፍት ማረጋገጥ ይቻላል። የእጅ ሙያ ያላቸውን አውሮፓውያን ጋፋት ላይ በማሰፈር ልዩ-ልዩ መሳሪያዎች እንዲመረቱ ያደርጉ ነበር። ጋሪ፣ ፋስ፣ መዝጊያና ይህን የመሳሰሉትን ስራዎች ቴዎድሮስ መሰልቸት ስለጀመሩ የኢንዱስትሪ ዞኑ ምርቱን ወደ መድፍና አዳፍኔ እንዲያሳድግ መጕተታት ጀመሩ። ለዚህም ገንዘብ፣ እህል፣ ማር፣ ቅቤ የትኛውንም አስፈላጊ ነገር በገፍ ከማቀረባቸው ሌላ ማበረታቻ የብር ጋሻ፣ ወርቅ ቅብ የበቅሎ ማሰሪያ፣ በቅሎና ፈረስ ይሸልሙ ነበር። እንዲህ ያደርግ የነበረ የዘመነ-መሣፍንት አንድ ገዢ ካለ በዕውቀቱ ሊነግረን ይገባል።

አፄ ቴዎድሮስ የቴክኖሎጂ ሽግግሩን ለማስለጥ ከመጣር ባሻገር አራሳቸውም የተግባሩ ተሳታፊ ነበሩ። ዶክተር ሔንሪ ብላንክ ‹‹የእስራት ዘመን አበሻ አገር›› በተሰኘ መጽሐፉ ላይ ‹‹አፄ ቴዎድሮስ ከወደቡ ላይ ተቀምጠው ጥይት እየሰሩ ‹ስራዬን ታያለህን? በዚህ ስራ አላፍርበትም› አሉ›› ይለናል። ከዚህ በተጨማሪ ገፅ 116 ላይ እንዲህ የሚል አስፍሯል፡-

‹‹አፄ ቴዎድሮስ በጣና ባሕር ላይ የሚንሳፈፉ ጀልባዎች ለማሰራት ያላቸው እምነትና ፍላጐት ገና የፀና ስለነበር የሌሎቹን ርዳታ ለማግኘት እንዲረዳቸው ሲሉ ራሳቸው ወርደው መርከብ መስራት ጀመሩ። ሰፊ ወለል ያለውና በከባድ መንኰራኩር የሚንቀሳቀስ ጀልባ ሰሩ። እንዲያውም ፓድል ስቲመር ፈልስፈው ሰርተው ነበር። ዳሩ ግን የሎኮሞቲቭ ክፍሉ ሳይሰራ ቀረ። ጀልባዋ ብዙ ጊዜ ከባህሩ ውስጥ እናያት ነበር። ጀልባዋን የሚያንቀሳቅሰው ሁለቱ መንኰራኩር በጣም ትልቅ ስለነበር ወደ ውሃው ውስጥ ጠልቆ እንዲገባ ለማድረግ በመቶ የሚቆጠር ሰው ያስፈልግ ነበር። በዚሁ ጀልባ ስራ መንፈሳቸው በጣም ተመስጦ ስለነበር ጊዜአቸውን በሙሉ ለዚሁ ተግባር ስላዋሉት ከሰፈፈራቸው አራት ማይልስ እርቆ ከሚገኝ ስፍራ ላይ ኃይለኛ ጠላት ተነስቶ ሳይሰሙ ቆይተዋል።›››

የበዕውቀቱ አፄውን የማሣነስ ድምዳሜው ከተግባራቸው እስከ ሞራል አቋማቸው ድረስ የዘመተ ነበር። እንዲህ ብሏል ‹‹እውነት ለመናገር አጤ ቴዎድሮስ በዘመናቸው ከነበሩ ወደረኞቻቸው ጋር ሲመዛዘኑ በሞራል እጅግ ኋላቀር ነበሩ።›››

በዕውቀቱ ለዚህ ድምዳሜው አስረጅ ያቀረበው የአፄውን ፀሐፊ ትዕዛዝ የአለቃ ዘነብን ምስክርነት ከሆነ እውቅና ባለው የህክምና ተቋም የሚደረግ ፅንስ ማቋረጥ ህጋዊ ነው። የዚህ ዓይነቱ ውርጃን የሚፈቅድ ህግ በሌሎች ሀገራትም በስራ ላይ ያለ ሲሆን ዋና ዓላማው አስገድዶ መድፈር የተፈፀመባት ግለሰብ ከደረሰባት አደጋ በተጨማሪ አደጋው ይዞት ከሚመጣው የተፈጥሮ፣ የስነ ልቦና እንዲሁም የኢኮኖሚ ችግር ለመታደግ ታስቦ የተቀመጠ ነው። በአስገድዶ መድፈር ምክንያት ያረገዘችው ግለሰብ ከደፈራት ሰው ፅንሱ ሊወስድ የሚችለው ዘረ መል በውስጡ ተፈጥሮአዊ ችግሮች ካሉት በፅንሱ በወደፊት ህይወት ላይ አደጋ ሊፈጥር ስለሚችል እናትየው ያለፍላጐቷ ባጋጠማት ግንኙነት ምክንያት የዚህ አደጋ ገፈት ቀማሽ እንዳትሆን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን ሌሎች ተፈጥሮአዊ ተያያዥ ችግሮችም በወደፊት የልጇ ህይወትና በእርሷ ላይ ችግር ይፈጥራሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ፅንሱን ካልፈለገችው ብታስወርደው እንደወንጀል አይቆጠርባትም። ሌላው ችግር ግለሰቧ ሊደርስባት ከሚችለው የስነ ልቦና ችግር አንፃር ልጅን የመጥላት እና በደፈራት ግለሰብ አይን የማየት ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል ለሚወለደው ልጅ ደህንነት እንዲሁም ለእናትየው የስነ-ልቦና ጤንነት ሲባል ፅንሱን እውቅና ያለው የጤና ተቋም ሄዳ ብታቋርጠው እንደ ወንጀል አይቆጠርም። አስገድዶ በመደፈር የመጣን ፅንስ ለማቋረጥ ህጋዊ ሽፋን የተሰጠበት ሌላው ምክንያት በሚወለደው ልጅ ምክንያት እናትየው ሊገጥማት የሚችሉትን ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ከወዲሁ ለመታደግ ነው። ምንም እንኳ እናት ለልጅዋ ማድረግ የሚገባት ነገሮችን ህግ ቢያስገድድም እናቶችም ይህን የማድረግ የሞራል ግዴታ ቢኖርባቸውም እንደዚህ ዓይነት የህይወት መስመር ውስጥ ለመግባት የእናትየው ፍላጐት አሁን ያላት የኢኮኖሚ አቅም እና ሌሎች ጉዳዮች ሊወስኑት ይችላሉ። ነገር ግን በዳብዳ የሚፈፀሙ አስገዳጅ ምክንያቶች በእናትየውም ሆነ በሚወለደው ህፃን የወደፊት የኑሮ ሁኔታ ላይ ችግር ሊፈጥሩ ስለሚችሉ እናትየው ፅንሱን ለማስወረድ ከፈለገችና በተገቢው ቦታ ሄዳ ከፈፀመችው ህጉ ሽፋን ይሰጣታል። ይቀጥላል።

ቸር እንሰንብት።

ነው። የማሳነስ ችግሩ ለሚያተልቅ ማስረጃ ቀልቡን አለመስጠቱ ነው እንጂ እዚያው መጽሐፍ ውስጥ አለቃ ዘነብ ስለአፄው እንዲህ ይላል፡-

‹‹ይህንን ክፋት ባየ ጊዜ እግዚአብሔር በህበሻ ላይ ንጉሥ ቴዎድሮስን አስነሳ። ምንዝር የማይወድ። ገንዘብ፣ ሐሰት፣ ስርቆት የማይወድ። ሸፍጥንም ሁሉ የማይወድ። እግዚአብሔርን የፈራ። እጅግ የሚሰጥ። እንግዳ የወደደ ለታመመ የሚያዝን በአንዲት ሴት የቀረበ።›››› በዕውቀቱ የጠቀሰው በእርግጠኝነት ከታመነ ይዟም የማይታመንበት ነገር አይታየኝም። አፄ ቴዎድሮስ ያከናወኗቸው የጭካኔ ተግባራት በዕውቀቱ እንዳደረገው በሌጣው የሚታዩ አይደሉም። ከህዝቡና ከክባቢ ሁኔታው ጋር ተገናዝቢ እንጂ። ይዜንን አስልተው የተደላደለ አቋም ላይ ለማረፍ የሞከሩ መርዕደ ወልደ አረጋይ የተሰኙ የታሪክ ምሁር ናቸው። ‹‹የቴዎድሮስ ዓላማዎች ከየት እንደመነጩ›› በተሰኘ ጥናታቸው እንዲህ ይላሉ፡-

‹‹ቴዎድሮስ ከልጅነታቸው ጀምሮ በሰዎች ተወዳጅነትን ወይም መጠላትን ካፈሩላቸው ጠባዮች መካከል ሐቀኝነታቸውና ታማኝነታቸው ነበሩ። በረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ ሒደት ኢትዮጵያውያን እውነት በመናገራቸውና በቃላቸው ዕኑ በመሆናቸው በጐረቤትና በሩቅ ሕዝቦች ታውቀዋል። ካስራስድስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ግን እነዚህ ጠባዮች ለብዙ ኢትዮጵያውያን እንግዶች እየሆኑ መጥተዋል። በግራኝ ወረራ አብዛኛው ሰው ጉልቱንና ሕይወቱን፣ እንዳያጣ ፈርቶ ንጉሱን ከድቷል። ሃይማኖቱን ክዷል። ከግራኝ ወረራ በኋላም ሰላምና የመንፈስ እረፍት የሚያሳጡ ሁኔታዎች በመፈራረቅ በመነሳታቸው የአድርባይነትና የምቀኝነት ጠባዮች እየጐሉ ሄዱ። በፊት ኢትዮጵያውያን በሐቀኝነታቸው የታወቁትን ያህል ከዚህ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በወላዋይነታቸውና አጠራጣሪነታቸው ዝናን አተረፉ። ይህን የጠባይ ለውጥ ያስመጡ የፖለቲካ አለመረጋጋትና የኑሮ አስተማማኝ አለመሆን ሲሆን ቴዎድሮስ እነዚህን ገና ሳያሻሽሉ የአስተያየት ለውጥ ማምጣትን አስቀደሙ።››

አፄ ቴዎድሮስ የቴክኖሎጂ ብቻ ሳይሆን የሞራልም ሥልጣኔ አባታችን ነበሩ የምንላቸው ለዚህ ነው። እንኳን አፄ ቴዎድሮስን ያህል ግዙፍ አምድ ለመገርሰስ ቀርቶ የመንደር ግራዋም ለመቁረጥ ምክንያት-ጉልበት፣ ልምምድና ጥናት ሊኖር ግድ አይልም-በዕውቀቱ?

ዳግማዊት ጃፓን፣ ዳግማዊ ቴዎድሮስ

(ክፍል ሁለት)



በእውቀቱ ስዩም

ዓለማየሁ ገላጋይ በቀደምለት፣ ስለስልጣኔ ባቀረበው ሐተታ ስለጃፓንና ስለ ኢትዮጵያ መመሣሠል እንዲሁም ስለዳግማዊ ቴዎድሮስ የስልጣኔ አርአያነት ተናግሮ አናግሮኝ ነበር። የዛሬ ሁለት ሰንበት እኔ ባቀረብሁት ሂስ ላይ መልስ ይዞ ቀረበ። በመልሱ ውስጥ ራሱን በሃገር ፍቅር የነደደ፣ እኔን ደግሞ የሃገር ፍቅር የጐደለኝ አስመስሎ በማቅረብ ከመርማሪዎች ያጣውን ድጋፍ ከአርበኞች ለመሰብሰብ ሞከረ።

ነገሩን በዝርዝር እንየው።

ወይ መመሣሠል!

አንባቢ እንደሚያስታውሰው፣ ጥንታዊት ኢትዮጵያና ጥንታዊት ጃፓን ስለለውጥ ተመሣሣይ አመለካከት እንዳልነበራቸው ፅፌ ነበር። ኢትዮጵያዊያን ለውጥን የሚያስጠላ ህዋስ ይዘው ተወልደዋል ብዬ አላስብም። ይሁን እንጂ ለውጥን እንዲፈሩና እንዲጠራጠሩ ያደረጋቸው ክፉ ገጠመኝ ተፈራርቆባቸዋል ብዬ አምናለሁ። በታሪካችን፣ ነባሩን ካዲሱ ጋር የሚያቻችል የርዕዮተ ዓለም ሽግግር እምብዛም አልታየም። ክርስትና በሚስፋፋበት ጊዜ መነኮሳቱ የአረሚያውያኑን ክብር፣ ርስት፣ አልፎ አልፎም ሕይወት ይነጥቁ ነበር። ቤተክርስትያኖችንም በጣፆት ቤተመቅደሶች ላይ ገንብተዋል። ኢማም አህመድ ወልደ አብራሃም አስልምናን ሊያስፋፋ የሞከረበት መንገድ ከደብረሊባኖስ አጠገብ መስጊድ በመገንባት ሳይሆን ደብረሊባኖስን በማቃጠል ካህናትን በመግደል ነው። አዲስ ሐሳብ አዲስ ጥፋት ተደርጐ እንዲፈራ ያደረገው ይህን የመሳሰለው ክፉ ገጠመኝ ነው። በጃፓን ታሪክ ግን ቡዲዝም በእንግድነት ሲመጣ ባላገሩን ሺንቶይዝምን አላባረረውም። ስለዚህ ሁለቱ ጥንታዊ ሕዝቦች ለውጥን በተመሣሣይ አይን አያዩትም ነበር ማለት ይቻላል።

አለማየሁ ተቃወመ። በ1614 (1638?) ጃፓኖች ክርስትያኖችን በአዋጅ ማሣደዳቸውን ቤተክርስቲያንንም ማገዳቸውን ለውጥን የመጥላት መገለጫ አድርጐ በመተርጐም ‹‹...**ይሄን ይሄን ስንመለስት ጃፓን እንዲያውም ከዓለም ህዝቦች ሁሉ በተለየ ለውጥን ባዋጅ ያገደች ድንበሯን የጠረቀመች ብቸኛ አገር ነች**›› ብሎ ፃፈ።

ዓለማየሁ ጃፓኖች ክርስትናን በ1614 ማገዳቸውን የጠቀሰው ልክ ነው። ይሁን እንጂ ክርስትና ከዚህ በፊት ለመቶ አመት ያላነሰ ጊዜ በጃፓን በነፃነት ይንሸራሸር እንደነበር የሚያውቅ አልመሰለኝም። ከበደ ሚካኤል በጃፓን እንዴት ሰለጠነች እንደገለፁት ‹‹...ጃፓኖች ለመጀመሪያ ጊዜ (በ1549) የፖርቹጋል ተወላጆች የሆኑ ካህናት ወደ አገራቸው በገቡ ጊዜ የክርስትያን ሃይማኖት በደግ አይን ተመልክተው እንዲያስተምሩ ፈቅደው አበረታቷቸው›› ። አለማየሁ ግን ክርስትና ገና የጃፓንን በር ሲያንኳኳ በካልቾ ተብሎ የተባረረ ይመሥል ቀዳሚ ታሪኩን ገድፎ ፅፏል።

ጃፓኖች መቶ አመታት የታገሡትን ሃይማኖት ሊያግዱ የተነሡበት ምክንያት የስፔን ቄሶች በተኩላ ገላቸው ላይ የበግ ሹራብ ደርበው ለቅኝ ግዛት ሲያደቡ ስለደረሱባቸው ነው። ይህም ራስን መከላከል እንጂ ለውጥን የመጥላት እርምጃ ተደርጐ አይቆጠርም።

ሌላው ቢቀር፣ ጃፓኖች ህልውናቸውን የወጠኑት በቻይኖች የተውሶ ፊደልና ባህል በመሆኑ አዲስ ሀሳብ ተቀባይነታቸውን ያጎላዋል።

‹‹በበፅውቀቱ ስዩም ፅሁፍ ውስጥ›› ይላል ዓለማየሁ። ‹‹ራስን አሳንሶ የመመልከት አባዜ ጉልቶ ይስተዋላል። ለምሳሌ ዶክተር ፅጌለ ገብረዮሐንስ ያቀረቡት ምርምር ያለ ሂስ መቀበል ጉዳት እንዳለው ጠቅሶ የበርትራንድ ረስልን ዘበታዊ ንግግር አገላብጦ ሳይመረመር ይውጣል››

ዓለማየሁ ከነባ አመለካከት የክርክር ሜዳ ወጥቶ ወደ አርበኝነት ጐራ ስልታዊ ማፈግፈግ አደረገ። ፅጌለ ገብረዮሐንስና እንግሊዛዊው ፈላስፋ ረስል ባንድ ሐሳብ ላይ ተስራክረው እኔ ለፈረንጁ ያደላሁ ይመስል በራስ ማሣነስ ሊከሰኝ ሞከረ። እኔ ከበርትራንድ ረስል የጠቀስኩት ጃፓኖች ቡዲዝምን ከመቀበላቸው በፊት መጥቀም አለመጥቀሙን ፈተሹት የሚለውን ንባብ ነው። ይህም የረስል የግል አስተያየት ሳይሆን ታሪካዊ ሐቅ ነው። ዓለማየሁ ታሪካዊ ሐቁን ‹‹ዘበታዊ ንግግር›› ብሎ የሚያናንቅበት መሠረት የለውም።

ዓለማየሁ ስለፈረንጅ ታሪክ የፈረንጅ ምንጭ መጥቀሴን ራስን ማሳነስ አድርጐ በተረጐመበት መጣጥፍ ውስጥ እሱ ራሱ ‹‹ጣይቱ ብጡል›› ስለተባለው የመኮንን እንዳልካቸው ያማርኛ ተውኔት የ‹‹ባዕዱ›› ሞልቬየርን አስተያየት ተውሷል። ራስን ማሳነስ ማለት እንዲህ ያለ ሳይተግር ጤፍ ብድር ነው።

ስለዳግማዊ ቴዎድሮስ

ስለዳግማዊ ቴዎድሮስ ለመናገር ትንሽ ፖለቲካዊ መናፍቅነት አስፈላጊ ነው። በበኩሌ ዓለማየሁ ንጉሡን የሞራል ስልጣኔ አርአያ ባያደርጋቸው ኖሮ እኔም ወደ ክርክሩ አልገባም ነበር። ንጉሡ፣ በዘመናቸው ከነበሩ ወደረኞቻቸው ጋር ሲነፃፀሩ በሞራል ኋላቀር ነበሩ ብዬ ነበር። እግርና እጅ በመቁረጥ መቅጣትን በይፋ የተቃወሙትንና ራሳቸውን ንጉሠ ዘብሔረ ኢትዮጵያ ብለው የሚጠሩትን ንጉሤ ወልደሚካኤልን ጠቅሻለሁ። በነበረው ላይ ለመጨመር፣ የራስ አሊን ሆደ ሰፊነት መጥቀስ ይቻላል። የሰሜኑ ራስ ውቤ በራስ አሊ ላይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ አድርገው ነበር። መፈንቅለ መንግስቱ ሲከሽፍ ራስ ውቤ በራስ አሊ እጅ ወደቁ። አሸናፊው ለተሸናፊው ምሕረት አድርገው ወደ ጥንቱ ማዕረጋቸው መለሷቸው።

ባገራችን ከደጐች ይልቅ ጀግኖች ይከበራሉ። ወትሮ በጠላት ተከብበን የምንኖር ሕዝብ በመሆናችን ጀግንነት ለሚባለው ነገር ዋጋ መስጠታችን ተገቢ ነው። ይሁን እንጂ በብዙ የታሪክ አጋጣሚዎች እንደታየው የውጭ ጠላትን አባርረን ስንመለስ እርስ በርሳችን ተከባብረን መኖር ያቅተናል። ለምን? ለአብሮ መኖር መሠረት የሆኑትን እነ መሐሪነትን፣ እነ ደግነትን፣ እነ ታጋሽነትን፣ መበልፀግ የሚገባቸውን ያህል አላበለፀግናቸውም። ወይም ለመሐሪዎቹ፣ ለደጐቹ፣ ለታጋሾቹ ተገቢውን ክብር የሰጠን አይመስለኝም።

ዓለማየሁ ቀጠል አደረገና ‹‹አፄ ቴዎድሮስ ያከናወኗቸው የጭካኔ ተግባራት በዕውቀቱ እንዳደረገው በሌጣው የሚታዩ አይደሉም። ከህዝቡ፣ ከክባቢ ሁኔታው ጋር ተገናዛቢ እንጂ›› በማለት የማያዋጣ ክርክር አመጣ። ይሄ ምን ማለት ነው? በቴዎድሮስ ዘመን የኖረው ሕዝብ በንጉሱ የደረሰበት ግፍ ተገቢ አለመሆኑን ያውቅ እንደነበር የምንገነዘበው

‹‹...አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ አንድዶ ለብልቦ አቃጥሎ ይፍጃችሁ›› የሚለው የምንትዋብ ግጥም ስንሰማ ነው። ዓለማየሁ ገላጋይ ነበልባሉ ከማይደርስበት ዘመን ላይ ተወልዶ የጭካኔውን ተገቢነት ሊያፀድቅ ይሞክራል። ያልተመለሰው ጥያቄ፡- የርህራሄን ትርጉም የሚያውቁ ሰዎችን ማግኘት በማይቸገርበት በዚያን ዘመን ዳግማዊ ቴዎድሮስ በርበሬ (Barbarian) የሚል ቅጽል ያስለጠፈባቸው ጭካኔ ውስጥ ለምን ገቡ የሚል ነው። ዓለማየሁ የመጨረሻ ሙከራ ለማድረግ የሚከተለውን የመርዕድ ወልደ አረጋይን ጥቅስ የሙጥኝ አለ።

‹‹...*ቴዎድሮስ ክልጅነታቸው ጀምሮ በሰዎች ተወዳጅነትን ወይም መጠላትን ካፈሩላቸው ጠባዮች መካከል ሐቀኝነታቸውና ታማኝነታቸው ነበሩ። በረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ ሒደት ኢትዮጵያውያን እውነት በመናገራቸውና በቃላቸው ፅኑ በመሆናቸው በጐሬቤትና በሩቅ ሕዝቦች ታውቀዋል። ካስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ግን እነዚህ ጠባዮች ለብዙ ኢትዮጵያውያን እንግዶች እየሆኑ መጥተዋል። በግራኝ ወረራ አብዛኛው ሰው ጉልቱንና ሕይወቱን እንዳያጣ ፊርቶ ንጉሱን ክድቷል። ሃይማኖቱን ክዷል። ከግራኝ ወረራ በኋላም ሰላምና የመንፈስ እረፍት የሚያሳጡ ሁኔታዎች በመፈራረቅ በመነሳታቸው የአድርባይነትና የምቀኝነት ጠባዮች እየጐሉ ሄዱ። በፊት ኢትዮጵያውያን በሐቀኝነታቸው የታወቁትን ያህል ከዚህ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በወላዋይነታቸውና አጠራጣሪነታቸው ዝናን አተረፉ። ይህን የጠባይ ለውጥ ያስመጡ የፖለቲካ አለመረጋጋትና የኑሮ አስተማማኝ አለመሆን ሲሆን ቴዎድሮስ እነዚህን ገና ሳያሻሽሉ የአስተያየት ለውጥ ማምጣትን አስቀደሙ*››

ዓለማየሁ ይህንን ጥቅስ የጠቀሰው የቴዎድሮስ ጭካኔ ከህዝቡና ካካባቢው ጋር ተገናዛቢ ነው ለሚለው ጭብጥ ማጠናከሪያ ይሆነኛል ብሎ ነው። ግን የመርዕድ ጥቅስና የዓለማየሁ ጭብጥ አራምባና ቆቦ ናቸው። የመርዕድ አንቀፅ ሲጨመቅ ከግራኝ በኋላ ኢትዮጵያውያን አጉል ባሕርያትን አዳብረዋል። ቴዎድሮስ ከህዝቡ ጋር ሲነፃፀሩ የባሕርይ ብልጫ አሳይተዋል። ቴዎድሮስ የስርዓት ለውጥ ለማምጣት ከመሞከራቸው በፊት የሕዝቡን ባሕርይ የማሻሻል ጥረት ማድረግ ነበረባቸው የሚል ነው።

አጠቃላይ ሐሳቡ በንጉሱ አመራር ቅደም ተከተል መፋለስ ላይ የቀረበ ሂስ እንጂ ጭካኔያቸውን የሚያፀድቅ አይደለም። ዓለማየሁ ጭብጤን ይደግፍልኛል ብሎ ይህን መጥቀሱ ያስተዛዝባል።

የመርዕድ ወልደአረጋይ ጥቅስ የዓለማየሁን ሐሳብ ባይደግፍም በራሱ ትክክልነቱ ያጠራጥራል። በመጀመሪያ የግራኝ ወረራን ተከትሎ የተከሰተ የሕዝብ ባሕርይ ድቀት መኖሩን የምናረጋግጠው እንዴት ነው? በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን የነበረው አድርባይነት ባጤ ዘርዓያዕቆብ ዘመን ከነበረው አድርባይነት እንደከፋ የምናውቀው በምን ሚዛን ነው?

አጤ ቴዎድሮስ ከገባሮቻቸው የተሻለ ባሕርይ እንደነበራቸው መጥቀስም ልክ አይመስልም። በደህናው ቀን የንጉሱ ጓደኛ፣ በጐደሎው ቀን እስረኛ የነበረው ዋልድማየር እንደገመገመው በጊዜው የነበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሩህና ንቁ የሚባል ነበር። ትምህርት ሲያገኝ ፈጥኖ ተቀባይ፣ ሩህሩህ ሲሆን በግፍ ሲነዱት ግን የቁም መንፈስ የሚያቆጠቁጥ አድርጐ ገልያታል። ዋልድማየር ከኢትዮጵያውያን ብላቴኖች መካከል ጥቂቱን ሂሳብ ጂኦግራፊና ታሪክ ማስተማር ጀምሮ በፈጣን የትምህርት አቀባበላቸው ተደምሞ ነበር።

በአውሮፓ ከሚገኙ ጥቂት ጥቁር ተማሪዎች ጋር ሲነፃፀሩ ከፍተኛ ብልጫ ያሳዩ ነበር። ከዚህ ሁሉ ጋር ሲነፃፀሩ ግን ቴዎድሮስ ከህዝቡ ጋር ሲነፃፀሩ ከፍተኛ ብልጫ ያሳዩ ነበር። ከዚህ ሁሉ ጋር ሲነፃፀሩ ግን

በፍትሕ ጋዜጣ ላይ ለምንጽፍ ሁሉ እየተናገሩ አለማነጋገር፣ እያሰቡ አለማሳሰብ



ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም

ይህ ጽሑፍ ለእኔም የተጻፈ በመሆኑ አንድ ቀልድ እንደመግቢያ ልናገር፤ አማኑኤል ሆስፒታል ሕመምተኛው ውጭ ፀሐይ እየሞቀ ይጽፋል፤ ሀኪሙ ይመጣና ‹‹ከበደ፣ እንደምናደርህ?›› ብሎት ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ፣ ሀኪሙ ምን እየጻፍክ ነው? ይልና ይጠይቃል፤ ህመምተኛው ‹‹ደብዳቤ›› ይላል፤ ሀኪሙ ‹‹ለማን ነው?›› ብሎ ሲጠይቅ፣ ሕመምተኛው ‹‹ለራሴ›› ይላል፤ ሀኪሙ የሕመምተኛውን የውስጥ ስሜት ለማወቅ ዓጉቶ ‹‹ምን ይላል?›› ብሎ ይጠይቃል፤ ሕመምተኛው በመደነቅ ዓይኑን በልጠጥ አድርጎ ‹‹ዶክተር መቼ ተላከና፣ መቼ ደረሰኝና!›› አለው፤ እኔም…

በኢትዮጵያ ውስጥ እያሰቡ ለወደፊት ማቀድ አያዋጣም፤ ለሁሉም ሰው የወደፊቱን የሚወስኑት ወንበሩ ላይ ተቀምጠው ሰይፉን የጨበጡት ብቻ ናቸው፤ ከአንድ ዓመት በኋላ ይህንን አድርጌ፣ ከሁለት ዓመት በኋላ ደግሞ ከዚህ ደረጃ ደርሼ… እያለ በራሱ ሀብት፣ በራሱ ጉልበትና በራሱ እውቀት ሥራውን እያቀነባበረ ከዓመት ወደ ዓመት በእቅድ የሚሄድ የተፈቀደለት ብቻ ነው፤ ፈቃዱም ቢሆን ለአንድ ዓመት የተሰጠው በሌላው ዓመት ይሰረዝ ይሆናል፤ ለባል የተፈቀደው ለሚስት አይሠራም ይሆናል፤ ምክንያቱ ግልጽ ነው፤ አንድ ሰውም ሆነ አንድ ድርጅት እቅድ እያወጣ እየተሳካለት ከአደገ በራሱ የሚተማመንና በራሱ ኃይል እየተራመደ የሚያድግ ሲሆን ላልተደላደለው ሥልጣን አስፈሪ ይሆናል፤ በቋፍ እንዲኖር የሚገደደው ደካማ ሆኖ በልመናና በመለማመጥ እንዲኑብጥ ስለሚፈለግ ነው፤ አንድ ሰው ራሱን ችሎ ብቅ ሲል በኩርኩም አናቱን እያሉ ማኮማተር ባህል ነው፤ አልፎ አልፎ እንዲህ በኩርኩም ልኩን እንዲያውቅ ካላደረጉት ጎበዙ ጎበዝ እየሆነ ጎበዝ ያፈራል፤ ከርሞ ጥጃ ከመሆን ይወጣል! ከርሞ ጥጃነት በሚፈለግበት ሥርዓት እድገት እንዴት ይመጣል?

ሀሳብን በጋዜጣ ማውጣት አደባባይ መውጣት ነው፤ አደባባይ የሚወጡበት ጉዳይ የግል ሳይሆን የአገርና የሕዝብ ነው፤ መሆን አለበት፤ አደባባይ በወጣው ጉዳይ ላይ በአገርና በህዝብ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ዜጋ ሁሉ ባለቤት ሊሆንበት ይችላል፤ በባለቤትነት ሊተችበት ይችላል፤ በጉዳዩ ላይ የሞቀ ክርክር ቢደረግበት ሁላችንም በብዙ መንገድ ተጠቃሚዎች ልንሆን እንችላለን፤ ነገር ግን እስከዛሬ የሚታየው አዲሱ ልምድ ከላይ ባለስልጣኖች እንደልባቸው ይናገራሉ፤ በግድም ይሁን በውድ አብዛኛው ሰው ይሰማቸዋል፤ ባለሥልጣኖቹን በማስተጋባት ቴሌቪዥኑና ራዲዮው ደጋግመው እስቲሰለች ድረስ ያሰማሉ፤ በግድም ይሁን በውድ የባለሥልጣኖቹ ንግግር ለብዙ ሰዎች ጆሮ ይደርሳል፤ ግን ጆሮ የደረሰ ሁሉ ወደልብ መተላለፉን እርግጠኛ መሆን አይቻልም፤ በአንጻሩ በግል ጋዜጦች ላይ የሚወጡት የተለዩና የተለያዩ ሀሳቦች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ አመራሩን የሚተቹ ናቸው፤ እነዚህን ጋዜጦች የሚያነብቡ በጣም ጥቂቶች ናቸው፣ ጋዜጦቹን የሚያገኙዋቸው በገንዘባቸው እየገዙ በመሆኑ የሰዎችን ቀልብ መሳባቸው ይታወቃል፤ እነዚህን ትችቶች ባለሥልጣኖቹ ጉዳያቸው አድርገው የሚያነቡዋቸው አይመስለኝም፤ የእነሱ ንቀት ሚስትህ አረገዘች ወይ ቢሉት፣ ማንን ወንድ ብላ! እንዳለው ነው መሰለኝ፤ ባለሥልጣኖቹ ሁለት ጥቅሞችን ያጣሉ፤ አንደኛ የተቺዎቹን ሀሳብ መረዳትና ከራሳቸው ሀሳብ ጋር የማመዛዘን ዕድሉ ያመልጣቸዋል፤ ሁለተኛው ሕዝቡ በነፃነትና ያለምንም ግዴታ ትችቱን በማንበቡ ብቻ የሚያስተላልፈውን መልእክት ሳያውቁት ይቀራሉ፤ የዚህ ውጤት የአገር ጉዳት ነው፤ እንግዲህ እነሱ የሚናገሩትን ይናገራሉ፤ ሌላውም የሚናገረውን ይናገራል፤ በሁለቱም ወገን የሚነገረው ስለአንድ አገርና ስለአንድ ሕዝብ ነው፤ በሁለቱም በኩል የተያዘው ፈሊጥ ሳያነጋገሩ መናገር ነው፤ ክፉ ሕመም ነው።

የሳያነጋገሩ መናገሩ ፈሊጥ የሚታየው በባለስልጣኖችና በተቺዎቻቸው መሀከል ብቻ አይደለም፤ በተቺዎቹም መሀከል ያው ነው፤ ተቺዎቹም መናገሩን እንጂ እርስበርሳቸው መነጋገሩን ገና የለመዱት አይመስልም፤ እንደታዘብሁት እስካሁን ድረስ በፍትሕ ጋዜጣ ላይ በየሳምንቱ የሚናገሩት ሁሉ እርስበርሳቸው እምብዛም አይነጋገሩም፤ ይህ ሊሆን የሚችለው እያንዳንዱ በሚናገረው ሁሉም ፍጹም ስምምነት ካላቸው ብቻ ነው፤ ወያኔ/ኢህአዴግም እንደዚህ ያለ ፍፁም ስምምነት ያለው አይመስለኝም፤ ወይም በጋዜጣው ላይ የሚናገሩት ሁሉ ይፈራራሉ ማለት ይሆናል፤ ለመፈራራታቸው ብዙ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል፤ ነገር ግን አንዱም ምክንያት ለአገርም፣ ለወገንም፣ ለራስም ጠቃሚ አይመስለኝም፤ እንዲያውም የባለስልጣኖቹን ባሕርይ ወደመውረሱ የሚያስጠጋ ይመስለኛል፤ ይህ እውነት ከሆነ፣ ማለት በእኩልነት መነጋገር የማንችል ከሆነ መጀመሪያ ማድረግ ያለብን እያንዳንዳችን ለየራሳችን ተገንዝበን ካረጋገጥን ራሳችንን የምናስተካክልበትን መንገድ መከተል ግዴታ ይሆንብናል።

የፍትሕ ጋዜጣ የተሟላና የተዋጣለት ነው ባይባልም፣ በጣም ተፈላጊና ብዙ ሰውም የሚያነብበው ነው፤ ሆኖም በማስፈራራት የተካኑ ሎሌዎች አቤ ቶኪቾን ለስደት ከዳረጉት ወዲህ ፍትሕ ትንሽ ደረቅ ብሏል! በሀሳብ፣ በአስተያየትና እውቀትን በማስፋት የሚቀርቡት መጣጥፎች አብዛኛውን ጊዜ ፀሐፊው ከራሱ ጋር ብቻ የሚያወራባቸው መስለው ይታያሉ፤ የአንባቢን አእምሮ የመኮርኮር፣ ክርክር እንዲከፍት የማድረግ ኃይል ያላቸው አይመስሉም፤ ይህ የመጣጥፎቹ ጉድለት አይመስለኝም፤ ጠጥቶ ዝም፣ የጋን ወንድም! የሚባለው ዓይነት አንባቢና ፀሐፊ ነው፤ በጋዜጣው ላይ ብዙ ሰዎች መጣጥፎችን ቢያቀርቡም እርስበርሳቸው ሲነጋገሩ ወይም ሲከራከሩ አይታዩም፤ ይህ የሕመም ምልክት ይመስለኛል፤ አንድ ሰሞን ከአቶ ስብሐት ነጋ ጋር፣ አንድ ሰሞን ከፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀኝ ጋር ክርክር ቢጤ ተጀመረና ሁሉም እየሮጠ በየምሽጉ ገብቶ ተቋረጠ፤ በዚያን ጊዜም ቢሆን ክርክሩን ከመሩት ሰዎች ውጭ የገባ አንድ ወይም ሁለት ሰው ብቻ ይመስለኛል።

በተለያዩ መንገዶች ደጋግሜ እንደገለጥሁት በእኩልነት ደረጃ ሆነን ለመነጋገርና ለመከራከር ያቅተናል፤ በየፊናችን ስንናገር ራሳችንን ላይ አውጥተን ሰሚውን ከታች አድርገን መደመጥን እንጂ እኛ በተራችን ሌሎችን ማድመጥ እንዳለብን አናውቅም፤ እኛ ለመናገር የምንደፍረውን ያህል ለተናገርነው መልስ የሚሰጠው ድፍረት እንዲያገኝ አንፈልግም፤ እንዲያውም መልስ ከተሰጠን እናኮርፋለን፤ ከመሳፍንት አገዛዝ የወረስነው ባህል ነው፤ ለዚህ ነው ክርክር የማንጀምረው፣ ቢጀመርም የማይቀጣጠለው።

አሁን ደግሞ ስለኢትዮጵያና ጃፓን፣ ስለአጼ ቴዎድሮስና ስለአንድ የጃፓን ንጉሥ ክርክር እየተካሄደ ነው፤ አዝማሚያው የተለመደውን ባሕርያችንን የያዘ ይመስለኛል፤ አንዱ ስለሁነት ሲናገር አንዱ ስለዓላማ ሉዓላዊነት እየተናገረ፣ አንዱ ስለአጼ ቴዎድሮስ ተግባር ሲናገር፣ ሌላው ስለአጼ ቴዎድሮስ ዓላማ መልስ ቢሰጥ መግባባት አይኖርም፤ ክርክሩን እያሻከረው ነው፤ በበኩሌ ሁለቱ ሰዎች የከፈቱት ክርክር ብዙ ቁም-ነገሮችን የያዘ በመሆኑ ብዙ ሰዎችን ይስባል የሚል እምነት ነበረኝ፤ አሁን እንደሚታየው ግን ሁለቱ ሰዎች እንደተለመደው እየተናገሩ ነው እንጂ እየተነጋገሩ አይደለም፤ ስለዚህም አንዳንዶቻችን ክርክር ውስጥ ገብተን የታሪክን አስተሳሰብና ታሪክን የማጥናትና የማጽዳት ኃላፊነታችንን ብንወጣ ጠቃሚ ይመስለኛል።

በክርክሩ ውስጥ ብዙ ሰዎች የሚያውቁትን እየያዙ ቢገቡበት ስለቴዎድሮስና ስለዚያ ዘመን ከፍተኛ ትምህርት እናገኝበት ነበር።

የዳግማዊ ቴዎድሮስን አገርዓቀፍ እንድምታ ለመመልከት ‹‹ከፍታ››

ዓለማየሁ ገላጋይ

ከዕውቀት ወደ ጭፍን እምነት፣ ከማሳወቅ በደፈናው ወደ ማጥመቅ፣ ከማስማማት ወደ ግትር ግዘት… ያዘነበለውን የበዕውቀቱ ስዩም መከራከሪያ ዕሁፍ ሳምንት አነበብኩ። ‹‹ዳግማዊ ጃፓን፣ ዳግማዊ ቴዎድሮስ›› ከተሰኘው ከዚህ ዳግማዊ ዕሁፍ የተረዳሁት አንድ ነገር ብቻ ነው። በዕውቀቱ በተለይ አፄ ቴዎድሮስን በተመለከተ አንዳች ጥርጣሬ እውስጡ በቅሏል። ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስን ውሸት ያገዘፉት፣ ስህተት ዘላለማዊነት ያጐናፀፉት፣ ማለባበስ ያከበራቸው፣ ስለመሆኑ ጠርጥሯል። ለጥርጣሬው ማረጋገጫ ሳያገኝ ደምድሟል። በድምዳሜውም ዕኑ አቋም ይሏል። ይሄን ዕኑ አቋም በዕውቀትና በምርምር ከማስደገፍ ይልቅ የሰብዓዊነትን ስስ ብልት ለመምታት ማነጣጠርን የክርክሩ አዋጪ መንገድ አድርጐ ወስዷል። እንዲህ ይላል፡-

‹‹በቴዎድሮስ ዘመን የኖረው ህዝብ በንጉሱ የደረሰበት ግፍ ተገቢ አለመሆኑን ያውቅ እንደነበር የምንገነዘበው

‘አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ
አንድዶ ለብልቦ አቃጥሎ ይፍጃችሁ’

የሚለውን የምንትዋብ ግጥም ስንሰማ ነው። ዓለማየሁ ገላጋይ ነበልባሉ ከማይደርስበት ዘመን ላይ ተወልዶ የጭካኔውን ተገቢነት ሊያፀድቅ ይሞክራል። ያልተመለሰው ጥያቄ የርህራሄን ትርጉም የሚያውቁ ሰዎችን ማግኘት በማይቸግርበት በዚያን ዘመን ዳግማዊ ቴዎድሮስ በርበራ (Barbaian) የሚል ቅፅል ያስለጠፈባቸው ጭካኔ ውስጥ ለምን ገቡ የሚል ነው።››

የበዕውቀቱ ዕሁፍ ‹‹ልብ›› ያለው እዚህ አንቀጽ ውስጥ ነው። …‹‹ዳግማዊ ቴዎድሮስ… ጭካኔ ውስጥ ለምን ገቡ?›› ይቺ ጥያቄ የብዙ ‹‹ንፁሃን›› እና ‹‹ጨዋዎች›› የፍርድ መሰናክያ ጉድባ ናት። ‹‹ለምን?›› ሰውን ከሰው ብቻ ሳይሆን ሰውን ከፈጣሪው ጋር ጭምር ለማቃቃር ጉልበት ያላት ጥያቄ። በነባሩ ትውፊታችን ብንመለከት የእግዚአብሔር ሕልውና ላይ በጠርጣሪነት (Agnosticism) እንዲህ የሚያነሳን ግጥም አለ።

‹‹የለህም እንዳልል ይመሻል ይነጋል፣
አለህም እንዳልል እንዲህ ይደረጋል፤››

በዕውቀቱ ስዩም ይሄንን የእግዚአብሔር ህልውና ግብረገባዊ ማረጋገጫ (Moral argument) ለአፄ ቴዎድሮስ የታሪክ ህልውና መለኪያ በማድረግ የመጀመሪያውን ስህተት ፈጽሟል። በመሆኑም ያ‹‹ንፁሃን እና ጨዋዎችን›› ለሚያጠቃው የፍርድ መሰናክያ ጉድባ እራሱን አጋልጧል። የበዕውቀቱ መሰናክያ ጉባ ጥቂት የጭካኔ ተግባራትን በማስረጃነት አቅርቦ አፄ ቴዎድሮስ ያላቸውን መልካም የታሪክ ሀብት ሁሉ የመውረስና የማደህየት፤ ዘመናዊነት የሌለው ጥንታዊ የበቀል ፍርድ ነው። በዕውቀቱ በነባሩ የትውፊት ወግ በአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ላይ ያለውን የተጠራጣሪነት አዝማሚያ በግጥም ቢያቀርብ እንዲህ የሚል ይመስላል፡-

‹‹የሥልጣን አውራ ብለው ይጠሩሃል፣
እንዳልቀበለው እንዲህ አድርገሃል፤››

የአፄ ቴዎድሮስ የሥልጣኔ አውራነት ‹‹እንዲህ በማድረጋቸው›› ሊመዘን አይገባውም። በዚህ ጉዳይ ላይ የዘመኑን መከራከሪያ እናቅርብ ብንል አፄ ቴዎድሮስ ‹‹እንዲህ ማድረጋቸው›› የአፈፃፀም ችግር ነው ብለን እንዘጋው ነበር። ከዚያ ባሻገር አፄ ቴዎድሮስ የቴክኖሎጂ ሆነ የሥነ-ምግባር ስልጣን አርአያነታቸው እንዳለ ለብቻው ተመዝኖ ክብደቱና ቅለቱ የሚረጋገጥ እንጂ ‹‹እንዲህ ከማድረጋቸው›› ጋር ተደብሎ የሚወራረስ አይደለም።

አፄ ቴዎድሮስ ውሸት እንዳላገዘፋቸው፣ ስህተት ዘላለማዊነት እንዳላጐናፀፋቸው፣ ማለባበስ እንዳላከበራቸው፣ ከጉቱ መታበይ እንዳላጐለመሳቸው… ለማረጋገጥ የሚያስችል ብዙ የታሪክ መረጃዎች አሉ። በዕውቀቱ ከሀሳብ ጨለማ ባሻገር ብርሃናማ የታሪክ ቅንጣቶችን እንዲለምድ ቢያስችለው ከብዙ በጥቂቱ እንጥቀስ። የሥነ-ምግባር ሥልጣኔን እናስቀድም።

ጳውሎስ ኞኞ Hennery Dutton የፃፈውን ጠቅሶና ተርጉሞ ‹‹አጤ ቴዎድሮስ›› የተሰኘ መፅሐፍ ላይ እንዲህ ይላል፡-

‹‹…ድሆችን እራሳቸው እየተቆጣጠሩ ይጠብቃሉ። ድንኳናቸው በተተከለበት ቦታ ሁሉ የድሆችን አቤቱታ መስማት ይወድዳሉ። ሁልጊዜ ስራ ከመጀመራቸው በፊት የድሆችን ጉዳይ ይሰማሉ። በጉዞም ላይ በሳምንት በሺዎች የሚቆጠር ብር ለድሆች ይሰጣሉ። ይኸንንም ስጦታ በሚሰጡበት ጊዜ ‹‹ድሆችን ባልረዳ ለእግዚአብሔር ያሳጡኛል። እኔም እራሴ ደሃ ነበርኩ ይላሉ››

እንኳን ንጉስ ያለፈለት ተራሰው ‹‹እኔም እራሴ ድሃ ነበርኩ›› ለማለት ይደፍራል? ያውም በዚያ ደሃ በሚነወርበት፣ በሚናቅበት፣ በሚረገጥበት እና በአጥንተ ሰባራነት በሚንቋሸሽበት ዘመን ነው አፄ ቴዎድሮስ ይሄንን ከአፋቸው ሲያወጡ የተሰሙት። ድሆችን እንደወገን መቁጠር ብቻ ሳይሆን ከእነሱ እንደአንዱ አድርጐ እራስን ማሰብ ከቴዎድሮስ ብንማር በዚህ ዘመን አስተዳደር ላይ ስንት የሥነ-ምግባር ችግር ይቀረፍ ነበር? ይሄ ነው አፄ ቴዎድሮስን የሥነ-ምግባር ሥልጣኔ አባት



የሚያሰኛቸው። ከዚያው ከጳውሎስ ኞኞ መጽሐፍ ይሄን እንጥቀስ፡-

‹‹ቴዎድሮስ ጋይንት ላይ ሠፍረው ሳለ ወታደሮቻቸውን በባላገሩ ላይ ተሰሪ አገቡ። ባላገሩ እንዲቀልብ በየቤቱ ማስገባት ማለት ነው። ተሰሪ ከገቡት ወታደሮች መካከል አንዱ ወታደር አንዱን ባላገር ገደለው። የሟች ወገንም ከቴዎድሮስ ዘንድ መጥቶ አመለከተ። ቴዎድሮም ወታደራቸውን ሁሉ አፈርሳታ አስቀምጠው ገዳዩን አውጣ ብለው ያዙ። ወታደሩም በመላው አድሞ ገዳዩን አላየንም እያለ በቁስ እየተገዘተ ወጣ። የሟች ገዳይ ወታደር በመጥፋቱ ቴዎድሮስ ተናደው፡-

‹‹ወታደር ብላ፣ ባላገር አብላ ያልሁ እኔ ነኝ። ደመኛህም እኔ ነኝና እኔን ግደል›› ብለው ተነስተው ለከሳሹ ነገሩት። ከሳሹም ‹‹እኔ ንጉስ መግደል አይቻለኝም›› አለ። ቴዎድሮስም እንዲያውስ ደም በከንቱ አይቀርም ብለው ለሟቹ ወገን የደም ገንዘብ ዋጋ ሰጥተው ሸኙት።››

በዕውቀቱ ስዩም ከዚህ የአፄ ቴዎድሮስ የዳኝነት ሥነ-ምግባር እርቆ እንኳንስ ያላግባብ ለገደለ ወታደራቸው ቀርቶ ልከውትም ለገደለው ኃላፊነት ለማይወስዱት ባለሥልጣናት መፍትሔ ሥራይ መሆኑን መቀበል አይሻም። ሌላ አንድ መሰል የዳኝነት ሥነ-ምግባር እንጥቀስ፡-

ይሄንን ሽራፊ ታሪክ የሚነግሩን አቶ ገሪማ ታፈረ ናቸው አንድ ጊዜ ቴዎሮስ አንድ ታማኝ ወታደራቸውን ጠርተው ‹‹በፍርቃ በር በኩል እርጉዝ ሴት እንኳን ብትሆን እንዳታልፍ ጠንክረህ ጠብቅ›› ብለው አዘዙ። በሌላ ቀን ደግሞ ሌላውን ወታደር ጠርተው ‹‹ፈረስ እያለዋወጥክ ይህን ወረቀት የጁ ሰጥተህ በአስቸኳይ በስድስት ቀን ውስጥ ተመልሰህ እንድትመጣ›› ብለው ላኩት።

በተላኪና በጠባቂ መካከል የ‹‹አልፋለሁ፣ አታልፍም›› ፀብ ተነስቶ ጠባቂው ተላኪውን ገደለው። የሟች ወገኖች ቴዎድሮስ ፊት ቀረቡ። ‹‹በችሎቱ ላይ›› ይላሉ አቶ ገሪማ ‹‹በችሎቱ ላይ የተቀመጠው ፈራጅ ሁሉ እየተነሣ ገዳዩን ‹‹በደለኛ ነህ ስትሞት ይታየናል›› እያሉ ፈረዱ። አንድ ፈራጅ ግን ከተቀመጡበት ተነስተው ‹‹…ማየት የሚገባን በመጀመሪያ ከንጉሱ የተሰጠውን ትእዛዝ ነው። አንዱን ጠርቶ በዚህ በር ያለኔ ፍቃድ ወንድ ይቅርና የፀሰቸ ሴትም ብትሆን እንዳታልፍ ብሎ ማዘዝ፤ እንደገና ሁለተኛውን ወታደር ጠርቶ ቀንና ሌሊት ሳታርፍ በስድስት ቀን የጁ ደርሰህ እንድትመለስ ብሎ ማዘዝ አግባብ ስላልሆነ ጥፋቱ የሚመለከተው ንጉሠ ነገሥቱን ነው። ነገር ግን ብርሃን ናቸውና ምን ይደረግ›› ብለው ተቀመጡ።

አጤ ቴዎድሮስ ይህንን ንግግር ሲሰሙ ከመቀመጫቸው ብድግ ብለው ‹‹እንዲህ ነው መሸምገል፣ ሁለት ጠጉር ማብቀል። በደለኛው እኔ ነኝ። ፍረዱብኝ›› ብለው ከተከሳሹ ወታደር ቦታ ወርደው ቆሙ። ወዲያውም ፈራጆች በፈረዱት ፍርድ መሠረት ለሟች ወገን 500 ብር የደም ዋጋ ቴዎድሮስ እንዲከፍሉ ተፈርዶ በስምምነት አለቀ። ለዚያን ዘመን ዋጋ በቴዎሮስ ላይ የተፈረደው 500 ብር አጠፌታ ዋጋ መሆኑ ነው።››

በዕውቀቱ ስዩም! በኢንተርኔት ለተጠየቀ ማብራሪያ ስንትና ስንት የግልምጫ ጡጫ የሚያወርድ መሪ ያለበት የዚህ ዘመን ተሳታፊ ነህና፤ የአፄ ቴዎድሮስን ከዙፋን ተነስቶ ተከሳሽ ሳጥን ውስጥ መቆም ልትኖርበት ባይሆንልህ ለምኞትህ ማሟያ በተቀበልከው በተገባ ነበር። ግን አልሆነልህም። የአፄ ቴዎድሮስን የሥነ ምግባር ሥልጣኔ አርአያነትን የሚያረጋግጡ ብዙ፣ እጅግ ብዙ የታሪክ ቅንጣቶችን እዚህ ማቅረብ ይቻላል።

ወደ ገፅ 14 ዞሯል



ከታዴዎስ ታንቱ

ከእንግዲህ መቃብር በርትተህ ተማር፤ ጸመ ድጓ ይዞ መጣልህ መምህር::

በጥይት ይደበደባሉ። ዛሬ ይፈፀማል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ኃይል ሹማምንት ወስነዋል። ሐዋርያው የሐይማኖት አባት አልተነገራቸውም። ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ጭካኔ በመነሳት ሊሆን የሚችለውን ለመገመት ግን በአስተውሎት እጥረት አይታሙም። ሞት ደግሞ አይፈሩም። የአቤልን ዕዋ በልበ ሙሉነት ይጨልጣሉ። በሐዋርያዊ ተልዕኮአቸው ለምዕመናን የረጅም ዓመታት አገልግሎት ተስፋ ሰንቀዋል። ለኢትዮጵያ አርቶዶክስ ክርስትና አስተምህሮ ተቀብተዋል። በአርበኝነት አቋማቸው ሣቢያ ግን በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ትዕዛዝ አሁኑኑ የሞት ቅጣት ይፈፀምባቸዋል። ያለፍርድ በውሳኔ ያልቃል።

ዛሬ ስምንት ቀናቸው ነው። ለብቻቸው ታሥረዋል። ሰሌን አንጥፈው ድንጋይ ይንተራሳሉ። በቀን አንድ እንጀራና ውኃ በቅል አልተነፈጉም። ከትናንት ወዲያ ማታ አንስቶ ግን እንጀራም ሆነ ውኃ አልገባላቸውም። ጾማቸውን ውለው አድረዋል። ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሹማምንት በወረደ ትእዛዝ ምንም ነገር እንዳይገባላቸው ተወስኗል። የግድያ ቅድመ ግድያ ትእዛዝ ፀንቷል።

ጧት ተነሥተው ሦስት ጊዜ አማተቡ። በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን! ከውዳሴ ማርያም የዕለቱን ፀሎት አደረሱ። ብዙም አልቆዩም። በመጽሐፍ ቅዱሳቸው ላይ ውዳሴ ማርያምና መስቀላቸውን አስቀመጡ። የነተበች ጋቢያቸውን ተከናነቡና ሰሌናቸው ላይ ድንጋዩን ተንተርሰው ኩርምት ብለው ተኙ። አንድ ሰዓት ያህል ዕንቅልፍ እምቢ ብሏቸው በሐሳብ ቀዩ! ያስባሉ! ያስባሉ! በድንገት ግን ዕንቅልፍ ወሰዳቸው። ማንም ምንም አልቀሰቀሳቸውም። ግን ነቁ። በሐሳብ ባሕር ሰመጡ። በዚህ መካከል ሁለት ጣሊያኖች መጥተው የታሰሩበትን ክፍል ሳንቃ ብርግድ አደረጉ። አንዱ መኮንን ሲሆን ሁለተኛው የበታች ሹም ነበር። ሐዋርያው ጋቢያቸውን ከግንባራቸው ገለጥ አድርገው ወደ በር ተመለከቱ። ጣሊያኖችም ተመለከቷቸው። ጀግናው ሐዋርያ አንዲት ኢጣልያንኛ ቃል እንኳን አያውቁም። ኢጣሊያኖቹ ደግሞ አማርኛ ፊዯሞ አይናገሩም። ምን ማድረግ ይችላሉ? ቱርጁማኑ ሹምባሽ ገብረ ወልድ ሩፌ ዘግይቷል። መኮንኑ ተቁነጠነጠ። ትዕግሥት አጣ። ሹምባሽ ገብረወልድ ግን ብዙ አልቆየም። እየሮጠ ደረሰ። መኮንኑ ተናድዶ ነበር። አሁን ግን ቀዝቀዝ አለ። ሐዋርያው ለገናናው የኢጣሊያ መንግስት ለመገዛት ከፈቃደኝነት አቋም ደርሰው ይሆን? ሹምባሽ ገብረወልድ ሩፌ የመኮንኑን ጥያቄ ከኢጣሊያንኛ ወደ አማርኛ መነዘረላቸው። ‹‹እኔ ከሐይማኖቴና ከሰንደቅ ዓላማዬ ሌላ ማንንም አልቀበልም›› ፍርጥም ያለ መልስ ሆነ። ሹምባሽ ገብረወልድ የሐዋርያውን ዕኑ አቋም ለኔቶቹ ደግሞ ወደ ኢጣሊያንኛ መነዘረው። ጣሊያኖቹ ተናደዱና በሩን እላያቸው ላይ ዘግተው ተመልሰው ሄዱ። ጀግናው ሐዋርያም ኩርምት ብለው ተኙ። ቀጥሎ ምን ሊሆን ይችላል? ሐዋርያው በሐሳብ ሰምጠዋል። የአርበኞችን ድል ለማየት ቋምጠዋል።

ከግማሽ ሰዓት በኋላ ጣሊያኖቹ ተመልሰው መጡ። ሹምባሽ ገብረወልድ በሩን ከፈተው። ሐዋርያው እንዲወጡ ተነገራቸው። መፅሐፍ ቅዱሳቸውን፤ መስቀላቸውንና ውዳሴ ማርያምን ይዘው ሊወጡ ሲሉ እንዲያስቀምጡ በሹምባሽ ገብረወልድ አስተርጓሚነት ተነገራቸው። ጀግናው ሐዋርያ ግን የጣሊያኖቹን ትዕዛዝ ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበሩም። ‹‹እኔ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ካልሆነ በስተቀር የሰውን አልቀበልም!›› ፅኑ አቋም አንፀባረቁ። ሹምባሽ ገብረ ወልድ ለጣሊያኖች ይህንኑ ነገራቸው። ጀግናው ሐዋርያ ቅዱስ ንብረታቸውን ይዘው ወጡ። አቅም አንሷቸው ሲንገዳገዱ ይስተዋላል። ኢጣሊያኖቹና ሹምባሽ ገብረወልድ ከኋላቸው እሳቸው ደግሞ ከፊት ነበሩ። አቅመ ቢሱ ግን ልበ ሙሉ ሐዋርያ ከተጠበቀው ፍጥነት በወረደ እርምጃ ተወስነዋል። ኢጣሊያኑ መኮንን ተናድዶ በጀርባቸው ላይ ባለ በሌለ ኃይሉ ረገጣቸው። ከመቅፅበት ወደቁ። መነሳት ተስኗቸዋል። ቀስ ብለው በሁለት እጃቸው መሬቱን ተመርኩዘው ተነሱ። ወዲያው መፅሐፍ ቅዱሳቸውን፤ መስቀላቸውንና ውዳሴ ማርያምን ሰብስበው ጉዟቸውን ቀጠሉ። ሐዋርያው የኢትዮጵያ ጀግና ሊገደሉ እንደሚወሰዱ ግን እስካሁንም አልተነገራቸውም። ብዙ ቤቶችን አልፈው አሁን ወደ አደባባይ ወጥተዋል። በጎሬ ከተማ ውስጥ ትልቁና ዋናው ሜዳ ይህ መሆኑ ይመዘገብልን። ሐዋርያው ከግድያ ስፍራ ደርሰዋል።

የፋሽስት ኢጣሊያ ሹማምንት ቆመዋል። ምድረ ባንዳ ወዲያ ወዲህ ይላል። ሕዝቡ ከገጠር ጭምር በትእዛዝ ተሰብስቧል። ሕዳር 24 ቀን 1929 ዓ.ም. እንደ ነበር ይዘናል። ፊርቶ የተሰበሰበ ሕዝብ በሐዘን ተውጧል። በሐዘን የተዋጠ ሕዝብ ፊርቶ ተሰብስቧል። ከቆሙት የኢጣሊያ ሹማምንት አንዱ በስልጣን ይበልጣል። ጀግናው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ሐይማኖት ሐዋርያ ቆመዋል። ሕዝቡ ከተወሰነው ርቀት በመቀነስ ወደ ፊት ከተጠጋ ይገደላል። ነፍስ ገዳይ ቡድን በተጠንቀቅ ይስተዋላል። ሁለት አርበኞች ግን ገና አልመጡም። አንደኛው ቀኝዝማች ይነሱ ይባላሉ። ሁለተኛው ደግሞ ግራዝማች ተክለ ሐይማኖት እንደ ነበሩ ታውቋል። ጀግኖቹ ከጀግናው ሐዋርያ ጋር አንድ ላይ ይገደላሉ። ሃያ ሜትር ጉድጓድ ተምሷል። አፏን ከፍቶ ይጠባበቃል። ጀግኖቹ አርበኞች አሁን ደረሱ። ሁለቱም እጆቻቸው በሰንሰለት ታስረዋል። በርካታ ባንዳዎች አጅበዋቸዋል። አርበኞቹ ከፊታቸው ፍርሃት አይነበብባቸውም። ከጀግናው ሐዋርያ አጠገብ እንዲቆሙ ተደረጉ።

የሚቀጥለው ሥነ ሥርዓት አሁን ቀጥሏል። ሹምባሽ ገብረ ወልድ ሩፌ ወደ አማርኛ ይመነዝረዋል። በጎሬ ትልቁ የፋሽስት ኢጣሊያ ሹም ንግግር ይሰማል። የሐዋርያውን ወንጀል በቅድሚያ ዘረዘረ። በተመሳሳይ መልኩ የሁለቱን አርበኞች ጥፋት አመለከተ። የፋሽስት ኢጣሊያ ሹም ንግግር አበቃ። የግድያ ሥነ ሥርዓት አሁን ይከናወናል። ሁለት ባንዳዎች ጀግናውን ሐዋርያ በግራና በቀኝ ይዘው ከጉድጓዱ አፍ ላይ አስቀመጧቸው። ጀግናው ሐዋርያ በመስቀላቸው ሦስቴ አማተቡ። የመሸበር ሁኔታ አይታይባቸውም። ለእናት ሀገራችን ክብር ሞትን በፀጋ ለማስተናገድ ቆርጠዋል። ማን ይፈራል ሞት ማን ይፈራል? ለእናት ሀገር ሲባል! በመቀጠል ደግሞ ባንዳዎቹ ሁለቱን አርበኞች ከጉድጓድ አጠገብ አመጧቸው። ቀኝዝማች ይነሱ ከሐዋርያው በግራ በኩል እንዲቀመጥ ተደረገ። ግራዝማች ተክለ ሐይማኖት ደግሞ በቀኝ በኩል ሆነ።

ስምንት አባላትን ያካተተ አንድ ነፍስ ገዳይ ቡድን ቆሞ ትእዛዝ ይጠባበቃል። አሁን ትእዛዝ ሊሰጥ ነው! አስተኳሹ ተዘጋጅቷል። ሁሉም ሰው ትርዒቱ የሚያስከትለውን ትርዒት በሐዘን ይመለከታል። ‹‹ተኩስ!›› ወታደራዊ ትዕዛዝ ተሰጥቷል። ድምምምምምም! ገቢራዊ ሆኗል። ሦስቱም የኢትዮጵያ ጀግኖች ከፊት ለፊታቸው በነበረው ጉድጓድ ውስጥ ወደቁ። አፈር ለመመለስ ከባንዳ ያነሰ ማን ይታዘዝል? ወዲያው ትእዛዝ ተሰጠ። በአካፋና በእጅ አፈሩ ተመለሰ። የብፁዕ ቅዱስ አቡነ ሚካኤል የግፍ አገዳደል በጎሬ።

ብፁዕ አቡነ ሚካኤል በጎንደር ክፍል ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ በአፈረዋናት ወረዳ ውስጥ በ1874 ዓ.ም. ተወለዱ። ወላጆቻቸው በግብርና ሥራ ይተዳደሩ እንደነበር በሕይወት ታሪካቸው ላይ ተመልክቷል። ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ በጎንደ አጠመም ሚካኤል የቤተ ክህነት ትምህርት ዕውቀት ገብይተዋል። እድሜአቸው ከፍ ሲል ወደ ገላውዲዎስ ደብር ተልከው ዕዋትው ዜማ በሚገባ አጥንተዋል። በዚሁ ብቻ ተወስነው አልተቀመጡም። ከፍተኛ የትምህርት ፍቅር ስለነበራቸው ወደ ማህደረ ማርያም አመሩ። እዚያ ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ ፀዋትው ዜማ ትምህርት ተከታትለው አጠናቀቁ። ተገቢውን እውቀት ቀስመዋል። በደረጃው ደረጃው የፊቀደውን በሚገባ አሟልተዋል።

የትምህርት ጥማታቸው ግን አልበረደም። የዕውቀት ጉጉታቸው ገደብ አጥቷል። አሁን ወደ ጎንደር ተመለሱ። መጽሐፍተ ብሉያትንና ሐዲሳትን ትርጓሜ በሚገባ ተማሩ። አወቁ። በዚህም ብቻ አላበቁም። ወደ ወሎ አመሩ። ቦረና ሜዳ ከአካለ ወልድ ጉባዔ ላይ ተገኝተው ትርጓሜ መጻሕፍትን አጠናቅቀው በመምህርነት ተመረቁ። የቅኔ ብቃታቸውም የሚደነቅ እንደነበር ታውቋል። በትምህርታቸው ሒደት በደብረ ሊባኖስ ትንሽ ቆይታ አድርገዋል። በመቀጠልም አዲስ አበባ መጥተው አሥራ አራቱን የቅዳሴ ትርጓሜ ተምረው ወጥተዋል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ መመኪያ የሆኑት ሐዋርያው አቡነ ሚካኤል በ1923 ዓ.ም. በአድባራቱና በገዳማቱ በኃላፊነት ቦታ ተመድበው ተግባራቸውን በብቃት ተወጥተዋል።

ጀግናው ሐዋርያ አቡነ ሚካኤል በ1923 ዓ.ም. አበው የጵጵስና ማዕረግ ሊቀበሉ ወደ ግብፅ በሔዱ ጊዜ እሳቸው አንዱ እንደነበሩ ታውቋል። ከማዕረገ ጵጵስናው በኋላ ተመድበው ወደ ጎሬ ሔዱ። ጎሬ ሳሉ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል እየገፋ መምጣቱን ሰሙ። ጊዜ አላባከኑም። ሕዝቡን እየሰበሰቡ ስለሀገር ፍቅር ያስተምሩ ገቡ። ሕዝቡ ለነፃነቱና ለሐይማኖቱ መሥዋዕት መሆን እንዳለበት ማስረዳት በተከታታይ ቅስቀሳ አደረጉ። የተቻላቸውን ሁሉ ፈፀሙ። ምዕመናንን በፀረ-ፋሽስት አቋም አነፁ።

ለነፃነታችንና ለአንድነታችን እጅግ ቀናዒ የሆኑት ሐዋርያው አቡነ ሚካኤል በ1928 ዓ.ም. ግፈኛው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በመጣ ጊዜ በፅኑ-አቋም ከአርበኞች ጋር ተሰለፉ። አላወላወሉም። አርበኞች በርትተው እንዲዋጉ ቀሰቀሱ። አሁንም ሕዝቡ አንድነቱን አጠንክሮ በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ላይ እንዲነሳ አሳሰቡ። ሳይታክቱ ሰሩ። በቁርጠኝነትና በዓላማ ፅናት ቆሙ። እንቅስቃሴአቸው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልን ማሳሰቡ አልቀረም። ወራሪው ኃይል ምን ማድረግ ይችላል? አሰበ! አሰበ! አሰበ! ለጊዜው ግን አዲስ የስልት ሐሳብ አልመጣለትም። አቡነ ሚካኤል ደግሞ ቅስቀሳቸውን ከማፋፋም አልተቆጠቡም። ያለ ነፃነት ሐይማኖት አይታሰብም። ውሎአቸው በሙሉ ከአርበኞች ጋር ሆነ። በእርግጥ ጠብመንጃ አልተኮሱም። ቦምብ አልወረወሩም። ለራሳም በፃፉት ደብዳቤ ‹‹...ቱርኮች አገሬን ይዘውብኝ ባላጋራ ሁነውኛልና መርከብ የለኝ በባህር አልችላቸው›› ብለው ነበር። በዚህ ምክንያት የእንግሊዝ እስረኞችና ሚሲዮናውያኖቹ መርከብ እንዲሰሩላቸው ትእዛዝ ሰጡ›› ይሄን የሚለው ጳውሎስ ኞኞ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ በሞተር የሚንቀሳቀስ ጀልባ የተሰራው በዚሁ ዓመት በሚያዝያ ወር ነበር። ራሳም ስለመርከቦቹ ስራ ሲገልፅ፦

‹‹...በስራው ቴዎድሮስም ተካፋይ ነበሩ። 60 ጫማ ርዝማኔ 20 ጫማ ስፋት ያላቸው ሁለት ጀልባዎች ተሰሩ። እነዚህ ሁለት ጀልባዎች እያንዳንዳቸው አንድ መቶ ሰዎች ሲጫኑባቸው ጀልባዋ ወደ ባህሩ ውስጥ ያዘቀጠችው አራት ኢንች ያህል ብቻ ነበር። ሚሲዮናውያኖቹና ሕዝቡ ተሰብስቦ በአድናቆት ጀልባዎቹን ሲመለከት ቴዎድሮስ ደግሞ በጣም ደስ ብሏቸው ነበር።››

አፄ ቴዎድሮስ ፍፁም ደስታ የሚሰማቸው ያሰቡት ቴክኖሎጂያዊ ተግባር ተፈፅሞ ሲመለከቱ ብቻ ነበር ማለት ይቻላል። ለሚሰሩ እጆች ያላቸው አክብሮትና ፍቅር የንጉነታቸውን ደረጃ የሚያስት ስሜት ቅልቅል ነበር። ዎልድሜየር እንደዛሬው አዳዲስ ሥራዎች ተሰርተው በሚያዩበት ጊዜም ‹‹የሚያላዝኑ እጆች አሁን እነኚህንም አፈር ይበላቸው ይሆናል›› እያሉ ያደንቃሉ። አንድ ጊዜ እንዲያውም የዎልድሜየርን እጅ አገላብጠው ስምዋል።

እኒህ ናቸው አፄ ቴዎድሮስ፣ እኛ የሚገቡንና የምናውቃቸው። በዕውቀቱ ‹‹ንፁሃንና ጨዋዎችን›› ለሚያጠቃው የፍርድ መሰናክያ ጉድባ እራሱን ያጋለጠው እነዚህን በመሳቱና ችላ በማሉ ነው። በዕውቀቱ ባለፈው ሳምንት ፅሁፍ ከአንዲት ሽጉጥ አልመነዘሙም። በአቋም ግን ሁሉንም አድርገዋል። በሐሳብ ፈፅመዋል። ምን ቀራቸው?

አይበገሬው አቡነ ሚካኤል ፈፅሞ የማይመለሱ ሆኑ። በሀገር ጉዳይ ለማንም እጅ አይሰጡም። ማን ማንን ይገዛል? የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተጨነቀ። ግትሩን ጳጳስ ለማለዘብ አዲስ አበባ ውስጥ ከባንዳ ጳጳሳትና ካህናት ጋር ስብሰባ ተቀመጠ። በመጨረሻ ለአቡነ ሚካኤል ሽማግሌ ተላከ። ምዕመናኑን ለገናናው የኢጣሊያ መንግስት ተገገርነት ካስተባበሩ በሰማይ የሚጠብቋትን ገነት በምድር እንደሚያገኟት ተነገራቸው። ይህ የባንዳ ካህናት ድምፅ ነው! አቡነ ሚካኤል ግን ውድቅ አድርገዋል። እሳቸው ይኸነኑ ኢትዮጵያ ግን ነፃ ትውጣ! ይህ የአቡነ ሚካኤል ድምፅ ነው! ምድራዊ ገነትን መቼ ቋመጡ? ነፃነታቸውና ሐይማታቸው ስለተነካ አራስ ነብር ሆኑ። በዚህ ላይ የኢዮብን ትዕግስት አይቀበሉም። የዳሞትን ጀግንነት ታጥቀዋል። ለሀገራቸው ይሰዋሉ። ለሐይማኖታቸው ይሰየፋሉ። ትዕግሥታቸው አልቋል። አማላጅ ካህናትን በቁጣ ሸኟቸው። ዳግመኛ እንዳይመጡባቸው አስጠነቀቋቸው።

ጀግናው አርበኛና ሐዋርያ አቡነ ሚካኤል ከጥቁር አንበሣ አርበኞች ጋር የጠበቀ ግንኙነት ፈጠሩ። ለአርበኞች የማበረታቻ መልእክት በየጊዜው ይልኩ ገቡ። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሕዝቡን እንዲያስተባብሩለት በግምባር ጠርቶም አነጋግሯቸዋል። እሳቸው ግን ‹‹ለእናንተ የተገባ ርጉም ይሁን!›› በማለት መልስ ሰጥተዋል።

ቆራጡ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ባሁኑ ሰዓት ሱጴ በተባለ ቦታ ከአርበኞች ጋር ይገኛሉ። ጦርነቱ ተፋፍሟል። ብዙ አርበኞች ተሰውተዋል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪዎችም በብዛት ተገድለዋል። የደም ጎርፍ ይስተዋላል። አቡነ ሚካኤል ከጦርነቱ ወረዳ ገለል እንዲሉ ተነግሯቸዋል። እሳቸው ግን ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። በሞታቸው ቆርጠዋል። አርበኞችን እግር በእግር እየተከታተሉ ሲያበረታቱ ይስተዋላል። ጦርነቱ ቀጥሏል። ሱጴ የደም መሬት ሆናለች። ድም! ድም! ቡም! ድም! ድም! ቡም! ቡም! ሬሣ ተከምሯል። አቡነ ሚካኤል የተሰዉ አርበኞችን መሣሪያ ወራሪው ኃይል እንዳይማርክ በሚደረገው ተግባራዊ እንቅስቃሴ መሪ ተዋናይ ሆነዋል። ዝናር ያልታጠቁ አርበኛ ወጥቷቸዋል። ጦርነቱ እንደ ቀጠለ ነው! ድም! ድም! ድም! ድም! ቡም! ቡም! ቡም! ቡም! ድም! ድም! አሁን ለወራሪው ኃይል ተጨማሪ ተዋጊና የጦር መሳሪያ መጥቶለታል። ለአርበኞች ግን ማንም የደረሰላቸው አልነበረም። የሰው ኃይላቸው መንምኗል። ጥይትም አልቆባቸዋል። ግፈኛው ወራሪ የበላይነትን ይዟል። አርበኞች ተከብበዋል። ምን ለማድረግ ይቻላል? ጥይት አልቆባቸው በእልህ እየተናጡ ቆመዋል። ሁለት ናቸው። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የአርበኞችን እጅ በሰንሰለት አሥሯል። አንድ ቡልቅባሽ ሽጉጥ ይዟል። ወደ አቡነ ሚካኤል ተጠግቷል! ከፊቱ ቁጣ ይነበባል። ምን ሊያደርጋቸው ይሆን? ሽጉጡን በግምባራቸው ላይ ደገነ። አቡነ ሚካኤል ምንም የፍርሃት ስሜት አላሳዩም። መለሰው። እንደገናም ደገነባቸው። ሞትን ንቀዋል። ዘና ብለው ቆመዋል። በካሚዮን ወደ ጎሬ ተጫኑ ሰማዕትነትን በፀጋ ተቀበሉ። አንድ! አንድ! አንድ! ለጀግናው ሐዋርያ ለአቡነ ሚካኤል አንድ ቋሚ መታሰቢያ ሐውልት በጎሬ ከተማ ለምን አልታነፀላቸውም? አሁንም ይቻላል! ኢትዮጵየዊነት ያሸንፋል!

ከእንግዲህ መቃብር በርትተህ ተማር፤
ጸመ ድጓ ይዞ መጣልህ መምህር::

ከሥነ ቃል የተወሰደ

የዳግማዊ ቴዎድሮስን ...

ከገፅ 3 የዞረ

ኩታቸውን ከትከሻቸው ገፍፈው የማልበስ፣ ተበድሮ የመመፅወት፣ ‹‹የእንግዶችን እግር ማጠብ ይገባናል›› እስከማለት የመጐናበስ ሥነ-ምግባራዊ ልቀት የአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ግርማ ነው። አይንህን ‹‹ለብርሃን›› ከፍተህ እንድትጓዝ ይሄን ያህል የታሪክ ሸኝት ከተደረገልህ በቂ ነውና ወደ አፄ ቴዎድሮስ የቴክኖሎጂ ስልጣኔ አባትነት እንሸጋገር።

በፕሮፌሰር ዶናልድ ክራሚ ግምገማ እንጀምር

‹‹ማብራራቱና መተንተኑ ቢጐድለውም የዘመናዊ ስልጣኔ ሀሳብ የገባው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ንጉሥ ነበር›› ይላል።

ባህሩ ዘውዴ ይሄንን የአፄ ቴዎድሮስን የዘመናዊ ሥልጣኔ ቀደምትነት ተቀብለው ለውጥ ለማድረግ ልዩ ትኩረት የሰጡት ካስተዳደር ይልቅ በወታደራዊ መስክ ነው ይላሉ። ወታደራዊ ኃይልና የፖለቲካ ስልጣን ምንጊዜም ተወራራሽ እንደሆኑ የጠቆሙት ባህሩ ‹‹አገር አሰለጥናለሁ ያለ መሪ ሁሉ መጀመሪያ የሚያተኩረው በጦር ሰራዊቱ እንደሆነ ተደጋግሞ የታየ ነገር ነው። ...ቴዎድሮስ ሥልጣኑን ለማዳበር ሠራዊቱን በሦስት አቅጣጫዎች ማሻሻል አለብኝ ብሎ ተነሣ። በአደረጃጀት፣ በሥነ-ሥርዓትና በጦር መሳሪያ።›› (የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847-1983 ገፅ 33)

አፄ ቴዎድሮስ በወታደራዊ መስክ ሾልከው አገር ለማዘመን ያስችላል ያሉዋቸውን የአደረጃጀት፣ የሥነ-ሥርዓትና የትጥቅ ግቦች ወደተግባር ለውጠው ውጤት ማየት ጀምረው እንደነበር በብዙ የታሪክ ምሁራን ተመስክሯል። ሰራዊቱን ለማደራጀት የተበታተነውን የግብር አሰባሰብ ወደ አንድ ለማምጣት የወሰዱት እርምጃ የመጀመሪያ ሙከራቸው ነበር። በዚህ መስክ ወታደሩን ከተሰሪነት (በየባላገሩ ቤት እየገባ ከመቀለብ) እንዲወጣና በደምወዝ እነዲተዳደር አድርገው ነበር። በወር እስከ ሺ ብር የሚከፈላቸው ወታደራዊ መሪዎች ያሉበት ዘመናዊ ሠራዊት ለማቋቋምም ችለው ነበር። ይሄ ዘመናዊ ጦር ተጠሪነታቸው ለመሳፍንቱ የነበሩትን የተለያዩና የተበታተኑ ጦሮች በማሰባሰብ አንድ አገር አቀፍ ብሔራዊ ጦር ለመጀመሪያ ጊዜ ለማቋቋም የተቻለበት ነበር። ወታደራዊ አደረጃጀቱ የሰራዊቱን የተዋረድ ሹመት ተግባር ላይ ያዋለ እንደነበር ይነገራል። ባህሩ ዘውዴ አስር ዓለቃ፣ ሃምሣ አለቃ እና ሺ አለቃ... የሚል ወታደራዊ ማዕረግና አደረጃጀት የተጀመረው በአፄ ቴዎድሮስ እንደነበር ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ።

አፄ ቴዎድሮስ ከወታደራዊ ሥርዓት ባለፈ ሰራዊቱን ዘመናዊ ጦር መሳሪያ የማስታጠቅ ህልማቸውን ለመተግበር የተነሱት በግዢ ሳይሆን በአገር ውስጥ ምርት እንዲሆን መፈለጋቸው ታላቁ የስልጣኔ አርአያ ያደርጋቸዋል። አፄው ከሴባስቶፖል መድፍ አስቀድሞ ሌላ መድፍ የመስራት ገድልም ፈፅመዋል። ከደባርቂት ውጊያ ማግስት የግብያችን መድፍ በመመልከት ግንድ አስፈልፍለው ባሩድ በመቅበር ክሩቅ የሚፈነዳ መድፍ ለመስራት ሞክረው ነበር። ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ብረቶችን በመቆራረጥና ከባሩድ ጋር በመደባለቅ የጠመንጃ አረር ይመረት ነበር። በዚህ አረር የማምረት ተግባር ላይ አፄ ቴዎድሮስ ቀጥተኛ በወዛደርነት ተሳታፊ ነበሩ።

‹‹መጋቢት 6 ቀን 1858 ዓ.ም. ቴዎድሮስ ለራሳም በፃፉት ደብዳቤ ‹‹...ቱርኮች አገሬን ይዘውብኝ ባላጋራ ሁነውኛልና መርከብ የለኝ በባህር አልችላቸው›› ብለው ነበር። በዚህ ምክንያት የእንግሊዝ እስረኞችና ሚሲዮናውያኖቹ መርከብ እንዲሰሩላቸው ትእዛዝ ሰጡ›› ይሄን የሚለው ጳውሎስ ኞኞ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ በሞተር የሚንቀሳቀስ ጀልባ የተሰራው በዚሁ ዓመት በሚያዝያ ወር ነበር። ራሳም ስለመርከቦቹ ስራ ሲገልፅ፦

‹‹...በስራው ቴዎድሮስም ተካፋይ ነበሩ። 60 ጫማ ርዝማኔ 20 ጫማ ስፋት ያላቸው ሁለት ጀልባዎች ተሰሩ። እነዚህ ሁለት ጀልባዎች እያንዳንዳቸው አንድ መቶ ሰዎች ሲጫኑባቸው ጀልባዋ ወደ ባህሩ ውስጥ ያዘቀጠችው አራት ኢንች ያህል ብቻ ነበር። ሚሲዮናውያኖቹና ሕዝቡ ተሰብስቦ በአድናቆት ጀልባዎቹን ሲመለከት ቴዎድሮስ ደግሞ በጣም ደስ ብሏቸው ነበር።››

አፄ ቴዎድሮስ ፍፁም ደስታ የሚሰማቸው ያሰቡት ቴክኖሎጂያዊ ተግባር ተፈፅሞ ሲመለከቱ ብቻ ነበር ማለት ይቻላል። ለሚሰሩ እጆች ያላቸው አክብሮትና ፍቅር የንጉነታቸውን ደረጃ የሚያስት ስሜት ቅልቅል ነበር። ዎልድሜየር እንደዛሬው አዳዲስ ሥራዎች ተሰርተው በሚያዩበት ጊዜም ‹‹የሚያላዝኑ እጆች አሁን እነኚህንም አፈር ይበላቸው ይሆናል›› እያሉ ያደንቃሉ። አንድ ጊዜ እንዲያውም የዎልድሜየርን እጅ አገላብጠው ስምዋል።

እኒህ ናቸው አፄ ቴዎድሮስ፣ እኛ የሚገቡንና የምናውቃቸው። በዕውቀቱ ‹‹ንፁሃንና ጨዋዎችን›› ለሚያጠቃው የፍርድ መሰናክያ ጉድባ እራሱን ያጋለጠው እነዚህን በመሳቱና ችላ በማሉ ነው። በዕውቀቱ ባለፈው ሳምንት ፅሁፍ ከአንዲት ሽጉጥ አልመነዘሙም። በአቋም ግን ሁሉንም አድርገዋል። በሐሳብ ፈፅመዋል። ምን ቀራቸው?

አይበገሬው አቡነ ሚካኤል ፈፅሞ የማይመለሱ ሆኑ። በሀገር ጉዳይ ለማንም እጅ አይሰጡም። ማን ማንን ይገዛል? የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተጨነቀ። ግትሩን ጳጳስ ለማለዘብ አዲስ አበባ ውስጥ ከባንዳ ጳጳሳትና ካህናት ጋር ስብሰባ ተቀመጠ። በመጨረሻ ለአቡነ ሚካኤል ሽማግሌ ተላከ። ምዕመናኑን ለገናናው የኢጣሊያ መንግስት ተገገርነት ካስተባበሩ በሰማይ የሚጠብቋትን ገነት በምድር እንደሚያገኟት ተነገራቸው። ይህ የባንዳ ካህናት ድምፅ ነው! አቡነ ሚካኤል ግን ውድቅ አድርገዋል። እሳቸው ይኸነኑ ኢትዮጵያ ግን ነፃ ትውጣ! ይህ የአቡነ ሚካኤል ድምፅ ነው! ምድራዊ ገነትን መቼ ቋመጡ? ነፃነታቸውና ሐይማታቸው ስለተነካ አራስ ነብር ሆኑ። በዚህ ላይ የኢዮብን ትዕግስት አይቀበሉም። የዳሞትን ጀግንነት ታጥቀዋል። ለሀገራቸው ይሰዋሉ። ለሐይማኖታቸው ይሰየፋሉ። ትዕግሥታቸው አልቋል። አማላጅ ካህናትን በቁጣ ሸኟቸው። ዳግመኛ እንዳይመጡባቸው አስጠነቀቋቸው።

ጀግናው አርበኛና ሐዋርያ አቡነ ሚካኤል ከጥቁር አንበሣ አርበኞች ጋር የጠበቀ ግንኙነት ፈጠሩ። ለአርበኞች የማበረታቻ መልእክት በየጊዜው ይልኩ ገቡ። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሕዝቡን እንዲያስተባብሩለት በግምባር ጠርቶም አነጋግሯቸዋል። እሳቸው ግን ‹‹ለእናንተ የተገባ ርጉም ይሁን!›› በማለት መልስ ሰጥተዋል።

ቆራጡ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ባሁኑ ሰዓት ሱጴ በተባለ ቦታ ከአርበኞች ጋር ይገኛሉ። ጦርነቱ ተፋፍሟል። ብዙ አርበኞች ተሰውተዋል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪዎችም በብዛት ተገድለዋል። የደም ጎርፍ ይስተዋላል። አቡነ ሚካኤል ከጦርነቱ ወረዳ ገለል እንዲሉ ተነግሯቸዋል። እሳቸው ግን ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል። በሞታቸው ቆርጠዋል። አርበኞችን እግር በእግር እየተከታተሉ ሲያበረታቱ ይስተዋላል። ጦርነቱ ቀጥሏል። ሱጴ የደም መሬት ሆናለች። ድም! ድም! ቡም! ድም! ድም! ቡም! ቡም! ሬሣ ተከምሯል። አቡነ ሚካኤል የተሰዉ አርበኞችን መሣሪያ ወራሪው ኃይል እንዳይማርክ በሚደረገው ተግባራዊ እንቅስቃሴ መሪ ተዋናይ ሆነዋል። ዝናር ያልታጠቁ አርበኛ ወጥቷቸዋል። ጦርነቱ እንደ ቀጠለ ነው! ድም! ድም! ድም! ድም! ቡም! ቡም! ቡም! ቡም! ድም! ድም! አሁን ለወራሪው ኃይል ተጨማሪ ተዋጊና የጦር መሳሪያ መጥቶለታል። ለአርበኞች ግን ማንም የደረሰላቸው አልነበረም። የሰው ኃይላቸው መንምኗል። ጥይትም አልቆባቸዋል። ግፈኛው ወራሪ የበላይነትን ይዟል። አርበኞች ተከብበዋል። ምን ለማድረግ ይቻላል? ጥይት አልቆባቸው በእልህ እየተናጡ ቆመዋል። ሁለት ናቸው። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የአርበኞችን እጅ በሰንሰለት አሥሯል። አንድ ቡልቅባሽ ሽጉጥ ይዟል። ወደ አቡነ ሚካኤል ተጠግቷል! ከፊቱ ቁጣ ይነበባል። ምን ሊያደርጋቸው ይሆን? ሽጉጡን በግምባራቸው ላይ ደገነ። አቡነ ሚካኤል ምንም የፍርሃት ስሜት አላሳዩም። መለሰው። እንደገናም ደገነባቸው። ሞትን ንቀዋል። ዘና ብለው ቆመዋል። በካሚዮን ወደ ጎሬ ተጫኑ ሰማዕትነትን በፀጋ ተቀበሉ። አንድ! አንድ! አንድ! ለጀግናው ሐዋርያ ለአቡነ ሚካኤል አንድ ቋሚ መታሰቢያ ሐውልት በጎሬ ከተማ ለምን አልታነፀላቸውም? አሁንም ይቻላል! ኢትዮጵየዊነት ያሸንፋል!

ከእንግዲህ መቃብር በርትተህ ተማር፤
ጸመ ድጓ ይዞ መጣልህ መምህር::

ከሕይወት የሚበልጥ ዓላማ የለም



በእውቀቱ ስዩም

ዓለማየሁ ገላጋይ ስለጃፓንና ስለቴዎድሮስ ክርክር አስጀምሮኝ ነበር። ባለፈው ሣምንት ጃፓንን በጓሮ በር አሰናብቶ አጤ ቴዎድሮስን ብቻ ይዞ ጠበቀኝ። ክርክሬን ዛሬ እቋጫለሁ። ባለፈው ሣምንት የተሰጠኝ ምላሽ ምንም እንኳን ከአፈጮሌነት ሙሉ በሙሉ የፀዳ ባይሆንም ወደ መከራከርያው ርዕሰ ጉዳይ ቀረብ የሚሉ ነጥቦችን ይዟል። ጥሩ ሙከራ ነው።

ዘግይቶ ክርክራችንን ለታደመ አንባቢ የኔ አቋም ‹‹ዳግማዊ ቴዎድሮስ የሞራል አርአያ ተደርገው የሚቆጠሩ አልነበሩም። ከዘመነኞቻቸው ጋራ ሲነፃፀሩ ንጉሡ በሞራል ኋላቀር ነበሩ›› የሚል ነው።

በሞባይል በደረሱኝ አንዳንድ መልእክቶች እንደተረዳሁት ሐተታዬ ያስከፋቸው ሰዎች አሉ። ግን ምን ይደረግ? ሰዎችን ሳያስከፉ እውነት መናገር፤ ሳይረጥቡ መታጠብ አይቻልም››

በዘመናችን ታሪክን የፖለቲካ ገባር የማድረግ አዝማሚያ አያለሁ። አዝማሚያው የጌቶችም የሸፍቶችም ነው። በኔ ግምት ይህ አዝማሚያ የታሪክን ንፁህ ግንዛቤ ይበክላል። ነገሮችን የማወቅ የጋለ ፍላጐት ብቻውን ታሪክን ለማጥናት በቂ ይመስለኛል።

ወደ ክርክሩ።

ዓለማየሁ ያጤ ቴዎድሮስን የሥነ ምግባር አርአያነት ለማሣየት የሚከተለውን አንቀጽ ጠቅሷል።

‹‹...ቴዎድሮስ ጋይንት ሠፍረው ሳለ ወታደሮቻቸውን በባላገሩ ላይ ተሠሪ አገቡ። ባላገሩ እንዲቀልብ በየቤቱ ማስገባት ማለት ነው። ተሠሪ ከገቡት ወታደሮች መካከል አንዱን ባላገር ገደለው። የሟች ወገንም ከቴዎድሮስ ዘንድ መጥቶ አመለከተ። ቴዎድሮስም ወታደራቸውን ሁሉ አፈርሳታ አስቀምጠው ገዳዩን አውጣ ብለው ያዙት። ወታደሩ በመሳው አድሞ ገዳዩን አላየንም እያለ በቁስ እየተገዘተ ወጣ። የሟች ገዳይ ወታደር በመጥፋቱ ቴዎድሮስ ተናደው ‘ወታደር ብላ፣ ባላገር አብላ ያልሁ እኔ ነኝ ደመኛህም እኔ ነኝና እኔን ግደል’ ብለው ተነስተው ለከሳሹ ነገሩት። ከሳሹም እኔ ንጉሥ መግደል አይቻለኝም አለ። ቴዎድሮስም እንግዲያውስ ደም በከንቱ አይቀርም ብለው ለሟች ወገን የደም ገንዘብ ዋጋ ሰጥተው ሸኙት››

ይሄን ትረካ ያቀረበው የቴዎድሮስን ‹‹የሥነ ምግባር ሥልጣኔ›› ያሳይልኛል ብሎ ነው። እስቲ የጥቅሱን ቡሰን ፈታተን በብልት በብልት እንፈትሸው።

(ሀ) በጥቅሱ ውስጥ ቴዎድሮስ ‹‹ወታደር ብላ፣ ባላገር አብላ›› የሚል ግፈኛ ሕግ ማውጣታቸውን ይናዘዛሉ። ይህም፣ ንጉሡ ወታደሮቻቸውን በደመወዝ ያስተዳድሩ ነበር የሚለውን ፈጠራ ያስተባብላል።

(ለ) ግፈኛው ሕግ ለወታደሩ ገደብ የለሽ ሥልጣን ሰጥቶታል። ገደብ የለሽ ሥልጣን ያለገደብ ያባልጋል። እንግዳው ባለቤቱን እስከመግደል ደርሷል። ቴዎድሮስ አቤቱታው ሲቀርብላቸው የችግሩ ምንጭ ግፈኛው ሕግ መሆኑን ተረድተዋል። ይሁን እንጂ ሕጉን ማፍረስ ሲገባቸው አላደረጉትም። በአለቃ ዘነብ ትረካ መሠረት በጋይንት ይህ ክስተት ከተፈፀመ ከወር በኋላ በጨጨሆ፣ ወታደር በባላገር ቤት ጥገኛ ሕዋስ ሆኖ እንዲገባ ተፈቅዶለታል። ሕጉን ያፈረሡት ካጤ ቴዎድሮስ የመሰት በትር ያመለጡት እምዬ ምኒልክ ናቸው።

(ሐ) ንጉሡ ደመኛህ እኔ ነኝ ብለው ባላገሩ እንዲገድላቸው መጋበዛቸው የይስሙላ ይሁን የምር አይታወቅም። ግን የምር ሆኖ ተጋባዡ ግብዣውን ቢቀበል ኑሮ መፍትሄ ይመጣ ነበር? አይመስለኝም። ችግሩ የሚፈታው ሕጉን ባጠቃላይ በማስወገድ እንጂ ንጉሡን በማስወገድ አልነበረም።

ባላገሩ የንጉሡን የግደለኝ ግብዣ አለመቀበሉ ‹‹በተቀባው ላይ እጅህን አታንሣ›› የሚለውን የጊዜውን ሕግ አክብሮ ነው። ታዲያ ጥቅሱ የሚያስረዳው የንጉሡን ስነ ምግባር ታላቅነት ነው ወይስ የስም የለሹን ባላገር ጨዋነት? ያለጥርጥር ሁለተኛው መልስ ነው።

ቴዎድሮስ ከባላገሩ ጋር ያላቸው የባላንጣነት ግንኙነት ሊቃውንት ከሚነግሩን ፈርቀዳጅነታቸው ጋር የሚጣጣም አይደለም። ሌላው ቀርቶ ከዘመነ መሣፍንት ትልልቅ መሪዎች ፖሊሲ ጋር ስናነፃፅረው ፖሊሲያቸው ኋላቀር ይሆንብናል። ከዘመነ መሣፍንት የኢትዮጵያ ዋና መሪዎች አንዱ የሆኑት ራስ ጉግሣ የባላገርን ንብረት በጉልበት ለሚቀማ ወታደር ከባድ ቅጣት ደንግገው ነበር። ፀሐፊ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ የሚሉትን እንስማ፦

‹‹...ራስ ጉግሣ መሬት የረቢ ናት። መሬት ያለው የሰም። አሁንም ዶሮ ያረደ በግ ይከፍላል። በግ ያረደ በሬ ይከፍላል። በሬ ያረደ የነፍስ ዋጋ ይከፍላል ብሎ አዋጅ ነግሮ አገሩን አለማው›› (ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ፣ ገፅ 119)

ስማቸው የማይታወቅ የቴዎድሮስ ዜና መዋዕል ፀሐፊ እንደዘገቡት መይሣው ካሣ ለወታደሮች የሰጡት ትዕዛዝ ‹‹የምትበላውን ያቅምህን ብላ። ቋንጣህን ዘልዝለህ አድርቅ። የተረፈውን ላም ግን እያረድህ መሬት ቆፍረህ ቅበረው›› የሚል ነበር። ወታደሩ ከስንቁ የተረፈውን በሬና ላም መሬት ቆፍሮ የሚቀብረው ጥሻ ሆኖ እንዲበቅልለት አይደለም። ባላገሩን ድራሹን ለማጥፋት ነው።

ቫልድማየር በጊዜው እንደተመለከተው የንጉሡ ወታደሮች በቅሎአቸውንና ፈረሶቻቸው የሚያሠማሩት በመስክ ላይ ሳይሆን በገበሬው አዝመራ ላይ ነበር። ገበሬው በለቅሶ ቢለምን የሚራራለትም ሆነ የሚሰማው አልነበረም።

ዓለማየሁ፦ አጤ ቴዎድሮስ በመጨረሻ ሰዓታቸው የእንግሊዝ እሥረኞችን ሳይገድሉ ማሰናበታቸውን ይጠቅሳል።

‹‹...አጤ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ በመጨረሻ የሽንፈት ሰዓት ላይ ሆነው ከአሽከሮቻቸው አንድ አማራጭ ቀረበላቸው አማራጩን ያቀረቡት ራስ እንግዳ ነበሩ። ‹‹ለምን ያዝናሉ? እነዚህን ነጮች መልሰን እናምጣና ገድለናቸው እንሸሽ ወይም ተዋግተን እንሙት።›› አሉ። አጤ ቴዎድሮስ ተስፋ ከመቁረጣቸው ብቻ ይሄንን አማራጭ አልተቀበሉትም። አጤው ለአላማ እንጂ ለበቀል አይገድሉም። በቁጣ ራስ እንግዳን እያዩ እንዲህ አሉ ‹‹...አንተ አህያ ባለፈው ሁለት ቀን ውስጥ የፈጀሁት ሰው አይበቃምን? እነዚህን ነጮች ገድዬ አበሻን በደም እንዳጥባት ነው የምትፈልግ?››

ያሠመርሁት እኔ ነኝ። ያሠመርሁትም የተጠቀሰው ትረካ ከተሠመረበት ትርጓሜ ጋር ያለውን መራራቅ ለማሳየት ነው። አጤ ቴዎድሮስ በመጨረሻ ሰዓት ነጮችን ማሰናበታቸው ጥሩ አድርገዋል። ግን በሞቴ ይሄ ትረካ ‹‹አጤው ለበቀል አይገድሉም›› የሚለውን ሐሳብ ለመደገፍ የሚቀርብ ነው? አጤ ቴዎድሮስ በትረካው ውስጥ በራሳቸው አንደበት በመጨረሻ ሰዓት ብዙ ሰው መፍጀታቸውን በፀፀት እየተናዘዙለት ዓለማየሁ አይሰማም። ምን ይሻላል? ንጉሡ የእንግሊዝን መቅረብ ሲያዩ በመቅደላ ያሉትን አያሌ እሥረኞች እጅና እግር እየቆረጡ ገደል ጨምረዋቸዋል። ይሄ ጭፍጨፋ በቀል ካልሆነ ዓላማው ምንድነው?

የመጨረሻው የክርክር ነጥብ ለበቀል መግደል ክፉ ሲሆን ለዓላማ መግደል ግን ጥሩ ነው የሚል አደገኛ መልእክት ያስተላልፋል። አንድ የደም ጥማት ያለበት (ሴዲስት) ግለሰብ ጥማቱን ለማርካት የሚያስፈልገው፣ ያገር መሪ መሆንና ለወንጀሉ መሸፈኛ አንዳች አላማ መፍጠር ሲሆን ነው።

ግፍን የክብር ልብስ በማልበስ፣ ግፍን ከባሕላችን ማስወገድ አንችልም። እቅጩን ለመናገር ከሕይወት የሚሻል ዓላማ በዚህ አለም ላይ የለም። ታላቅ ዓላማ ላይ ለመድረስ የትኛውንም መንገድ መያዝ ተፈቅዷል ለሚሉ ሰዎች ያቶ ሀዲስ አለማየሁን ጥቅስ ጋብገፄ ልሰናበት።

‹‹...ክፉ መንገድ እመልካም ግብ አያደርስም። ክፉ ሥራ እንደተኮሱት ጥይት አላማውን ይገድላል። ክፉ ሥራ ሠርቶ መልካም መልካም ውጤት አገኛለሁ ማለት እንክርዳድ ዘርቶ ስንዴ ለማምረት እንደ መመኘት ነው።››

(የልምጥጥ ገፅ 217)

ድህረ-ኢህአዴግ ... ከገፅ 9 የዞረ

ሊኖሩን እንደሚችሉ አይነገረንም። እንደ 2ኛ ክፍል ተማሪ፦ እውነት/ሐሰት ብቻ ብለህ ምረጥ እንባላለን። እኛም ይሄው ስለሚቀለን ለስንፍናችን ጥሩ ሰበብ አገኘን ማለት ነው። የጠያቂዎቻችንን ፊት እና የሃይል ሚዛን አይተን የሚያዋጣ የመሰለንን እንመርጣለን። በዚህ ረገድ የባለቤቱ ግላዊ የፖለቲካ ስህተቶች እንደተጠበቁ ሆነው ‹‹የ3ኛ አማራጭ መፍትሄን›› ሊያቀርብ የሞከረውን የኢዴፓው አቶ ልደቱ አያሌውን አማካይ መስመር ከገፈው ፓርቲ በላይ ሊያጠፉት የተነሱት የተቃውሞ ጐራ ውስጥ የተከተሙት የ60ዎቹ ትውልድ አባላት መሆናቸውን ስንገነዘብ፤ ከፖለቲካዊ ፉክክርም በላይ እንደ ህዝብ የሚንፀባረቅብንን ወደአንድ ጐራ ብቻ የመከተት ጠርዘኛ አቋማችንን እና ከመመርመር ይልቅ አሉባልታ የመቀበል ጠባያችንን ያመለክታል። አሉባልታ ደግሞ መመርመር የማይሻ የሰነፍ ሰው የመረጃ ምንጭ ነው።

ስለዚህም በእውር-ድንብር ጉዞ የተማሩ አፈ-ጮሌዎች ሲያታልሉን እንኖራለን። ሚዛን አንጠብቅም፤ አናመዛዝንም። ካንዱ ጫፍ ወደሌላኛው ስንንገዋገው አገራችንንም እኛንም ለአደጋ አሳልፈን እንሰጣለን። ከእኛ የተለየ ሃሳብ ያለውን በመናፍቅነት እየፈረጅን ውጉዙ-ከ-መአሪዮስ ስናደርግ የበለጠ ወደ ጽንፈኝነት እየገፋነው አቻችሎ የሚያኖረንን መሃከለኛ መንገድ እናጠፋለን።

እርስ-በርሳችንም በውሃ-ቀጠነ ምክንያት የፖለቲካ ፀጉር ስንሰነጥቅ እና ስንሻኮት በራችንን ለውጭ ኃይሎች ጣልቃ-ገብነት እናመቻቻለን። እዚህ ጋር አንድ ወዳጀ ያጫወተኝን ታሪክ ልጥቀስ። እነሆ፦

ጃርቶች በብርድ ወራት ብቻቸውን ሊኖሩ አይችሉም። በመሆኑም ከቅዝቃዜ ለማምለጥ ሲሉ እርስ-በርሳቸው ተጠጋግተው እና ክብ-ሠርተው ይሟሟቃሉ። ነገር ግን የጃርቶች እሾህ የሚዋጋ በመሆኑ ምቾትም አይሰማቸውም። እሾሁ ወጋን! ብለው ቢነጣጠሉ ደግሞ የሰው ጦር እያደነ ይጨርሳቸዋል። በመሆኑም፦ ጃርቶች በዚች ምድር ሲኖሩ ከእሾህና ከጦር መምረጥ ይኖባቸዋል። ታዲያ እኛ የሰው ልጆ የሆንን ኢትዮጵያውያን ከጃርት እናንሳለን?

በታሪካችን ውስጥ በተከሰቱ ክፉ ገጠመኞች የተነሳ እኛና/ሌሎች (We/others) በሚል የከረረ የልዩነት ድንበር ተከልለን በአሉታዊ የቅራኔ ትስስር የተያያዝነው የእምነት እና የብሔር ቡድኖች፤ ከ20 ዓመታት ወዲህ በተከሰቱ ዓለማዊ እና ሃገራዊ የፖለቲካ ክንውኖች ሳቢያ ይህን የልዩነት መስመር ያደመቅነው ይመስለኛል። የመንግስትም ሞራል-አልባ የፖለቲካ አጨዋወት በሁሉም እሴቶቻችን ላይ ለሥልጣኑ ሲል ቁማር በመቆመሩ ፍጥጫችንን አባብሶታል። በውጤቱም፦ ልዩነቶቻችን በረከቶች እንጂ መርገምቶች ሳይደረጉ በአንድ አገር ጥላ ስር የሚያስኖሩን አገራዊ የዝምድና ገመዶች እየላሉ እንደሆነ ተሰምቶኛል። ልዩነቶቻችን ላይ በማተኮር ተመሳሳይነታችንን የዘነጋነው ይመስለኛል።

መለያየት እጅግ የቀለለ የሰነፍ ሰው ስራ ነው። ማፍረስ አይከብድም፤ ትዕግስት አይጠይቅምና! ይኸው በጉራፈርዳ እንዳየነው በ24 ሰዓት ውስጥ ሁሉንም መመነቃቀር እና መንግሎ ሜዳ ላይ መጣል ይቻላል። አንድ መሆን ግን የትጉህ ሰዎች መልካም ፍሬ ነው። መገንባት ፈታኝ ነው- ጥበብ ይጠይቃልና! ህብረት በፍቅር የመዋሃድ ጉዞ ነው። ዳገት ቁልቁለት፣ አባጣ ጎርባጣ ቢኖረውም የአብሮነት ጉዞ ብቻ ከማዝገም ሺህ ጊዜ ይልቃል። ምሉዕነት ከአብሮነት፤ ጐዶሎነት ከብቸኝነት ይመጣሉና እኛ ግን የቀደመውን መልካም ነገር ብንመኝ ይበጀናል። አዎ በአብሮነት ምሉዕ መሆንን በነፃ-ፈቃዳችን ብንመርጥ ህይወታችን ይበለፅጋል። እኛ ከተዋደድን ቋንቋም፣ ብሔርም፣ ዘርም፣ ሃይማኖትም የህይወታችን ማጣፈጫ ቅመሞች ይሆናሉ። ምክንያቱም አንዳቸውም ስንኳ ከፍቅር አይበልጡምና! ፍቅር ደግሞ ከልብ እምነት እንጂ ካይምሮ ጥርጣሬ ፈልቆ አያውቅም።

ፕሮፌሰር መስፍን በ1986 ዓ.ም. ባሳተሙት ‹‹ኢትዮጵያ ከየት ወዴት?›› በሚለው መጽሐፋቸው፦ ‹‹...የኢትዮጵያዊነት ችግር ኢትዮጵያ አይደለችም፤ ችግሩ የስርዓት ችግር ነው። የቤቱ መቃጠል ለትኋኑ በጀኝ እንዳለው ቂል እንዳንሆን።...›› ሲሉ ካስጠነቀቁ በኋላ በዛው ገጽ 32 ላይ ትንሽ ወረድ ብለው ደግሞ፦ ‹‹...ሆኖም የኢትዮጵያ ታሪክ ሊያስተምረን እንደሚችለው ኢትዮጵያዊነት እንደላስቲክ ነው። ሲስቡት ይሳባል፤ ሲለቅቁት ይሰበሰባል። ማለት -ይሳብና ይሳሳል እንጂ አይበጠስም።›› ብለው ነበር። ታዲያ ፕሮፍ በአዲስ ጉዳይ መጽሔቱ ቃለ-ምልልስ ላይ ለምን ይዜን ያህል ተስፋቸው ተሟጠጠ?

ምስጋና- አስጀምሮ ሳይቆረጥ ላስጨረሰኝ የብርሃንና ሰላም ጌታ!

አዲስ መጽሐፍ በገበያ ላይ

በቅርቡ በወጣው የሊዝ አዋጅ ላይ ያተኮረ

‹የኢትዮጵያ መሰረታዊ የሊዝ ሕግ ሀሳቦችና የሚያስከትላቸው ችግሮች›

በሚል ርእስ

መጽሐፍ ታትሞ በገበያ ላይ ዋለ!

በመጽሐፉ አዲሱ የሊዝ አዋጅ፣

- በሕገመንግስቱ የተረጋገጠውን የዜጎች የንብረት ባለቤትነት መብት ከህዝብ ጥቅምና መብት ጋር በተጣጣመ መልኩ ሚዛናዊ ከማድረግ አንጻር ምን ያህል ተሳክቶለታል?
- የነባር ባለይዞታዎችን መብት በማስፋትም ሆነ በማጥበብ ምን አዲስ ነገር ይዞ መጣ?
- መሬትን በሊዝ ይዞ የሚጠቀም ሰው መብትና ግዴታዎቹ ምንድ ናቸው?
- የሊዝ አዋጁ ከመሬት ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ የሙስና ተግባራትን ይቀንሳል ወይስ ያባብሳል?
- ከሊዝ አዋጅ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበት ስርአት ፍትሀዊ ነው ወይ?
- በአዋጁ ላይ ምን አይነት ማሻሻያዎች ሊደረጉ ይገባል?

የሚሉና ሌሎች በርካታ በህዝቡ የሚነሱ ጥያቄዎችን በማንሳት ለጥያቄዎች የተብራራ ምላሽ እንዲሁም የማሻሻያ ሀሳቦችን ይዘላችሁ ቀርቧል።

በመካሻ አበራ (ኤል.ኤል.ቢ)



መጽሀፉን ገዝተው ያንብቡ!
ዋና አከፋፋይ ዓይናለም መጻሕፍት መደብር